# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የ2017 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ

*(በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክርቤት የፀደቀ)*

ሐምሌ 2016

**ባህርዳር**

# ማውጫ

ማውጫ ........ i
መግቢያ ........ 1
የክልሉ አጠቃላይ ገፅታ በአጭሩ ........ 3
ክፍል አንድ፡- የ2016 በጀት ዓመት የልማትና መልከም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ........ 5
1.1. የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻፀም ........ 5
1.1.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻፀም ........ 5
1.1.2. የሥራ አጥነት ሁኔታ ........ 6
1.1.3. የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ........ 7
1.1.4. የድህነት ሁኔታ ........ 8
1.1.5. መዋዕለ-ንዋይ አፈጻፀም ........ 8
1.1.6. የልማት ፋይናንስ አፈጻጸም ........ 9
1.2. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች አፈጻፀም ........ 10
1.2.1 የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም ........ 10
1.2.1.1. ግብርና ልማት ........ 10
1.2.1.2. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ........ 15
1.2.1.3. የማዕድን ሀብት ልማት ........ 16
1.2.1.4. ባህልና ቱሪዝም ልማት ........ 18
1.2.1.5. ሳይንስና ቴክኖሎጅ ልማት ........ 19
1.2.1.6. ንግድና ገበያ ልማት ........ 20
1.2.1.7. ስራና ስልጠና ........ 23
1.2.1.8. መሬት አስተዳደር ........ 25
1.2.2. የከተማ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም ........ 29
1.2.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም ........ 31
1.2.3.1. ትምህርትና ስልጠና ........ 31
1.2.3.2. ጤና ጥበቃ ........ 33
1.2.3.3. ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ........ 36
1.2.3.4. ወጣቶችና ስፖርት ልማት ........ 39
1.2.4. የመሠረተ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም ........ 41
1.2.4.1. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ........ 41

1.2.4.2. መንገድ ........ 44
1.2.4.3. ውሃና ኢነርጅ ........ 45
1.2.4.4. መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ........ 46
1.2.5. የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ አፈጻፀም ........ 48
1.2.5.1. ሠላምና ፀጥታ ........ 48
1.2.5.2. ፍትህ ........ 52
1.2.5.3. ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ........ 54
1.2.6. የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ አፈጻፀም ........ 56
1.2.7. የኮሚኒኬሽን ዘርፍ አፈጻፀም ........ 57
1.2.8. የፕላንና ልማት አፈጻፀም ........ 59
ክፍል ሁለት፡- የዕቅድ መነሻዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዓላማዎች እና ዋና ዋና ግቦች፤ ........ 61
2.1. የዕቅድ መነሻዎች ........ 61
2.2. የዕቅዱ የትኩረት መስኮች ........ 62
2.3. የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 62
2.4. የዕቅዱ ዓላማዎች ........ 63
2.5. የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ........ 63
2.5.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅድ ........ 63
2.5.2. የሥራ እድል ማስፋት ........ 65
2.5.3. የዋጋ ግሽበት መቀነስ ........ 65
2.5.4. መዋዕለ-ንዋይ ዕቅድ ........ 66
2.5.5. የልማት ፋይናንስ ዕቅድ ........ 66
2.6. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች ዕቅድ ........ 67
2.6.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ........ 67
2.6.1.1. ግብርና ልማት ........ 67
2.6.1.2. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት ........ 70
2.6.1.3. የማዕድን ሀብት ልማት ........ 72
2.6.1.4. ባህልና ቱሪዝም ልማት ........ 73
2.6.1.5. ሳይንስና ቴክኖሎጅ ልማት ........ 74
2.6.1.6. ንግድና ገበያ ልማት ........ 75
2.6.1.7. ስራና ስልጠና ........ 76
2.6.1.8. መሬት አስተዳደር ........ 77
2.6.2. የከተማ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ........ 79

2.6.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ........ 80
2.6.3.1. ትምህርትና ስልጠና ........ 80
2.6.3.2. ጤና ጥበቃ ........ 82
2.6.3.3. ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ........ 86
2.6.3.4. ወጣቶችና ስፖርት ልማት ........ 88
2.6.4. የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ........ 89
2.6.4.1. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ........ 89
2.6.4.2. መንገድ ........ 90
2.6.4.3. ውሃና ኢነርጅ ........ 91
2.6.4.4. መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ........ 92
2.6.5. የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ ዕቅድ ........ 92
2.6.5.1. ሠላምና ፀጥታ ........ 92
2.6.5.2. ፍትህ ........ 95
2.6.5.3. ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ........ 96
2.6.6. የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ ዕቅድ ........ 97
2.6.7. የኮሚኒኬሽን ዘርፍ ዕቅድ ........ 98
2.6.8. የፕላንና ልማት ዕቅድ ........ 99
ክፍል ሦስት፡- የክትትልና ድጋፍ አግባብ ........ 102

# መግቢያ

በክልላችን ብሎም በሀገራችን ድህነትን ቅነሳ ዋነኛው የልማት አጀንዳ ሲሆን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነዚህ እየተመዘገቡ ያሉ ሁለንተናዊ የልማት ውጤቶች በመንግስትና በህዝብ የተቀናጀ ጥረት በመሆኑ ይህንን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በየበጀት ዓመቱ ያሉ መልካም ውጤቶችን ይበልጥ ለማስፋፋትና መሰረት ለማስያዝ እንዲሁም እጥረቶችን በመቅረፍና ወደ ታለመለት ግብ በመድረስ የተያዘውን የእድገትና የብልጽግና ጉዞ ለማረጋገጥ ሰፋፊ ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

የ2017 በጀት ዓመትም የክልሉን ልማት ለማስቀጠል እንዲቻልና በክልሉችን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገትን የሚፈታተኑ አዝማሚያዎችን ለማስወገድ በማስፈጸም አቅም፣ በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ፣ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡ ስለሆነም የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ውጤቶች ላይ በመመስረት የክልሉን ብሎም የሀገሪቷን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የልማት ዕድገት ለማረጋገጥ መላ ህዝቡን በማሳተፍ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኮረና ወረርሽኝ በሽታ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት እንዲሁም በክልሉ በተከሰተው የጸጥታ ችግር መንግስት ሙሉ ትኩረቱን አድርጎ የቆየ በመሆኑ የክልሉ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዕድገት ላይ መሰናክል ፈጥሯል፡፡ ስለሆነም በ2017 በጀት ዓመት ይህን የሚያካክስ ስራ መስራትን ታሳቢ በማድረግ የክልሉን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት በስፋት በማንቀሳቀስ የክልሉን ህዝብ ከድህነት ለማውጣት እንዲቻል ከዚህ በፊት ይታዩ የነበሩትን አደናቃፊ አመለካከቶችና ጎታች አስተሳሰቦች በማስወገድ አበረታች ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል፡፡

በአሁኑ ወቅት ካሉ አበይት ችግሮች ዉስጥ አንዱ የዋጋ ንረት ሲሆን አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክንያት የግንባታ ወጪ በመጨመሩ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ በተከሰተው በሰላም እጦት ምክንያት በገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የፈጠረ በመሆኑ ለልማት የሚውለውን የፋይናንስ አቅም በሚፈለገዉ ልክ እንዳያድግ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የዋጋ ንረትን በመቀነስና ሠላምን በማረጋገጥ ረገድ የተጠናከረ ስራና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል፡፡

የዕቅዱ ልዩ ባህሪ ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ ለቀጣይ ዓመታት የተተነበየውን የዕድገት ግብ መሰረት በማድረግ በ2017 በጀት ዓመት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ያለመ መሆኑ፣ የማክሮ ትንበያው ከዘርፎች የዕድገት ግብ ጋር የተሳሰረ መሆኑና ዓመታዊ የዕድገት ግቦችን ለማሳካት ለዕድገቱ ወሳኝ ድርሻ ያላቸዉን ሴክተሮች በመለየት በመጠን (quantity) እና በእሴት ጭማሪ ምን ያህል አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለባቸዉ በሚያመላክትና ትስስርን በጠበቀ መልኩ የታቀደ መሆኑ ነው፡፡ ዕቅዱ በዋናነት በውጤታማነት ተፈጻሚ እንዲሆን ሁሉም በየደረጃው የሚገኝ የፖሊቲካና የሲቪል ሰርቪስ አመራር አካላት፣ ሰራተኞች፣ ህብረተሰቡና ሌሎች አጋር አካላት በሙሉ የዕቅዱን ዓላማና ግብ በውል በመረዳት ለተፈጻሚነቱ በከፍተኛ ተነሳሽነት በውጤት የሚገለጽ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የክልሉ አጠቃላይ ገፅታ በአጭሩ

የአማራ ክልል በ8º 41’ እስከ 14º 26’ ሰሜን የኬክሮስ እና በ35º 26’ እስከ 40º 25’ ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ክልሉ በምስራቅ የአፋር፣ በምዕራብ ሱዳንና ቤንሻንጉል፣ በሰሜን ትግራይ ክልል እና ኤርትራ እንዲሁም በደቡብ በኦሮሚያ ክልል ይዋሰናል፡፡ ክልሉ በ14 ዞኖችና በ8 ሪጂኦ ፖሊታን ከተሞች 153 ወረዳዎች እና በ77 የከተማ አስተዳደሮች በ4,160 ቀበሌዎች (በገጠር 3,539፡ በከተማ 621) አስተዳደራዊ እርከን ተከፋፈለ ነዉ፡፡

በመኸር በመልማት ላይ የሚገኝ 5.12 ሚሊየን ሄ/ር መሬት ያለ ሲሆን የምግብ፣ የኢንዱስትሪና የኤክስፖርት ሰብሎችን የሚያመርት እና በሀገሪቱ ከሚመረተው አጠቃላይ ምርት እስከ 33 በመቶ ድርሻ ያለውና ከእንስሳት ሃብት አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከአጠቃላዩ የእንስሳት ሃብት 28.6 በመቶ የሚሸፍን ክልል መሆኑን የ(CSA 2010) መረጃ ያሳያል፡፡

ክልሉ በአምስት ዋና ዋና የአየር ንብረቶች የተከፋፈለ ሲሆን 10.01 በመቶ ያህሉ በረሀማ /ደረቅ ቆላ/ 19.75 በመቶ ያህሉ ቆላ፣ 23.01 በመቶ ወይና ደጋ፣ 26.03 በመቶ ደጋማና ቀሪው 21.2 በመቶ ያህሉ ደግሞ ውርጭና ቁር የአየር ንብረት ባለቤት ነዉ፡፡ የክልሉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ27 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ ሲሆን ዝቅተኛው ከ11.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ይወርዳል፡፡ እንዲሁም ዓመታዊ የዝናብ መጠን ዝቅተኛው ከ200 ሚሜ (26.91 በመቶ) በታች ከፍተኛው ደግሞ ከ2,200 ሚ/ሜትር (5.65 በመቶ) በላይ ይመዘገባል፡፡

ክልሉ የትልልቅ ወንዞች ባለቤት በመሆኑ በአጠቃላይ በሶስት ዋና ዋና ተፋሰሶች ተከፍፍሎ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ እነርሱም የዓባይ፤ የተከዜና የአዋሽ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ ከነዚህ ተፋሰሶች መካከል የአባይ ወንዝ ተፋሰስ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ሲሆን የተከዜ ተፋሰስ ደግሞ በሁለተኛነት ደረጃ የሚታይ ነው፡፡ እንደ ጣና፣ አርዲቦና ሎጎ የመሳሰሉ ሀይቆችም በክልሉ ውስጥ የሚገኙና የከርሰ ምድርና የገፀ-ምድር ውሃን ጨምሮ 1.2 ሚሊየን ሄክታር መሬት በመስኖ መልማት የሚችል አቅም ያለው ክልል ነው፡፡ በተጨማሪ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ለማመንጨት፣ የዓሣ ሀብት ልማት ለማስፋፋት እና የትራንስፖርት አግልግሎት ለማካሄድ የሚያስችል ከፍተኛ መጠን ያለዉ የውሀ ሀብት ክምችት ባለቤትም ነዉ፡፡ ይሁን እንጅ እስከ አሁን በጥቅም ላይ የዋለው የውሃ ሃብት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ በማዕድን ሃብትም ቢሆን በጥናት ከታወቁት ወርቅ፣ ኦፓል፣ ብረት፣ የከሰል ድንጋይ

እንዲሁም ለኢንዱስትሪ እና ለኮንስትራክሽን ግብዓትነት ሚዉሉ በርካታ ማእድናት ያሉት ክልል ነዉ፡፡

የክልሉ የህዝብ ብዛት እንደ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት የስነ-ህዝብ ቆጠራ መሰረት በማድረግ የፕላንና ልማት ቢሮ መረጃ (2017 ዓ.ም) የስነ ህዝብ ፕሮጀክሽን እንደሚያሳየዉ 23,878,998 (ወንድ-11,884,006፡ (49.9 በመቶ) ሴት፡- 1,994,992 (50.1 በመቶ) እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከዚህም ዉስጥ በገጠር የሚገኘዉ የህዝብ ቁጥር ብዛት 18,440,002 (ወንድ 9,320,257 ሴት 9,119,745) ሲሆን በከተማ ደግሞ 5,438,996 (ወንድ 2,563,750 ሴት 2,875,246) ነዉ፡፡ ከክልሉ ሕዝብ 56.2 በመቶ የሚሆነው በሥራ ሊሰማራ የሚችል /15-64 ዓመት/ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ብዛት ያለው የሰው ኃይል በአንድ በኩል በአጭር ጊዜ የሥራ እድል መፍጠርን የሚጠይቅ ሲሆን በሌላ በኩል ለክልሉ ዕምቅ ሃብትና ለአገር ውስጥ ገበያ መሠረት የሚሆን ነው፡፡

በመሆኑም የክልሉን ህዘብ ከድህነት ለማዉጣት ሃብቱን በትክክል ለይቶ ጥቅም ላይ ማዋል የሁሉም ተሳትፎና ርብርብ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን ታሳቢ ያደረገ የ2017 በጀት ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ዕቅዱ በዋናነት የ2016 በጀት ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈጻጸም፣ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ መነሻዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ ዓላማዎች፣ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት፣ መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡

# ክፍል አንድ፡- የ2016 በጀት ዓመት የልማትና መልከም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም

## 1.1. የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻፀም

### 1.1.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት አፈጻፀም

በፕላንና ልማት ቢሮ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ መሠረት ክልሉ በ2015 በጀት ዓመት 5.6 በመቶ ክልላዊ ጥቅል ምርት ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ በተጠቀሰው ዓመት በክልሉ የተመዘገበው ዕድገት ከዘርፎች አንጻር ሲታይ የግብርናው ዘርፍ የ3.6 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የ6.1 በመቶ እና የአምራች ኢንዱስትሪው 14.2 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ የ8.5 በመቶ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔው በ10 ዓመት መሪ ዕቅዱ ከተቀመጠው 9.3 በመቶ አማካይ የዕድገት ግብ አንጻር ሲለካ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል የአምራች ዘርፎችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየተደረገ ያለው ጥረት ዉስን እንደሆነ እና በተጨማሪም በኮቪድ በሽታ ወረርሽኝ  በሰሜኑ ጦርነት እንዲሁም የሚያመለክት ነው፡፡

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን በሚመለከት በ2015 በጀት ዓመት የግብርናው ዘርፍ 52.5 በመቶ፣ ኢንዱስትሪው የ15.7 በመቶ እና የአምራች ኢንዱስትሪው 8.6 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ የ33.2 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ይህም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ከክልሉ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ በአንጻሩ ግን የኢንዱስትሪው ድርሻ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ የክልሉ ኢኮኖሚ አሁንም በግብርናው ላይ ጥገኛ እንደሆነ መዋቅራዊ ለዉጥ ሽግግሩ አዝጋሚና በታቀደዉ መሰረት እየሄደ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡

ስለሆነም የኢኮኖሚ ዕድገቱ አመርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ከማድረግ አንጻር ለግብርናው ዘርፍም የሚገባውን ያህል ትኩረት በመስጠት መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጡ አሠራሮችን መከተል፣ በኢንዱስትሪው ዘርፍና በተለይም በአምራች እንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ የሚታዩ ማነቆዎችን በመፍታትና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግና የአገልግሎት ዘርፉም አምራች ዘርፎችን /ግብርናና ኢንዱስትሪ/ መሠረት አድርጎ እንዲያድግ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የአገልግሎት ዘርፉን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፃዉን መሰረት በማድረግ ለእድገቱ ቀጣይነት በሚረዳ መልኩ ትኩረት በመስጠት ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

### 1.1.2. የሥራ አጥነት ሁኔታ

እንደ ክልሉ የስነ-ህዝብ መረጃ በ2016 ዕድሜዉ ከ15-64 የሆነዉ የክልሉ አመራች ሀይል 56.2 በመቶ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ሆኖም ግን በ2014 አጠቃላይ የስራ አጥነት ምጣኔ 20 በመቶ እንደነበር እንዲሁም እድሜያቸዉ ከ15-29 ዓመት ሆናዉ ወጣቶች የስራ አጥነት ምጣኔ 28.3 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህ አሃዝ ከሃገር አቀፉ 26.8 በመቶ የወጣት ስራ አጥነት ምጣኔ በላይ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በከተሞች ያለውን የሥራ አጥነት ሁኔታ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃ እንደሚያመለክተው በክልሉ በ2010 በጀት ዓመት ከነበረበት 19.7 በመቶ በ2014 በጀት ዓመት ወደ 20.0 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የወንዶች የሥራ አጥነት ምጣኔ 10.8 በመቶ ሲሆን የሴቶች ደግሞ 29.5 በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት በከተሞች እድሜያቸዉ ከ15-29 የሆኑ በክልሉ አጠቃላይ የስራ አጥነት ምጣኔ 28.3 በመቶ ሲሆን የወንዶች 17.9 በመቶ እና የሴቶች 35.8 በመቶ መሆኑን ያሳያል፡፡

በክልሉ ያለው የሥራ አጥነት ምጣኔ 28.8 በመቶ ከአገር አቀፉ አማካይ 19.4 በላይ ሲሆን ይህም ምን ያሄል ችግሩ የከፋ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ከጾታ አንጻር ሲታይ ደግሞ የሴቶች የሥራ አጥነት ሁኔታ ከፍተኛ ሲሆን ከዕድሜ አንጻር ሲታይም የወጣቶች የሥራ አጥነት ሁኔታ የበለጠ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ማለት የሴቶች ኢኮኖሚያዉ አሳታፊነት በጣም አነስተኛ እንደሆነ እና በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል የሚጠይቅ ነዉ፡፡ የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎች ይሄንን ነባራዊ ሁኔታ በመገንዘብ ችግሩን ለመፍታት የተጠናከረ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት በከተማና በገጠር 68,175 በ11 ወሩ 64,766 ኢንተርፕራይዞችን በመመስረት 1,232,280 በ11 ወሩ 1,170,666 የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 21,699 ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን በጠቅላላው ወንድ 462,708 ሴት 328,881 ድምር 792,00 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም በ11 ወሩ በኢንተርፕራይዝ 33.5 በመቶ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ 67.61 በመቶ፣ በዓመቱ በኢንተርፕራይዝ 33.5 በመቶ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ 67.61 በመቶ ማከናወን መቻሉን ያመለክታል፡፡

የሥራ አጥነት ችግር መንስዔ በዋናነት ብዙ የሥራ ዕድል ሊፈጥር የሚችል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እየተስፋፋ አለመሄዱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ማክሮ ኢኮኖሚዉ ላይ ተገቢና ጉልህ ስራ በመስራት ተጨማሪ የስራ እድሎች ገበያዉ ላይ እንዲፈጠሩ በማድረግ የስራ አጥነት ቁጥሩን ለመቀነስ የሚረዱ ዋና ዋና ስራዎችን አጠናክሮ መስራት ይጠይቃል፡፡

### 1.1.3. የዋጋ ግሽበት ሁኔታ

የዋጋ ግሽበት በአንድ አሀዝ እንዲወሰን በማድረግ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ይታያል፡፡ ስለሆነም የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ የመንግስትና የብሔራዊ ባንክ ዋና ዓላማ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በማዕከላዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃ መሠረት በሰኔ ወር 2015 በጀት ዓመት የተመዘገበው የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ ክልላዊ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 33.1 ከመቶ ሆኗል፡፡ በሰኔ ወር 2015 በጀት ዓመት ክልላዊ የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የምግብ የዋጋ ግሽበት በ32.2 ከመቶ ሲሆን የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ ክልላዊ ምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበትም በ34.3 ከመቶ ተመዘግቧል፡፡

በተመሳሳይ በ2016 በጀት ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረት 26.6 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህ ማለት የሸቀጦች ዋጋ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የነበረን የሸቀጦች ዋጋ የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል ፡፡ በዚህም ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ 24.3 በመቶ ሲሆን፡ የምግብ ነክ ሸቀጦች ዋጋ ደግሞ 28.1 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት የአማራ ክልል የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ሲታይ 33.1 በመቶ የደረሰ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑት 32.2 በመቶ ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች ደግሞ 34.3 በመቶ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ማለት በክልሉ የተመዘገበዉ የዋጋ ንረት ከሃገራዊዉ አማካይ የዋጋ ንረት ጋር ሲነጻጸር የበለጠ መሆኑን መላክታል፡፡ ስለሆነም ይህንን ታሳቢ ያደረገ ሰፊ ስራ መሰራት እንዳለበት ያመላክታል፡፡

በመሆኑም የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ የአምራች ዘርፎችን ምርታማነት ማሳደግና የምርት ጭማሪን በእጅጉ ከፍ ማድረግ የሚያስችል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ ክልሉ ለአገር አቀፉ የግብርና ምርት ከ1/3ኛ በላይ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ በተለይ የግብርናውን ምርታማነት በማሳደግ የምርት አቅርቦትን መጨመር የሚያስችሉ ስራዎችን አጠናክሮ በመስራት ረገድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሌላውና ቀለል ተደርጎ ሊታይ የማይገባው እንደ መንስዔ የሚታየው ጉዳይ ሠው ሠራሽ ችግር/ምርት በማከማቸትና በመደበቅና ሠው ሰራሽ እጥረት እንዲኖር ማድረግ፣ አላስፈላጊ ዋጋ መጨመር ወዘተ/፣ የግብይት ሥርዓቱ የተሳለጠ አለመሆን ሲሆን ይህን ችግር ከመቅረፍ አንጻር የአሠራር ስርዓት መዘርጋት፣ የቁጥጥር ስራን ማጠናከርና ተጠያቂነትን በማስፈን ጤናማ የግብይት ስርዓት እንዲኖር የማድረግ ስራን አጠናክሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የምርት ግብዓቶችንና ምርቶችን በቀላሉ በማጓጓዝም የአቅርቦት ሰንሰለቱ ጤናማ እንዲሆንና

በአጠቃላይም የተረጋጋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲኖር ካስፈለገ ሰላምና መረጋጋት ወሳኝ ስለሆነ በዚህ ረገድም ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራ ይገባል፡፡

### 1.1.4. የድህነት ሁኔታ

በክልሉ ድህነት ለመቀነስ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ዘርፈ ብዙ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል፡፡ የተገኘው የኢኮኖሚ መሻሻልም ብዙሃኑን ያሳተፈና ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ነዋሪዎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2013 በጀት ዓመት ከነበረበት 773 የአሜሪካ ዶላር በ2014 በጀት ዓመት ወደ 804 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ያለ ሲሆን ይህ መጠን በ2015 በጀት ዓመት ወደ 874 የአሜሪካ ዶላር ማደጉን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የድህነትና የኑሮ ደህንነት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ2003 በጀት ዓመት ከድህነት ወለል በታች የሚኖረውን 30.5 በመቶ የክልሉን ህዝብ የድህነት ምጣኔ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 26.1 በመቶ ብቻ ማውረድ የተቻለ ሲሆን በሌላ በኩል በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ የከተማና የገጠር ህዝቦች የድህነት ምጣኔ እንደ ቅደም ተከተላቸው በ2003 ዓ.ም ከነበረው የ29.2 በመቶ እና የ30.7 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 11.6 በመቶ እና 28.8 በመቶ የቀነሰ መሆኑ በክልሉ ውስጥ የከተማው የድህነት ምጣኔ መሠረታዊ በሚባል መልኩ ዝቅ ያለ መሆኑንና የገጠሩ ድህነት ምጣኔ ግን ብዙ ያልቀነሰ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዓለም ባንክ ጥናት እንደሚያመለክተው በክልሉ ያለው የሀብት ልዩነት (በድሃና በሀብታም መካከል) ከአገር አቀፉም በላይ ከፍተኛ የሆነና ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑም እየሰፋ መምጣቱን ነው፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት ከሚደረግ ጥረት ጎን ለጎን ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ድህነትን በእጅጉ መቀነስ የሚያስችል ስለሆነ በዚህ ረገድ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### 1.1.5. መዋዕለ-ንዋይ አፈጻፀም

የክልሉ አጠቃላይ ኢንቨስትመንት በ2012 በጀት ዓመት ብር 144.17 ቢሊዮን በጊዜው የገበያ ዋጋ የነበረ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ወደ ብር 320.5 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም ባለፉት አራት ተከታታይ አመታት በአማካይ የ24.3 በመቶ ዕድገት ነበረው፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የያዘው ድርሻ ሲታይ በ2012 በጀት ዓመት የ28.1 በመቶ ድርሻ ያስመዘገበ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ 29.6 በመቶ ነው፡፡ የክልሉን ኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ በተሰራው ስራ በ2016 በጀት ዓመት 330.85 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ399,712

ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 2,260 በኢንቨስትመንት ወደ ክልሉ መሳብ በመቻሉ እጅግ የሚያበረታታ ውጤት ነው፡፡

ኢንቨስትመንት (Gross capital formation) ለኢኮኖሚ ዕድገት እንደ መነሻ የሚወሰድና ለአጠቃላይ ክልላዊ ልማት አስቻይ ሁኔታ ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ ስለሆነም የሚፈለገውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የኢንቨስትመንት መጠኑ በእጅጉ ማደግ ይኖርበታል፡፡

## 1.1.6. የልማት ፋይናንስ አፈጻጸም

የመንግስት ፋይናንስን በሚመለከት የክልሉ ጠቅላላ ወጪ በአስር ዓመቱ መነሻ አመት (2012 በጀት ዓመት) ብር 46.58 ቢሊዮን ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት በክልሉ ለልማት ጥቅም ላይ የዋለው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ወደ ብር 67.76 ቢሊዮን አድጓል፡፡ የዕድገት ምጣኔው ተወስዶ ሲታይ የክልሉ ወጭ 39.48 ቢሊዮን ብር ዕድገት አሳይቷል፡፡ ነገር ግን የመደበኛ በጀት ወጪ የ32.23 ቢሊዮን ጭማሪ ሲያሳይ የካፒታል በጀቱ በ7.25 ቢሊዮን ብር ወጪው ጭማሪ  ይታያል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከአጠቃላይ ወጪው የመደበኛ ወጪ ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 78.9 በመቶ በ2015 በጀት ዓመት ወደ 80.13 በመቶ ከፍ ሲል በተቃራኒው የካፒታል ወጪ ድርሻ ግን በተጠቀሱት የበጀት ዓመታት ከነበረበት 21.1 በመቶ ወደ 19.87 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው የክልሉ መንግስት ለመደበኛ ወጭ ከአመት አመት እየጨመረ መሄዱና አብዛኛው በጀት ለመደበኛ ወጪ እየዋለ መሆኑን ያመላክታል ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ከቀጠለ በአጠቃላይ የኢንቨስትመንት ልማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጠር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም በክልሉ በካፒታል በጀት የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ከአጠቃላይ የክልሉ ልማት ፍላጎት ከመመለስ አንፃር ሲታይ ክልሉ ወደኋላ የቀረበት ሁኔታ እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በጥናት ላይ የተመሠረተ የክልሉን ልማት ሊያግዝ የሚያስችል የበጀት ምደባ እንዲኖር መሠራት ይኖርበታል፡፡

የገቢ አሰባሰብን በሚመለከት በ2015 በጀት ዓመት ከመደበኛና ከከተማ አገልግሎት ገቢ በድምሩ ብር 47.97 ቢሊየን ለመሰብሰብ ታቅዶ 41.39 ቢሊየን (የዕቅዱን 86.01 በመቶ) ተሰብስቧል፡፡ ክልሉ የልማት ወጪውን በራሱ ገቢ የመሸፈን አቅሙን በተመለከተ ዝቅተኛ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን መሻሻልም አሳይቷል፡፡ ይኸውም በ2012 በጀት ዓመት 14 በመቶ የነበረው በ2015 በጀት ዓመት ግን ወደ 42.49 በመቶ ደርሷል፡፡

ምንም እንኳን በ2015 በጀት ዓመት ወጪን በራስ ገቢ የመሸፈን አቅም ወደ 42.49 በመቶ ከፍ ያለ ቢሆንም ገቢው ካጠቃላይ የክልሉ ጥቅል ምርት (Tax to GDP ratio) ጋር ሲነጻጸር በ2012 በጀት ዓመት 2.7 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ 3.8 በመቶ ደርሷል፡፡ በመሆኑ የገቢ መሰረቱን ማስፋት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት በመሰብሰብ ረገድ ሠፊ ስራ መሠራት ይኖርበታል፡፡

የፋይናንስ ተቋማትን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር አሁንም ዉስንነት ቢኖርም በባንኮች፣ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት እና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት እየተሰበሰበ ያለው ተቀማጭ የቁጠባ ገንዘብ ከዓመት ዓመት መጨመር አሳይቷል ይሁን እንጅ በክልሉ አብዛኛው ህብረተሰብ የሚገኘው በገጠር በመሆኑና የክልሉ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ በመመስረቱ አሁንም ለዘርፈ የፍይናንስ አቅርቦት ተደራሽነት አነስተኛ ነዉ፡፡

በክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት በክልሉ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የቁጠባ መጠን በጠቅላለ 267.9 ቢሊየን ብር ደርሷል፡፡ ስለሆነም በገጠር የፋይናንስ ተቋማትን የማበራከትና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በማጎልበት የተቀማጭ ቁጠባን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ በዓመቱ በክልሉ የተሠራጨው ብድር 132.6 ቢሊየን ብር ነው፡፡ ከተቆጠበው የተሠራጨው መጠን 49.5 በመቶ ብቻ ሲሆን ይህም አብዛኛውን የክልሉ ተቀማጭ ቁጠባን ወደ ክልሉ ኢንቨስትመንት ከመቀየር አኳያ ዉስንነት ያለበትና የክልሉ ነዋሪ በቆጠበው መጠን ልክ ከብድሩ ተጠቃሚ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ የተቀማጭ ቁጠባው በብድር መልክ እየተሰጠ ያለው እንደ አገር ቢሆንም በክልሉ በብድር የተወሰደው ከተቆጠበው አንፃር ሲታይ እንደ ክልል ቆጣቢ ህብረተሰብ (Net saver) መሆኑን ያሳያል ይህም ማለት ህብረተሰቡ በፈጠረዉ ሀብት ኢንቨስት እያደረገ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡

## 1.2. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች አፈጻፀም

### 1.2.1 የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም

#### 1.2.1.1. ግብርና ልማት

የክልላችን ኢኮኖሚ በአብዛኛው የተመሠረተው በግብርና ላይ ነው፡፡ ይህም ሲባል ከክልሉ ኢኮኖሚ በየዓመቱ በአማካይ 164.9 ቢሊየን ብር በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ በግብርና ሴክተር የሚገኝ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ግብርና በአማካይ 52.5% የሚሆነውን እሴት ጭማሪ ለክልሉ ኢኮኖሚ በማመንጨት ላይ ያለ ሴክተር ነው፡፡ ከግብርና ሴክተር እሴት ጭማሪ

ውስጥ ደግሞ በየዓመቱ በአማካይ 110.98 ቢሊየን ብር ወይም 67% በላይ የሚሆነውን የሚሸፍነው የሰብል ምርት እሴት ጭማሪ ነው፡፡ ከክልሉ አጠቃላይ ኢኮኖሚም ቢሆን የሰብል እሴት ጭማሪ በአማካይ 37.5% ይሸፍናል፡፡ በ2015/16 የምርት ዘመን በግብርና ቢሮ የምርት ትንበያ መሰረት በመደበኛና በኮሞዲቲ የመኸር ሠብሎች የተገኘውን 145,304,384 ኩ/ል ምርት በ2015/16 የምርት ዘመን 5,185,468 ሄ/ር መሬት በማልማትና ምርቱንም በ16.4% በማሣደግ 169,652,386 ኩ/ል ምርት ማምረት፣ ምርታማነቱንም በ2015/16 ምርት ዘመን ከነበረበት 28.2 ኩ/ል/ በሄ/ር ወደ 32.7 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን አፈፃፀምን በተመለከተ የክልሉን አርሶ አደር በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው በአባወራና እማወራ የግብርና የልማት ቡድን አደረጃጀት በማጠናከር ነዉ፡፡ ስለሆነም የክልላችን አርሶ አደር አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችሉ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 6,574,946 አርሶ አደር የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6,461,748 (98) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ለአ/አደሮች ተገቢውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት በሁሉም ግብርና ልማቶች በምክረ ሀሳቡ መሰረት ሙሉ ፓኬጅን ለ2,296,001 አርሶ አደሮች እንዲተገብሩ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ ,409,731 ሴት 310,566 በድምሩ 1,720,297 (75) አርሶ አደሮች ለመፈጸም ተችሏል፡፡

የሰብል ልማት በተመለከተ፡ በ2016/17 በመኸር ወቅት የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ 5,185,468 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 71% ያህሉ መሬት በ1ኛ ዙር የታረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ እስካሁን 2ኛ ዙር 2,428,201 ሄ/ር(66.1%) እንዲሁም 3ኛ ዙር እርሻ 1,173,171 ሄ/ር(31.9) መሬት ማረስ ተችሏል፡፡ በምርት ዘመኑ 897,809 ሄ/ር በትራክተር ለማረስ ታቅዶ እስከ 11 ወሩ ድረስ 542 ትራክተር በመጠቀም 310,226 ሄ/ር (86%) መሬት ማረስ ተችሏል፡፡ በበልግ ወቅት 239,509 ሄ/ር ማሳ በማልማት 4,260,370 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ እስካሁን 250,439.5 ሄ/ር (104.6%) ማሳ በማልማት ምርቱ እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ የዘር ብዜት በተመለከተ፡ በ2015/16 ምርት ዘመን በተለያዩ ሰብሎችና ዝርያዎች እስካሁን ሊሰበስብ ከታቀደው 315,109 ኩ/ል ዘር ውስጥ 190,805 ኩ/ል (60.6%) ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት መሰብሰብ ከተቻለው ዘር 213,704 ኩ/ል ጋር ሲነጻጸር በ22,899 ኩ/ል ማነስ አሳይቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ 102,031,197 ሜ3 መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ 55,374,175 (54%) ሜ3 ተዘጋጅቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ22,543,110 ሜ3 በማነስ ያሳያል፡፡ በ2016/17 ምርት ዘመን ለመኸር ልማት 8,277,642 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ 5,006,714 የቀረበ ሲሆን ከቀረበዉ ውስጥ 4,054,407 ኩ/ል (80.9%) ለአርሶ አደር ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም 312,242 ኩ/ል የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን ለማቅረብ ታቅዶ 115,175 ኩ/ል በማቅረብ 85,457 ኩ/ል ማሰራጨት ተችሏል፡፡

አትክልትና ፍራፍሬ መስኖ ልማትን በሚመለከት፡- በ2016 በጀት ዓመት በመስኖ ልማት 333,416 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 301,469 ሄ/ር (90%) መሬት ታርሶ 299,764 (90%) ሄ/ር በዘር ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን በ1ኛ ዙር መስኖ ልማት 25,723,636 ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 29,705,814 (115.5%) ኩ/ል ምርት ተሰብስቧል፡፡ የመስኖ ስንዴ ልማት ስራችን ስናይ ደግሞ በበጀት አመቱ 250,006 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ እስከ 11ወሩ 151,276 ሄ/ር (60.5%) በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡ በመሆኑም በመስኖ ስንዴ ከለማዉ መሬት ዉስጥ እስከ 11ኛ ወሩ ከ113,712 ሄ/ር መሬት ላይ 4,043,924.75 ኩ/ል ምርት ተሰብስቧል፡፡በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 15,241 ነባር ችግኝ ጣቢያ ለማካሄድና 373 በአዲስ ለማቋቋም ታቅዶ 2,277 (15%) ነባር ችግኝ ጣቢያ ማካሄድና 21 (5.6%) አዲስ ችግኝ ጣቢያ ማቋቋም ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 18,529,841 የቡናና የቆላና የደጋ ፍራፍሬ ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ 15,278,653 (82%) ችግኝ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በጀት ዓመት ጠቅላላ 18.5 ሚሊዮን የቡናና ፍራፍሬ ችግኝ ለተከላ ለማዘጋጀት ታቅዶ 15.2 ሚሊዮን የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ቡና 8.3 ሚሊዮን፤ የቆላ ፍራፍሬ 6.3 ሚሊዮን እና የደጋ ፍራፍሬ 0.57 ሚሊዮን ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም 466,451 ተሳታፊ አርሶ አደሮችን ለመለየት ታቅዶ 129,345 (27.7%) የተከናወነ ሲሆን እንደ ክልል ለተከላ ለተዘጋጀዉ 15.2 ሚሊዮን ችግኝ መትከያ እስከ 11ወሩ 3.5 (22.9%) ሚሊየን ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡

2015/16 ምርት ዘመን 386,356 የአቮካዶ ችግኝ በ1,259 ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ፤ እስከ 11 ወሩ 121,956 (31%) የአቮካዶ ችግኝ በ313ሄ/ር መሬት ላይ በማልማት 2,868 (231 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በምርት ዘመኑ 241,706 የማንጎ ችግኝ በ879 ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል በእቅድ ተይዞ እስከዚህ ሩብ ዓመት 106,316 (43%) የማንጎ ችግኝ በ369ሄ/ር በማልማት 4,273 (414 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ 130,630 የሙዝ ሳከር በ79ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል

ታቅዶ፤ እስከዚህ ሩብ ዓመት 73,845 (58%) የሙዝ ሳከር በ46 ሄ/ር መሬት በማልማት 2,448 (123 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በምርት ዘመኑ 64,700 የአፕል ችግኝ በ56ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ፤ 54,505 (84%) የአፕል ችግኝ በ44ሄ/ር መሬት በማልማት 627 (176 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ 46,080 የብርካን ችግኝ በ138ሄ/ር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ፤እስከዚህ ሩብ ዓመት 46,080 (100%) የብርቱካን ችግኝ በ166 ሄ/ር መሬት በማልማት ,405 (400 ሴቶች) አርሶ አደሮች ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡

የግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ሜካናይዜሽን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ  በአርሶ አደሮች፤ በማህበራት፤ በድርጅቶች እና በግብርና ቢሮ አማካኝነት 151 ትራክተሮችን በማቅረብ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በዚህም የክልሉን የትራክተር ቁጥር ወደ 1,892 ማድረስ ተችሏል፡፡ በክልላችን ከሚታረሰው መሬት ውስጥ 60% የሚሆነው ለመካናይዜሽን ምቹ በመሆኑ 46 የሰብል መውቂያ ኮምባይነር ለማቅረብ ታቅዶ 13 ኮምባይነር በማቅረብ ለማሰራጨት የተቻለ ሲሆን በክልሉ ያለውን የኮምባይነር ቁጥር 54 ለማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 186 ትሬሸር እና 27 የአኩሪ አተር መውቂያ መሳሪያ ለማቅረብና ለማሰራጨት ታቅዶ 81 ትሬሸርና 26 የአኩሪ አተር መውቂያ መሳሪያ  ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 9,863 የውሀ መሳቢያ ሞተር ለማቅረብ ታቅዶ 3,120 በማቅረብ ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል፡፡

ክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሀብት ባለቤት ነው፡፡ በክልላችን ከእንስሳት ሀብቱና ተዋጽዎች የሚገኘው እሴት ጭማሪ ከሰብል ምርት እሴት ጭማሪ ቀጥሎ ከፍተኛ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ከክልሉ ኢኮኖሚ በየዓመቱ በአማካይ ከ40.77 ቢሊየን ብር በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ ከእንስሳት ሀብቱ የሚገኝ ሲሆን በአማካይ ከ14% በላይ የሚሆነው እሴት ጭማሪ በዚህ ዘርፍ ተሸፍኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም ወተት ምርት በበጀት ዓመቱ በበጀት ዓመቱ ወተት ምርት 1,841,733 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 1,903,058 ቶን ወይም የዕቅዱን (100%)ማከናወን ተችሏል፣ በበጀት ዓመቱ የሥጋ ምርት 551,455.3 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 349,930 ቶን ወይም የዕቅዱን (63.4%) ተከናዉኗል፣ የእንቁላል ምርት በበጀት ዓመቱ 764 ሚ/ዮን ለማምረት ታቅዶ 701 ሚ/ዮን በማከናወን የዕቅዱን (92%) ተከናዉኗል ፣የማር ምርት በበጀት ዓመቱ 30,133 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 20715 በማድረስ የዕቅዱን (69%) ተከናዉኗል፣ የአሳ ምርት በበጀት ዓመቱ 37,554 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 29,332 ቶን የዕቅዱን (78%) ተከናዉኗል፣ ቆዳና ሌጦ በበጀት ዓመቱ 9,109,009 ለገቢያ ለማቅረብ ታቅዶ 6,173,242 በማከናወን የዕቅዱን 68% መቅረቡን ያሳያል ፡፡

የኅብረት ስራ ማህበራት ስራዎች አፈጻጸምን ስናይ፡- በበጀት ዓመቱ 2,600 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋም ታቅዶ 1852 (76%) መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋም ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ነባር የኅብረት ስራ ማኅበራት ካፒታላቸውን በብር 923,533,908 ለማሳደግ ታቅዶ በብር 699,829,180 (76%) ማሳደግ የተጫለ ሲሆን የቁጠባ አገልግሎትን ከማሳደግ አንጻር በበጀት ዓመቱ ብር 1,870,372,191 በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት መደበኛ ቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ 1,456,048,581 (78%) መደበኛ ቁጠባ ማሰባሰበ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የብድር ስርጭት አግልግሎትን ለማሳደግ ብር 9,339,186,228 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት ለአባሎቻቸው ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 5,,342,,170,,392 (58%) የገንዘብ ቁ/ብ/ኅ/ስ/ማ/ ለአባሎቻቸው ብድር መሰራጨቱን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ለ6,624 መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት የሂ/ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 1897 (28.6%) ማከናዎን ተችሏል፡፡ ለዩኒዬኖች የኦዲት አገልግሎት መስጠት፡- በበጀት ዓመቱ ለ76 የኅ/ስራ ማህበራት ዩኒየኖችን የሂ/ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ45 (59%) ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ጉድለትን ስናይ የኦዲት አገልግሎት ካገኙት 1,897 መሠረታዊ የኅ/ስራ ማህበራት ውስጥ በ281 (14.8%) ብር 25,692,072 ጉድለት ተከስቷል፡፡ እንዲሁም የኦዲት አገልግሎት ካገኙት 45 የኅ/ስራ ማህበራት ዩኒዬኖች ውስጥ በ9 ዩኒየኖች ላይ ብር 26,365,766 ጉድለት ተከስቷል፡፡ በአጠቃላይ በመሠረታዊ ኅ/ስ/ማህበራት እና በዩኒየኖች ብር 52,057,838 ጉድለት የተከሠተ ሲሆን በጉድለት ከተከሰተው ዉስጥ በድርድር ብር 14,981,538 እና በፍርድ ቤት ዉሳኔ ብር 7,226,279 በድምሩ ብር 22,207,817 ማስለመስ ተችሏል፡፡

በግብርና ምርምር ዘርፍ 628 ሙከራዎችን ለመስራት ታቅዶ 526 (84%) የተከናወነ ሲሆን በሰብል 257፣ በእንስሳት 141፣ በአፈርና ዉሃ ምርምር 61፣ በደን 44፣ ማህ/ም/ሃ/ግ/ኤ 17፣ በምግብ ሳይንስ 10 እና በዘር 7 የምርምር ሙከራዎች ተከናዉነዋል፡፡

የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ስራዎች አፈጻጸምን በሚመለከት፡ የ2015/16 የምርት ዘመንን ተከትሎ በተፈጠረው የዝናብ መቆራረጥ ምክንያት በክልላችን የተወሰኑ አካባቢዎች ድርቅ ተከስቷል፡፡ የመልሶ ማቋቋም ስራውን በተደራጀ መንገድ ጊዜ ተገኝቶ ሳይሰራ ከተፈናቃይ ላይ የድርቅ መከሰት እና የኑሮ ውድነት ተደራርቦ ችግሩን ውስብስብ አድርጎታል፡፡ የገጠመውን የድርቅ ችግር ምላሽ ለመስጠት ወደ ቦታው የባለሙያ ቡድን በመላክ የጥናት ስራ የተሰራ ሲሆን እስካሁን ባለው ሁኔታ የድርቁን ስፋትና የችግሩን መጠን ስንመለከት 9 ዞኖች፣ 43 ወረዳዎች፣ 429 ቀበሌዎች ላይ ተጋላጭነቱ ያለ ሲሆን

ከሰ/ጎንደር 3 ወረዳዎች እና ከዋግኽምራ 3 ወረዳዎች ውጭ ያሉት በከፊል የችግሩ ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ በዚህ የተነሳ 1,846,895 ሰዎች የዕለት ምግብ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ታሳቢ ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በሌላ በኩል 621,797 (68,630 በመጠለያ ውስጥ) ያሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 260,197 ተፈናቃዮች ከኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ ዞኖች የመጡ በመሆናቸው ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ የማወያየት ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ዙር ወደ ቦታቸው ለመሄድ ከወሰኑት 51,782 ቤተሰብ ውስጥ 5,589(10.7%) ወደ ቦታቸው ተመልሰዋል፡፡

የዕለት ምግብ ምላሾችን በተመለከተ፤ ከክልሉ መንግስት ለመጠባበቂያ ከተያዘው ውስጥ 38,076 ኩ/ል የምግብ እህል ለ751,289 ተጠቃሚዎች ተመድቦ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከክልሉ መንግስት ካዝና 430 ሚሊዮን ብር የተፈቀደ ሲሆን በ300 ሚሊዮን ብር የምግብ እህል ግዥ ተፈፅሞ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትና ያልተጠቀሱ በርካታ ጥረቶች በመደረጋቸው የአደጋውን መጠን መቀነስ የተቻለ ቢሆንም በቀጣይ በግጭት ምክንያት ወደቀያቸው ያልተመለሱትንና በድርቁ ምክንያት ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልጉትን ወገኖች በመከታተል ዘላቂ መፍትሄ ሊበጅላቸው እንደሚገባን አውቀን መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡

### 1.2.1.2. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት

የክልላችንን ኢንዱስትሪ ለክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ የ44.92 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ ወይም ደግሞ የ15% ድርሻ አለው፡፡ በክልላችን አምራች ኢንዱስትሪው ከኮንስትራክሽን ዘርፉ ቀጥሎ ለኢንዱስትሪው እሴት ጭማሪ ማደግ አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡ ዘርፉ በአማካይ ከ18.92 ቢሊየን ብር በላይ እሴት ጭማሪ ለኢንዱስትሪው በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው በአማካይ የ6.2 በመቶ ድርሻ ያለው ይህ ዘርፍ ከኢንዱስትሪው እሴት ጭማሪ ደግሞ በአማካይ የ42 በመቶ ድርሻ ያለው መሆኑን አመታዊ የጥቅል ምርት ግመታ መረጃ ያመለክታል፡፡

ስለሆነም በበጀት ዓመቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አጠቃላይ ምርታማነት በ2015 በጀት አመት መጨረሻ ከተወሰደዉ ግምገማ አንጻር 56.04% ብቻ ስለሆነ የኢትዬድያ ታምርት ንቅናቄን በማጠናከር የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነት በዚህ አመት መጨረሻ ወደ 73% ማሳደግ የሚጠበቅ ቢሆንም የተለኩት ኢንዱስትሪዎች ከ50% በታች በመሆናቸዉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አጠቃላይ ምርታማነት ማወቅ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በአምስት የኢንዱስትሪ ክላስተሮች እና በ22 የኢንዱስትሪ መንደሮች ላይ ወደ ምርት

ያልገቡ ፋብሪካዎችን ፈጥኖ ወደ ምርት ማስገባት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡ በሌላ በኩል የክልሉን ኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳደግ በተሰራው ስራ 11 ውስጥ 330.85 ቢሊየን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ እና ወደ ስራ ሲገቡ ለ399,712 ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 2,260 ባለሃብቶች ወደ ክልሉ መሳብ መቻሉ እጅግ የሚያኮራ ተግባር ነው፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከሚገኑ ምርቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግን በተመለከተ በ11 ወር ከ37 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች 68799 ቶን በመላክ 110 ሚሊ.ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ አነስተኛ1፣መካከለኛ 8፣ከፍተኛ 24 በድምሩ 33 አምራች ኢንዱስትሪዎች 127488.979 ቶን በመላክ 116.11 ሚሊየን እንዲሁም ከሆርቲካልቸር 2,388.76 ቶን በመላክ 13.15 ሚሊየን በድምሩ 129.26 ሚሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ በኢንዱስትሪ ቁጥር 89% እና በገቢ 100 % መፈጸም ተችሏል ፡፡ በተመሳሳይ ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻን ከማሳደግ አንፃር በ11 ወሩ 467 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ 61 አይነት ተኪ ምርቶች በማምረት በ191,152 ቶን ምርት 262 ሚሊዮን ዶላር ውጭ ምንዛሬን ማስቀረት/መተካት በሚል በእቅድ ተይዞ 264 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየትና በመደገፍ 65 አይነት ምርቶች እንዲመርቱ በማድረግ 338519.181 ቶን ላይ 681.885 ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬን መተካት/ማስቀረት ተችሏል፡፡አፈጻጸም በተኪ ምርት መጠን 100% እና በገቢ 100% ነው፡፡ይህ ውጤት ከወቅቱ አንፃር ደህና ቢመስልም ከግብ አንፃር ከለካነው በርካታ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡

### 1.2.1.3. የማዕድን ሀብት ልማት

የማዕድን ስራን በተመለከተ የሰባት ወረዳዎች ነባር የሥነ ምድር ካርታ ስራ ጥናት ሠነድ 10,658.42 ካ.ኪ.ሜ (በአዊ ዞን በጓንጓ ወረዳ በ1,108 ካሬ ኪ.ሜ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን በአንኮበር ወረዳ በ693 ካሬ ኪ.ሜ፣ በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ በ906 ካሬ ኪ.ሜ፣ በዋግ ኽምራ ዞን በሰቆጣ ወረዳ በ1766 ካሬ ኪ.ሜ፣ በሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ ወረዳ በ1950 ካሬ ኪ.ሜ፣ በመስራቅ ጎጃም ዞን በደጀን ወረዳ 621 ካሬ ኪ.ሜ እና በደቡብ ጎንደር ዞን በስማዳ ወረዳ 2257.42 ካሬ ኪ.ሜ) የስነምድር ካርታ ስራ ጥናት ለመስራት ታቅዶ የስነ-ምድር ጥናቱ 100% ተጠናቀቆ ርክክብ በመፈጸም የስነ-ምድር ካርታ ጥናት በበጀት ዓመቱ 936.58 ካ.ኪ.ሜትር በማጥናት ሽፋኑን 21.12% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ጠቅላላ

የስነ-ምድር ጥናት ሽፋን 31,867.98 ካ.ኪ.ሜትር ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማዕድን ኢንቨስትመንትን የሚያሣድጉ የኢኮኖሚ ቀጠናዎችን ልየታ ሽፋንን 10,000 ካ.ኪ.ሜ ለማሳደግ ታቅዶ 4000 ካ.ኪ.ሜ በመፈፀም በካርታ ላይ የማመላከት ስራ በመስራት 80% መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከማዕድን ኢንቨስትመንት አኳያ የማዕድን ነክ ፋብሪካዎችን እንዲቋቋሙ በበጀት በ11 ወሩ 87 የኮንስትራክሽን ማዕድናት የምርመራ እና የምርት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዶ 74 ፈቃዶችን በመስጠት ከ11 ወሩ ደግሞ 85% ማከናወን ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለ2,597 ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃዶች ለመስጠት ታቅዶ 900 ማከናወን የተቻለ 34.65% እንዲሁም ለ102 አነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 122 መፈፀም የተቻለ ሲሆን አፈጻፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማዕድን ዘርፉ ከሚሰማሩ ባለሃብቶች፣ ኩባንያዎች እና ኢንተርፕራይዞች ለ33,857 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዞ ለ22,515 (66.5%) (ው- 15,174 ሴ- 7,341) ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን 12,253 (ወንድ 7,658 ሴት 4595) የሚሆኑት ወጣቶች ሲሆን የተፈጠረውም የስራ ዕድል በከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፣ በአነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፣ በማዕድን ምርመራ ሥራ ፈቃድ፣ በአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፣ በወርቅ አቅራቢነት፣ በነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ማደያ እና በከበሩ ማዕድናት ዕደ-ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ 15,691 ኪ.ግ ጥሬ ኦፓል ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከጥሬ ኦፓል 5,225,000 USD የውጭ ምንዛሬ ለማገኘት ታቅዶ 20,321 ኪ.ግ ወደ ውጭ በመላክ 1,237,824 USD ማገኘት የተቻለ ሲሆን የምንዛሬ አፈጻፀም 27.3% የምርት አፈጻፀም ደግሞ ከ100% በላይ ነው፡፡ 952 ኪ.ግ እሴት የተጨመረበት ኦፓል ለውጭ ገበያ በማቅረብ 1,375,000 USD የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ታቅዶ 361 ኪ.ግ ወደ ውጭ በመላክ 651,217 USD ማግኘት የተቻለሲሆን የምርት አፈጻፀም 38% የምንዛሬ አፈጻፀም ደግሞ 47.4% ነው፡፡ ሌላው 110 ኪ.ግ ወርቅ ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ 4,243,204 USD የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ዕቅድ ታቅዶ ከወልቃይት ሴቲት ሁመራ ዞነና ከሰሜን ጎንደር 8.331 ኪ.ግ ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ 608,854 USD ማግኘት ተቻለ ሲሆን የምንዛሬ አፈጻፀም 11.3% የምርት አፈጻፀም ደግሞ 7.6% ነው፡፡ ከሮያሊቲ፣ ከመሬት ኪራይ፣ ከፈቃድ አገልግሎት እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ክፍያዎች ብር 55,401,176 ለመሰብሰብ ታቅዶ 43,284,570 (ከሮያሊቲ 18,018,898፣ ከቁርጥ ዋጋ 12,581,959፣ ከመሬት ኪራይና

ከሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች 12,683,713) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 78% ነው፡፡ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ2.78 በመቶ በቅናሽ የሚያሳይ ስለሆነ ይህን አፈጻጸም በማስፋት የማስቀጠልና የተሻለ ገቢ የመሰብሰብ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ በሚመረቱ የማዕድን ውጤቶች የመተካት አቅምን 281,250 ቶን ምርት በሀገር ምርቶች በመተካት 59,269,501 USD ለማዳን ታቅዶ 29,197,785 USD የውጭ ምንዛሬ ማዳን(49.48%) የተቻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

የማዕድን ነክ ፋብሪካዎችን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በኩል በበጀት ዓመቱ 7 ከፍተኛ የማዕድን ነክ ፋብሪካዎችን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 6 እያመረቱ የሚገኙ ፋብሪካዎች ምርታቸውን እንዲያሳድጉ እና እየተገነቡ ያሉትን የግንባታ ፍጥነታቸውን እንዲጨም\ የድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክልላችን ፍቃድ በመሥጠት እያስገነባቸው ካሉት 5 የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መካከል ትልቁና ግዙፉ የለሚ ናሽናል ሲምንቶ ፋብሪካ 95% በመድረስ ለምረቃ የቀረው መሆኑን ያሳያል፡፡

#### 1.2.1.4. ባህልና ቱሪዝም ልማት

ከባህል ስራዎቻችን አንጻር በበጀት ዓመቱ በ295 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ በማካሄድ ለ32 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ እንዲሰራ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ162 ቅርሶች ላይ የጉዳት ልየታ ስራ የተሰራ ሲሆን ለ87 ቋሚ ቅርሶች  የጥገናና ክትትል ስራ በመስራት አፈጻጸሙን ከተያዘው የጉዳት ልየታ አንጻር 54.9 በመቶ ከቅርስ ጥገና አንጻር ከዕቅድ በላይ ለማከናወን  የተቻለ ሲሆን ለ956 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ994 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ተሰርቷል፡፡ በ6 ጥንታዊ የስዕል ቅርስ የጥገና ስራ ለማከናወን ታቅዶ 2 (33.34) ቅርሶችን ጥገና ስራ እተከናወነ ሲሆን ለ295 ቋሚና ለ11,807 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንክብካቤ እና የጽዳት እንዲሁም የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ለመስራት ታቅዶ ለ555 ቋሚ እና ለ15,449 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጽዳት እና የእንክብካቤ ሲሰራ ለ425 (>100 %) ቋሚ እና 8811 (74.6%) ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ተሠርቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ 316 ለሚሆኑ ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኙ እና የወሰን  ክለላ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ 85 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እና 60 ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ ስራ ተሰርቷላቸዋል፡፡ በዚህም አፈጻጸሙ ከዕቅዱ አንጻር በይዞታ ማረጋገጫ

26.9 በመቶ እንዲሁም ከወሰን ክለላ አንጻር 19 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ በተለያየ ጊዜያት በህገ-ወጥ የቅርስ ዝዉዉር እና ስርቆት ከቅርስ ተቋማት የተዘረፉ 239 ቅርሶችን ለማስመለስ ታቅዶ 140 (58.6 በመቶ) ቅርሶችን (ከዚህ ውስጥ ሁለት ትልልቅ የእጅ መስቀሎችና አንድ መካከለኛ የእጅ መስቀል) ከኤርፖርት በጉምሩክ ባህርዳር ቅርንጫፍ አማካኝነት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 33 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 33 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ለመመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙን ከዕቅዱ አንጻር 100 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 81 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችና 10 ቋሚ ቅርሶችን በአዲስ ምዝገባ ተካሂዷል፡፡

የክልላችን የቱሪስት ፍሰትን በተመለከተ፤ በበጀት ዓመቱ ክልሉን የሚጎበኙ የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን 8,150,016 ለማድረስ ታቅዶ 6,283,802 በማድረስ አፈጻጸሙ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር 77 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰትን 93,366 ለማድረስ ታቅዶ 17,305 ማድረስ በመቻሉ አፈጻጸሙ ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 18.53 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ጠቅላላ የቱሪስት ፍሰትን 8,243,382 ለማድረስ ታቅዶ 6,301,107 ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 76 በመቶ ደርሷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 4,099,900,000 ብር ገቢ ለማግኘት በዕቅድ ተይዞ 2,378,872,489 ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙ ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 58.27 በመቶ ማድረስ እንደተቻለ የሚሳይ ሲሆን ክልሉን ከሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች 190,884,000 ብር ገቢ ለማግኘት በዕቅድ ተይዞ 70,137,061 ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙ ከዓመቱ እቅድ አንጻር 34.65 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዚህም ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች 4,273,327,400 ብር ገቢ ለማግኘት በዕቅድ ተይዞ 2,445,009,550 ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙ ከበጀት ኣመቱ ዕቅድ አንጻር 57.22 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

### 1.2.1.5. ሳይንስና ቴክኖሎጅ ልማት

የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ሽፋንን ከማሳደግ አንጻር የአብክመ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ኮሚሽን ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ማፈላለግ፣ መምረጥ፣ ማስገባት፣ ማላመድ፣ መፍጠርና መጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂ በማልማትና በማሸጋገር የክልሉን ዕድገት ለማረጋገጥ ተልዕኮ ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 11 ወራት ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ለ81,500 የማህበረሰብ ክፍሎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ22,317 (27.38%) ያህል ስልጠና መስጠት የተቻለ ሲሆን ለ2,000 ባለሙያዎች አድቫንስድ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,320 (66%) ወጣት ባለሙያዎች

የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ለ6,500 ወጣቶች በኢንተርንሽፕና የትብብር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 2,985 ወጣቶች የስራ ላይ ስልጠና በመስጠት 45.9% መፈጸም ተችሏል፡፡ በሀገር በቀል ዕውቀቶችን ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ 20 የሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለመምረጥ ታቅዶ 10 (50%) የሀገር በቀል ዕውቀቶችን መምረጥ ተችሏል፡፡ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለ10 ወረዳዎች አዲስ የወረዳኔት መስመር ለማስገባት ታቅዶ ለምዕራብ ጎንደር ዞን ብቻ ማስገባት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 10% ብቻ ነው፡፡

በሌሎች ተቋማት 10 አፕልኬሽኖችን ለማልማት ታቅዶ የወሳኝ ኩነት ሲስተም፣ በደቡብ ወሎ ዞን HRM ሲስተም እና ሌጀር ኦቶሚሽን ተለምቶ ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 30% ነው፡፡ የተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን 4 ሲስተም ለማልማት ታቅዶ ዌብ ቤዝድ ሪፖርቲንግ ሲስተም የዶክመንቴሽንና የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ተሰርቶ የማልማት ስራው የተጠናቀቀ ሲሆን የሙከራ ስራው በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ 15 ድረገጽ ለማልማት ታቅዶ ለተለያዩ ተቋማት 10 (66.7%) ድረገጽ ማልማት ተችሏል፡፡ በዳታ ማዕከል 15 ዌብ ሳይት ሆስት ለማድረግ ታቅዶ 2 (13%) ዌብ ሳይት ሆስት ማድረግ እንዲሁም በዳታ ማዕከል 11 አፕልኬሽኖችን ሆስት ለማድረግ ታቅዶ 2 ሲስተም ሆስት በማድረግ 18.18% መፈጸም ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 22,000 የህብረተሰብ ክፍሎች በቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 2702 (12.28%) ህብረተሰብ ክፍሎች በቪዲዮ ኮንፈረንስ ቴክኖሎጅ እና ዙም ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የቪዲዮ ኮንፈረንስ ቴክኖሎጅን በመጠቀምና ኦንላይን አገልግሎት በመስጠት 3,187,428 (7.96%) ብር ከመንግስት ሊወጣ የነበረን ወጭን ማዳን ተችሏል፡፡

### 1.2.1.6. ንግድና ገበያ ልማት

የንግድ፣ሆቴልና ሪስቶራንት ንዑስ ዘርፍ ከአገልግሎት ሴክተር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ንዑስ ዘርፍ ሲሆን በአማካይ 33.8% የሚሆነውን የአገልግሎት ዘርፍ እሴት ጭማሪ እንዲሁም በአማካይ ከ10% በላይ የሚሆነውን የክልሉን ኢኮኖሚ በየዓመቱ ይሸፍናል፡፡ ስለሆነም በበጀት አመቱ በቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት በማሳደግ የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድ መስጠትና እድሳት አገልግሎቶችን 100% በኦንላይን በማካሄድ የንግድ ፈቃድ ቁጥሩን ወደ 544,903 ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ 97,295 በ11 ወሩ ለ89,186 የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 24,751 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከዓመቱ 25.44% እንዲሁም ከ11

ወሩ 27.7% ቢሆንም ክንውኑ ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት 89,881 ጋር ሲነጻጸር 65,130 (72.3%) በማነስ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 116,535 በ11 ወሩ 106,823 የንግድ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ39,501 ከዓመቱ 34% እና ከ11 ወሩ 37% መፈጸም ሲቻል አፈጻጸሙ ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት 115,094 ጋር ሲነጻጸር 75,593 (65%) በማነስ ያሳያል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ለ428,763 የንግድ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 201,085 (47%) የንግድ ስራ ፈቃድ ማደስ ተችሏል፡፡ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት 355,054 ጋር ሲነጻጸር 153,969 (43%) በማነስ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በ11 ወሩ 293,952 የንግድና ምዝገባ አገልግሎት በኦንላይን መስጠት የተቻለ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የንግድ ፈቃድ እድሳት ሰኔ 30 የሚጠናቀቅ ቢሆንም የኢፌዲሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ክልሉ ያጋጠመውን ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የንግድ ፈቃድ ያላደሱ ነጋዴዎች ተግባራቸውን እያከናወኑ ጎን ለጎን እስከ 2017 በጀት ዓመት ድረስ ማደስ እንደሚችሉ አቅጣጫ ያስቀመጠ በመሆኑ ነጋዴውም ይህን ዕድል ተጠቅሞ ዕድሳቱን ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ከሰብል ገበያ ትስስር ጋር በተገናኘ በሀገር ውስጥ ገበያ የሰብል ምርት ትስስር ለመፍጠር በድህረ እና በቅድመ የሰብል ምርት ትስስር በዓመቱ 4,228,486 እና በ11 ወሩ 3,870,591 ኩ/ል ለማስተሳሰር ታቅዶ 2,719,509 (70%) ከአመቱ 64% ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት 4,417,055 ጋር ሲነጻጸር 1,697,546 (38%) በማነስ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኔኖች ከራሳቸው አቅም 420 ሚሊዮን በተጨማሪ ያለባቸውን የካፒታል ችግር ለመፍታት ከ18 ዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች የተዘዋዋሪ ብድር 678 ሚሊዮን በድምሩ 1.1 ቢሊየን ብር ተዘዋዋሪ ብድር በመመደብ በድግግሞሽ ለምርት ግዥ ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ 508,420 ኩ/ል የግብርና ምርት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርት በፈሳሽ 5.1 ሚሊዮን ሊትር እና በጠጣር 157,000 ኩ/ል ለመንግስት ሰራተኞችና ለከተማ ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ጥረት ተደርጓል፡፡፡

ወደ ውጭ የሚላኩ አስገዳጅ ምርቶች የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን (ሰሊጥ፣ ቦሎቄ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር እና ቡና) ከፍ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት በመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ማዕከል ግዥ ተፈጽሞ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ማዘጋጃ መጋዘን በበጀት ዓመቱ 5,864,841 ኩ/ል በ11 ወሩ 5,049,817 ኩ/ል በመሸኛ ለመላክ ታቅዶ በ11 ወሩ 3,657,195 ኩ/ል (72.4%) እንዲሁም ከዓመቱ (62.4%) ምርት ማቅረብ ሲቻል ከባለፈዉ ተመሳሳይ ወቅት 3,765,193 ጋር ሲነጻጸር 107,998 (2.8%) በማነስ ያሳያል፡፡ አፈፃፀሙ

በዝርዝር ሲታይ ሰሊጥ በምርት ዘመኑ በዓመቱ 2,000,000 ኩ/ል ለመላክ ታቅዶ 1,514,608 ኩ/ል (75.7%) ምርት የተሸኘ ሲሆን ከጥራጥሬ ሰብሎች ነጭ ቦሎቄ 473,564 ኩ/ል ታቅዶ 142,831 (30%)፣ቀይ ቦሎቄ 162,869 ኩ/ል ታቅዶ 46,703 (29%)፣ቡላ ቦሎቄ 93,531 ኩ/ል ታቅዶ 156,088 (167%)፣ ጥቁር ቦሎቄ 3,019 ኩ/ል ታቅዶ 817 ኩ/ል (27%)፣ማሾ 454,471 ኩ/ል ታቅዶ 507,801 (112%) እና አኩሪ አተር 2,071,068 ኩ/ል ታቅዶ 1,288,347 (62%) በመሸኛ መላክ ተችሏል፡፡ ጠቅላላ ከተላከው የአስገዳጅ የሰብል ምርት በዓመቱ 515 ፣በ11 ወሩ 473 ሚ/ዶላር ይገኛል ተብሎ ታቅዶ ከሰሊጥ 288.33 ሚ/ዶላር፣ከጥራጥሬ ሰብሎች 179.14 ሚ/ዶላር በድምሩ 467.47 ሚ/ዶላር ከዓመቱ (90%)፣ከ11 ወሩ (98.8%) የዉጭ ምንዛሬ ለማግኘት ተችሏል፡፡

የኢንዱስትሪ ሰብሎች ወደ ውጭ ገቢያ መላክን ስንመለከት ደግሞ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ዉጪ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ አግሮፕሮሰሲንግ (ፕሮቲን ፓውደር፣ ሽቶ፣ ጣሂናን) በዓመቱ 20,000 ቶን በ11 ወሩ 18,667 ቶን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 25,383.9 ከዓመቱ (>100%) ከ11 ወሩ (>100%)ቶን ማቅረብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የኬሚካል ውጤቶች (ጠርሙስ) በዓመቱ በቁጥር 7,000,000 በ11 ወሩ 6,533,333 ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 4,200,000 ከዓመቱ 60% ከ11 ወሩ 64.28% ማቅረብ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ጨርቃጨርቅና አልባሳት በዓመቱ 5,000,000 በ11 ወሩ 4,666,667 ኪ.ግ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ በ11 ወሩ 3,718,828 ማቅረብ ሲቻል አፈፃፀሙም ከ11 ወሩ 79.69% ከዓመቱ 74.4% ሲሆን የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ በበጀት ዓመቱ 38 ሚ/ዶላር፤ በ11 ወሩ 34.6 ለማግኘት ታቅዶ 31,928,434 ሚ/ዶ (92.28%) ከዓመቱ ደግሞ 84% ነው፡፡

የእንሰሳት እና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት ትስስር በበጀት አመቱ 1,639,586 በ11 ወሩ 1,501,188 የቁም እንስሳት ወደ ቀጣዩ መዳረሻቸው በመሸኛ እንዲጓጓዙ ለማድረግ ታቅዶ 812,526 (54.13%)ከ11 ወሩ(>300%) የተከናወነ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 1,400,041 ጋር ሲነጻጸር 587,515 (41.9%) በማነስ ያሳያል፡፡ 3,887,799 ቆዳና ሌጦ ምርት ከፋብሪካዎች ጋር ለማስተሳሰር እና የዓሳ ምርት 2,591 ቶን ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ቆዳና ሌጦ 2,590,409 (66.8%) እና የዓሳ ምርት 1,925.95 (74.33%) በቅደም ተከተላቸው መሰረት ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 3,546,523 ጋር ሲነጻጸር ቆዳና ሌጦ 956,114 (26.9%) እና አሳ በ542 (21.9%) ቶን በማነስ ያሳያል፡፡ 166,378 ቶን የወተት ምርት ግብይት እና 527 ቶን የስጋ ግብይትን ለማስተሳሰር ታቅዶ 119,109.6 (71.59%) ወተትና 691.1 (>100%) ስጋ ማከናወን ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የእንቁላል ምርት በበጀት ዓመቱ 27,425,205 ለማስተሳሰር ታቅዶ 21,366,291 (77.9%) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ የዶሮ ምርት ግብይት 2,755,366 ለማስተሳሰር ታቅዶ 2,560,057 (92.91%)፣የማር ምርት ግብይት 17,093 ለማስተሳሰር ታቅዶ 7,391.03 (43.24%)፣ የተቀነባበረ መኖ ምርት ግብይት 1,182 ቶን ለማስተሳሰር ታቅዶ 1,293.58 (87.58%) ለማስተሳሰር ተችሏል፡፡

ከቁም እንሰሳት ኤክስፖርት አንፃር በ11 ወሩ ዳልጋ ከብት በቁጥር 1,114 ኤክስፖርት በማድረግ 668,678 ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 93 (8.4%) የዳልጋ ከብት በመላክ 55,800 ዶላር (8.4%) ማግኘት ተችሏል፡፡ አሳ 23.05 ቶን ለመላክ ታቅዶ 31.36 ቶን 136.05% መፈጸም ተችሏል፡፡ በግና ፍየል 21,519 ለመላክ ታቅዶ 25,990 (120%) በመላክ 1,506,330 ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 1,819,300 (120%) ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከቁም እንሰሳት እና አሳ ኤክስፖርት የሚጠበቅ የውጭ ምንዛሬ በ11 ወሩ 2,182,764.75 ዶላር ታቅዶ 1,881,372 (86.19%) ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡

### 1.2.1.7. ስራና ስልጠና

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር 68,175 በ11 ወሩ 64,766 ኢንተርፕራይዞችን በመመስረት 1,232,280 በ11 ወሩ 1,170,666 (ቋሚ 936,533 ጊዜያዊ 234,133) የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 21,699 ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙ ሲሆን ቋሚ ወንድ 304,290 ሴት 248,104 ድምር 552,394 ፣ ጊዜያዊ ወንድ 158,418 ሴት 80,777 ድምር 239,195 በጠቅላላው ወንድ 462,708 ሴት 328,881 ድምር 791,589 የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በ11 ወሩ በኢንተርፕራይዝ 33.5%፣ በስራ ዕድል 67.61%፣በዓመቱ በኢንተርፕራይዝ 33.5%፣ በስራ ዕድል 67.61% ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 384,139 (58.98%) ቋሚ እንዲሁም 5,062(>100%) ደግሞ ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን አፈጻጸሙን ስናይ ከግቡ መድረስ ካለመቻሉም በላይ >80% የሚሆኑትን የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች ቋሚ እንዲሆኑ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አንጻር ክፍተቶች ያሉበትና በርካታ ዜጎች በጊዜያዊ ስራዎች የተሰማሩ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ስለዚህ የሚፈጠሩ የስራ መስኮች በተቻለ መጠን ቋሚ እንዲሆኑ አልሞ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ከማድረግ አኳያ በአገር ውስጥ የስራ ስምሪት ዜጎችን ባልተወሰነ ጊዜና በተወሰነ ጊዜ (ስራ) በተለያዩ የስራ ዘርፎች የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የበጀት ዓመቱ ዕቅድ

30,404 እስከ በ11 ወሩ ድረስ ደግሞ 28,883 ሲሆን ክንውን ወንድ 7,164 ሴት 10,546ድምር 17,710 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከበጀት ዓመቱ 58.2% እንዲሁም ከ11 ወሩ ደግሞ 61.3% መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ለ50,000፣ በ11 ወሩ ለ39,517 ዜጎች በተደረገላቸው ድጋፍ አማካኝነት መብትና ደህንነታቸው ተጠብቆ በኤጀንሲዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሥራ ፈላጊዎች የታቀደ ሲሆን ክንውኑም ወንድ 1,278 ሴት 62,283 ድምር 63,561 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከዓመቱም ከ11 ወሩም ከ100% በላይ ነው፡፡

ውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ሥራዎች በሚመለከት የቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጠና ተቋማትን የቅበላ አቅም እንዲያድግ ማድረግ፣ በመንግስትና በግል ኮሌጆች በመደበኛው ስልጠና ነባር 69,202፣ አዲስ ቅበላ 136,098 ሰልጣኞችን በጠቅላላው 205,300 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን ታቅዶ በመንግስት ኮሌጆች ነባር ሰልጣኞች ወንድ 11,202 ሴት 12,803 በድምሩ 24,005፣ አዲስ ሰልጣኞች ወንድ 5,610 ሴት 7,119 በድምሩ 12,729፣ ነባርና አዲስ ወንድ 16,812 ሴት 19,922 በድምሩ 36,734 እንዲሁም በግል ኮሌጆች ነባር ሰልጣኞች ወንድ 6,776 ሴት 20,025 ድምሩ 26,801፣ አዲስ ሰልጣኞች ወንድ 2,256 ሴት 7,410 ድምሩ 9,666፣ ነባርና አዲስ ወንድ 9,032 ሴት 27,435 በድምሩ 36,467፣ በአጠቃላይ በመንግስትና በግል ኮሌጆች ነባር እና አዲስ ሰልጣኝ ቅበላ ወንድ 25,844 ሴት 47,357 ድምር 73,201 መፈፀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 35.65% ነው፡፡

በሌላ በኩል የሼድ አቅርቦት ስራዎችን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር 2,600 ሼዶችን በመገንባት 7,800 ኢንተርፕራይዞችን (28,200 አንቀሳቃሾችን)፣ በ11 ወሩ 2,427 ሼዶችን በመገንባት 7,280 ኢንተርፕራይዞችን (26,320 አንቀሳቃሾችን) ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፡- 799 ሼዶች ተጠናቀው 929 ሼዶች (የባለፈውን ዓመት 130 ጨምሮ) ለ1,589 ኢንተርፕራይዞች፣ 4,863 (ወንድ 2,966 ሴት 1,897 አንቀሳቃሾች) ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ አፈጻጸሙ ከዓመቱ በተገነቡ ሼዶች 30.3%፣ በኢንተርፕራይዝ 20.37%፣ በአንቀሳቃሽ 17.24%፣ ከ11 ወሩ በተገነቡ ሼዶች 32.25%፣ በኢንተርፕራይዝ 21.82%፣ በአንቀሳቃሽ 18.44% ማከናወን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በክልላችን ለ436 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የስራ መደብ የተፈቀደ ቢሆንም እስካሁን 417 ማዕከላት

ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። የተሟላ በሚባል ደረጃ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ 252 ናቸው።

### 1.2.1.8. መሬት አስተዳደር

በበጀት ዓመቱ ለ380,944 ለባለይዞታዎች 1,422,081 የማሳ ካርታ፣ በ11 ወራት ለ338,617 ባለይዞታዎች 1,264,072 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ352,924 (አባወራና እማወራ 153,375፣ አባወራ 84,557፣ እማወራ 85,161፣ የጋራ ይዞታ ከባልና ሚስት ውጭ 18,854፣ የወል 6,456፣ ለመንግስት ተቋማት ለ1,741፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት 2,344) ባለይዞታዎች 1,339,157(94%) የማሳ ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ ከባለይዞታ ከ11 ወሩ 104.2%፣ ከዓመቱ 92.6% ነው። በሌላ በኩል በ11 ወራት ለ15,230 ተጋላጭ ህ/ሰብ ክፍሎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ በ11 ወራት ለ2,924 (ወንድ -1,658፣ ሴት-1,266) (ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናት 667 (ወንድ -416፤ ሴ-251)፣ አካል ጉዳተኞች 437(ወንድ 212፣ ሴት 225)፣ አረጋውያን 485(ወንድ 277፣ ሴት 208) የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 19.2%፣ ከዓመቱ 16.1% ነው።

በበጀት ዓመቱ ለ47,513፣ በ11 ወራት 43,554 ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,907 ( ወንድ 1,892፣ ሴት 1,018) ባለይዞታዎች 145,253,323 ብር የብድር ተጠቃሚ ሲሆኑ አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 7%፣  ከአመቱ ደግሞ 6% ነው። በተጨማሪም በ113 ወረዳዎች 100% የማሳ መረጃ በማጥራት 548,995 ማሳዎችን ወደ NRLAIS ሲስተም እንዲያሸጋግሩ በማድረግ የሚቀርቡትን 262,893 የመሬት ግብይቶች ማረጋገጥ፣ ማጽደቅ በሲስተሙ በመመዝገብ የመሬት መረጃ ስርዓት ደህንነትንና ቀጣይነትን ለማሻሻል በበጀት ዓመቱ 548,995፣ በ11 ወራት 512,395 ማሳዎችን ወደ NRLAIS ሲስተም እንዲያሸጋግሩ ለማድረግ ታቅዶ በ47 ወረዳዎች በ461 ቀበሌዎች የ618,483 ማሳዎች መረጃ ወደ ሲስተም የማሸጋገር ስራ ተሰርተል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 120.7%፣ ከዓመቱ 112.7% ነው።

በገጠር መሬት ያለውን ህገ-ወጥ ተጠቃሚነትን በመከላከል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቀነስ 184,801 አቤቱታና መልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት፣ ያላግባብ ይዞታቸውን አጥተው የነበሩ ባለይዞታዎች ይዞታ ማስመለስ ዋና ተግባር ተደርጎ ሲሰራ የቆየ ሲሆን አላግባብ ይዞታቸውን ያጡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ በማጥራት

ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ለማድረግ በበጀት አመቱ 7,440 (ወንድ 4,442፤ ሴት 2,998)፣ በ11 ወራት የ6,820 (ወንድ 4,072፤ ሴት 2,748) ታቅዶ የ1,657 (ወንድ 847፣ ሴት 810) ባለመብቶች ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎችም) መሬት እንዲመለስላቸው ተደርጓል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 24.3%፣ ከአመቱ 22.3% ነው። ሌላዉ በበጀት ዓመቱ ከ1,916 ግለሰቦች 227 ሄ/ር፣ በ11 ወራት ከ1,756 ግለሰቦች 208 ሄ/ር ከይዞታ መብት ህጉ ከነፈጋቸዉ አካላት መሬት ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያየ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከ 686 ግለሰቦች 781 ሄ/ር መሬት ማስመለስ ተችሏል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 39%፣ ከአመቱ 35.8%መፈጸም ሲቻል በበጀት ዓመቱ ከ41,088 ህገወጦች 15,842 ሄ/ር፤ በ11 ወራት ከ37,664 ህገወጦች ከ14,522ሄ/ር የተወረሩና የተገፉ የወል መሬቶች መሬት ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያየ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የ25,282 ህገወጦች 7,112 ሄ/ር መሬት የማስመለስ ስራ ተከናዉኗል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 67%፣ ከዓመቱ ደግሞ 61.5% ነዉ።

በ178 ቀበሌዎች ለ 177,374 ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘጋጅቶ አሁን ካለው 3,122 ወደ 3,300 ቀበሌና ከ3,309,568 ወደ 3,486,942 ባለይዞታ ማድረስና ርክክብ ማድረግ ለ 177,374 ባለይዞታዎች ርክክብ በማድረግ አሁን ካለው 2,688,164 ባለይዞታዎች ወደ 2,865,538 ባለይታዎች ርክክብ በማድረግ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ጥናትና ትግባራ በማድረግ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ታቅዶ፡- በበጀት ዓመቱ ለ177374፣ በ11 ወራት 161,595 የመሬት ተጠቃሚ ባለይዞታዎች አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት በ11 ወራት 195,645 የመሬት ተጠቃሚዎች የተዘጋጀውን እቅድ ለማስረከብ ታቅዶ ለ65,282 መሬት ተጠቃሚ ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ በማዘጋጀት ለ33,476 ባለይዞታዎች ርክክብ ተፈጽሟል። አፈፃፀሙ እቅድ ከማዘጋጀት አንጻር ከ11 ወሩ 40%፣ ከዓመቱ 36% ሲሆን እርክክብ ከማድረግ አንጻር ከ11 ወሩ 17%፣ ከዓመቱ 18.9% ተከናውኗል። በበጀት ዓመቱ 1,399,911 ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ ተዘጋጅቶ ርክክብ የተደረገላቸውን ባለይዞታዎች በቂ ድጋፍና ክትትል አድርጎ ወደ ተግባር ለማስገባት ታቅዶ በአስራ አንድ ወሩ 758,079 (54.1%) ተጠቃሚዎች ወደ ተግባር ገብተዋል።

በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አ/አደር በቀበሌ ማእከል ለማሰባሰብ በ200 ቀበሌዎች አዲስ ፕላን በማዘጋጀትና በ152 ቀበሌዎች 17,490 ቦታዎችን በመሸንሸን የቀበሌ ማእከላት ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲከናወኑ ድጋፍ በማድረግ፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የገጠር ቀበሌ ማእከላት የእድገት ማእከል እንዲሆኑ ለማስቻል የተቋሙ ዋና እቅድ ተደርጎ የተወሰደ ሲሆን የገጠር

ቀበሌ ማእከላት የእድገት ማእከል ሆነው የአ/አደሩን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያላቸው ሚና የጎላ ነው። ይህን እውን ለማድረግ 48 (24%) ስኬጅ ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን 3,856 (22%) ቦታዎች በመሸንሸን 4,468 (34.5%) ቦታዎችን ለተጠቃሚወች ማስረከብ ተችሏል። እንዲሁም 12,920 ሳይት ፕላን ለመስጠት ታቅዶ 5,645 (39.7%) ሳይት ፕላን የተሰጠ ሲሆን ግንባታ ላጠናቁ ተጠቃሚዎች ለ3,808 (31.7%) ገንቢዎች ቋሚ ካርታ ሲሰጥ በተመሳሳይ በነዚህ እና መሰል ተግባራት ከቀበሌ ማእከላት አገልግሎቶች ክፍያዎች በበጀት ዓመቱ ብር 5,242,838.00 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 10,040,492 ( ከእቅድ በላይ) ገቢ መሰብሰብ ተችሏል።

ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬታቸውን ለሚለቁ 50,502 ባለይዞታዎች 22.69 ቢሊዮን ብር በህግ የተፈቀደውን የካሳ መጠን በማስላት እግዲከፈል ማድረግና መልሶ የማቋቋም ተግባራትን ለማከናወን ታቅዶ የ10,675 (እማወራና አባወራ 6,401፣ እማወራ 2,154፣ አባወራ 2,123) የልማት ተነሽዎች ብር 4.75 ቢሊዮን ብር የካሳ ክፍያ ተከናውኗል። አፈፃፀሙ ከባላይዞታ ከ11 ወሩ 22.8%፣ ከበጀት ዓመቱ 20.9% ነው። በሌላ መልኩ በልማት ምክንያት ተነሺ ባለይዞታዎችን መልሶ ለማቋቋም በዓመቱ ለ5,050፣ በ11 ወራት 4,629 ባለይዞታዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 2,157(አባውራ 431፣ እማውራ 520፣ አባወራና እማወራና 1,202) ባለይዞታዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 46.6%፣ ከበጀት ዓመቱ 42.7% ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ተነሺ ባለይዞታዎችን ለማቋቋም በአመቱ ለ2,525፣ ባለይዞታዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 1,252 (49.6%) (ወንድ 769፣ ሴት 483) ባለይዞታዎች የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪም በበጀት በአመቱ ለ25,251፣ ባለይዞታዎች ባላቸው የካፒታል አቅም መሰረት በተለያዩ የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ ለ7,324 (ወንድ 5,201፣ ሴት 2,053) ባለይዞታዎች ተደራጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 31.6%፣ ከዓመቱ 29% ነው።

የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ስራዎችን በተመለከተ፡- በበጀት ዓመቱ 10,560 ሄ/ር ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል እና ለባለሃብቶች የሚተላለፍ መሬት ለመለየት ታቅዶ 7,562 ሄ/ር ነፃ መሬት በመለየት የእቅዱን 71% መፈጸም ሲቻል በ11 ወራት 132 ሄ/ር ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚውል ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ 146 ሄ/ር በመለየት የአመቱን እቅድ 90% መፈጸም ተችሏል። እንዲሁም

በበጀት ዓመቱ 60ሄ/ር ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውል ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ 35 ሄ/ር በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ መሬት መለየት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከዓመቱ 63% ሲሆን ከ11 ወሩ 67% ነው፡፡ በዚህም ነጻ መሬት በተለየባቸው ዞኖች ነጻ መሬቶችን ለማስተላለፍ በዞን ደረጃ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ 32 ባለሃቶች፣ በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ 151 ባለሃብቶች፣ በአገልግሎት ዘርፍ 17 ባለሃብቶች በድምሩ 200 ባለሀብቶችን የመለየት ስራም ተሰርቷል፡፡ አፈፃፀሙ ከ11 ወሩም ሆነ ከዓመቱ 57% ነው፡፡ በድምሩ በ3ቱም ዘርፎች(በግብርና፣ በኢንዲስትሪና በአገልግሎት) የተለየ ነፃ መሬት በዓመት እቅድ 10,872፣ ክንውን 7,745፣ ሄ/ር (71%) መሬት የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከነዚህ ተግባራት ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ 5,283,480፣ በ11 ወራት የአገልግሎት ገቢ ብር 3,975,480 ከሁሉም ዘርፎች ለመሰብሰብ ታቅዶ በጠቅላው በሁሉም ዘርፎች ብር 3,220,035.90 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 81%፣ ከዓመቱ 61% ነው፡፡

በተጨማሪም የሁለተኛ የይዞታ ማረጋገጫ ድብተር ለመስጠት የሚሰራባቸውን ወረዳዎች ከአየር ፎቶግራፍ፣ ኢስላ ዳታና ከመስክ ከተሰበሰበ መረጃ በመጠቀም በተለያዩ ሶፍትዌሮች በመታገዝ ለተግባሩ የሚያገለግሉ በ250 ቀበሌዎች የመስክ ካርታ፣ በ300 ቀበሌዎች የትቻታ ካርታዎችን እንዲሁም በ275 ቀበሌዎች የማሳ ካርታዎችን በማዘጋጀት በግብዓትነት ማቅረብ፣ መረጃዎችን ማደራጀትና መተንተን፣ መረጃ ለሚጠይቁ መረጃዎችን ማቅረብን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ የ250፤ በ11 ወራት የ230 ቀበሌዎችን የመስክ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ80 ቀበሌዎች የመስክ ካርታ በማዘጋጀት ከ11 ወሩ 34.7%፤ ከዓመቱ 32% ማከናወን የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የ275፤ በ11 ወራት የ250 ቀበሌዎችን የማሳ ካርታና ተያያዥ መረጃዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ186 ቀበሌዎች የማሳ ካርታ በማዘጋጀት ከ11 ወሩ 74.4%፣ ከዓመቱ 67.6% ማከናወን ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በከተሞች በአመቱ 77፣ የቀጠና ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ 31 የቀጠና ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን 40.3% ሲሆን በአመቱ 387 በ11 ወራት 291 የሰፈር ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በ11 ወራት 112 የሰፈር ካርታዎች የተዘጋጁ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 38% ከአመቱ 29% ነው፡፡ ሌላዉ በ11 ወራት 70,950 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ በ11 ወራት 10,037 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 14.1%፣ ከአመቱ 12.9% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ በከተሞች ለ 77,400 የይዞታ ወሰን ለማካለል፣ የይዞታ ወሰን ቅየሳ ስራ ለመስራት ታቅዶ ባለፉት አስራ አንድ ወራት 17,178(22%) የይዞታ ወሰን የማካለል ስራ

የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ11 ወሩ 24%፤ ከዓመቱ 16,808 የይዞታ ወሰን ቅየሳ ስራ በመስራት ከዓመቱ ከ21.7% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ 1,600፣ የ2ኛ ደረጃ እና የ3ኛ ደረጃ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ሞኑመንት በስታንዳርድ መሰረት በማምረት ለመትከል ታቅዶ 235 (14.6%) ሞኑመንት በማምረት መትከል ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ ለ77,400፤ የከተማ መሬት ባለይዞታዎች የመብት ምዝገባ በማድረግ የመብት ምዝገባ ለተደረገላቸው ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ በ11 ወራት 12,493 ይዞታዎችን በመመዝገብ ለ10,919 ባለይዞታዎች የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ከ11 ወሩ የመብት ምዝገባ 17.6%፣ ከዓመቱ የዕቅዱ 16% መፈጸም ሲቻል ሰርተፊኬት ከመስጠት አንጻር ከ11 ወሩ 15%፣ ከአመቱ ደግሞ 14% መፈፀም ተችሏል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ለ77,400፤ በ11 ወራት ለ70,950 የይዞታ መብት የተረጋገጥላቸው ይዞታዎችን ማስረጃ ለመብት ምዝገባ ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ በ11 ወራት 8,055 ማስረጃዎችን ርክክብ በመፈፀም ከ11 ወሩ 11%፣ ከዓመቱ የዕቅዱን 10% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመሬት ተግባራት ጋር ተያይዞ የተሰበሰበ ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ከመሬት ግብይት አገልግሎት፤ ከቀበሌ ማእከላት አገልግሎቶች ክፍያዎች፤ ልዩልዩ የአገልግሎት ገቢ (የከተማ ቤትና የይዞታ ስም ዝውውር) በጠቅላላዉ 231,725,152 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 1.2.2. የከተማ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም

ከህብረተሰብ ተሳትፎ ተግባራት አንጻር በበጀት ዓመቱ በ683 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 50% እንዲያዋጣ በማድረግ 2,611,860,000 ብር የሚገመት የህብረተሰብ ተሳትፎ ለማድረግ ግብ ተይዞ በ11 ወሩ በጥሬ ገንዘብ 331,909,182 ብር፣ በጉልበት 368,801,826 ብር፣ በቁሳቁስ 284,070,030 ብር በድምሩ 984,781,038 ብር አስተዋጽኦ ተደርጓል፡፡ በመንግስት በኩልም 492,146,995 ብር ለአካባቢ ልማት ስራዎች ወጪ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው ለአካባቢ ልማት ስራዎች 1,476,928,032 ብር ወጪ የተደረገ ሲሆን የህዝብ ተሣትፎ አፈፃፀም 37.70% ነው፡፡

የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ በ683 ከተሞች የገቢ ሀብታቸውን ውጤት በሚያመጣ መንገድ አሟጠው በመጠቀም የመሰረተ ልማት ወጭያቸውን 70% ከራሳቸው ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ገቢ እንደሸፍኑ ለማድረግ ግብ የተያዘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በ606 መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች 7,000,128,000.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ

536,576,006 ብር (7.67%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በገቢዎች ቢሮ በኩል ከ77 ከተማ አስተዳደሮች 15,500,000,000 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 3,140,464,906 ብር (20.26%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከሀገራዊው የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ጋር የተጣጣመ ክልላዊ የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን እና የከተሞች ክላስተር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቀዶ የክልላዊ ከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ዝግጅት አንድ አካል የሆነው የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ሪፖርት የተጠናቀቀ ቢሆንም ዋናው ክልላዊ የከተማ ልማት ስፓሻል ፕላን ዝግጅት በተለያዩ ምክንያቶች ተፈፃሚ አልሆነም፡፡

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ አሳታፊ፣ ጥራት ያለውና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የከተማ ፕላን ዝግጅት እንዲኖር በማድረግ ለ105 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ፣ ለ90 መሰረታዊ የከተማ ፕላን፣ ለ15 ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም 30 የሰፈር ልማት ፕላን (NDP) ለማዘጋጀት ግብ ተይዞ በ11 ወሩ የ92 (87.62%) ከተሞች መሠረታዊ ካርታ፣ ለ71 (78.89%) ከተሞች መሰረታዊ የከተማ ፕላን፣ ለ8 (53.33%) ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን እንዲሁም 26 (86.67%) የሠፈር ልማት ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የ80 ከተሞችን መሠረታዊ መረጃዎች በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ የ71 (88.75%) ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎች (Urban Profile) በማሰባሰብና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ በክልሉ የሚገኙ 683 ከተሞች በተዘጋጀላቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማትና አገልግሎቶች ቅንጅትና ትግበራ ፕላን እንዲመሩ ለማድረግ ግብ ተይዞ በፕላን የሚመሩ ከተሞች ቁጥር 676 ማድረስ የተቻለ ሲሆን የቀሩት 7 ከተሞች በቀጣይ ፕላን ተዘጋጅቶላቸው ወደ ፕላን ትግበራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

ህገ ወጥ ግንባታን በተመለከተ በ311 ከተሞች 75,211 ህገ-ወጥ ይዞታዎች መረጃቸው አደራጅቶ በመያዝ እና በማፍረስ 86 ሄ/ር ቦታ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ153 ከተሞች 34,363.8 (45.69%) ህገወጥ ይዞታዎች ተደራጅተው የተያዙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 7,737 (10.29%) ህገ ወጥ ግንባታ እንዲፈርሱ በማድረግ 64.59 (75.10%) ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ከመሬት ዝግጅት አኳያ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ለጨረታና ለምደባ 5,500 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,045.709 ሄ/ር (55.38%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡በ138 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ የተደራጁ 302 ነባር ማህበራትን በማጠናከር በከተሞች ከሚመነጨው ቆሻሻ 1,100,000 ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ ለማስወገድ ታቅዶ በ77 ከተሞች  የሚገኙ 200 ነባር

ማህበራትን በማጠናከር 954,072.27 (86.73%) ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡

በ16 ከተሞች እንደ የከተሞች የእድገት ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በመስፈርቱ ከ3ኛ ወገን ነጻ እንዲሆን ለማድረግ ግብ ተይዞ በ11 ወሩ በ16 ከተሞች በስታንዳርዱ መሰረት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ለማድረግ ታቅዶ በ4 ከተማ ተከናውኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ በ683 ከተሞች 880,000 የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 22 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 1,510 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ በ9 ወሩ በ383 (56.08%) ከተሞች ወንድ 489,525 ሴት 432,204 ድምሩ 921,729 (104.74%) የህብረተሰብ ክፍሎችን በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠርና በቀጥታ በማሳተፍ 19,130,165 (86.96%) ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በዚህ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 1,209.281 ሄ/ር (80.08%) አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡ በ215 ከተሞች  በፕላን የተመላከቱ 1500 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ በ100 ከተሞች የሚገኙ 1413 (94.2%) አረንጓዴ ቦታዎች የተለዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለ980 (69.35%) አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡

## 1.2.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም

### 1.2.3.1. ትምህርትና ስልጠና

በአማራ ክልል የትምህርት ዘርፍ በየዓመቱ ለኢኮኖሚው በአማካይ የ8.3 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከማህበራዊ ልማት ዘርፍ ስራዎቻችን አንዱና ምናልባትም ለክልላችን ሁሉን አቀፍና ዘላቂ ለውጥ ትልቅ ሚና የሚጫወተው ለዜጎች ተደራሽና ጥራቱ የተጠበቀ  የትምህርት ስራ መስራት ነው፡፡ ስለሆነም በበጀት አመቱ በቅድ-መዝግጅት ተግባር ግብአት ማሟላት አንዱ ሲሆን ሰብአዊ ግብአትን ማሟላት ቀዳሚው ነው፡፡ በዚህም ከሚያስፈልገው 184,304 የሰው ሀይል መካከል 175,824 (ወንድ 98,892፣ ሴት  76,932) ወይም 95.4% በስራ ላይ ነው፡፡ በተጨመሪም በበጀት አመቱ በቅድመ-ዝግጅት ወቅት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ቁሳዊ ግብዓቶችን ከማሟላት አንፃር በ11 ወሩ 5,451 ክፍሎችን በአዲስ መገንባት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 3,442 የመማሪያ ክፍሎችና 2,009 ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም 8,882 ክፍሎችን መጠገን የተቻለ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 5,136 የመማሪያ ክፍሎችና 3,746 ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል 92,298 ኮምባይንድ ዴስክ ለማቅረብ ታቅዶ 79,178(85.78%) ማሳካት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ትምህርት

ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች ቅድመዝግጅት ስራዎች ተጠናቀው በተመሳሳይ ቀን ትምህርት መጀመር ባይቻልም ያጋጠሙ ፈተናዎችን ተቋቁመው በቂ ዝግጅት ከአደረጉ 492 አጸደህፃናት መካከል 415 (84.3%)፣ 6,247 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4,804 (76.9%) እና 471 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 341 (72.4%) ትምህርት ቤቶች በትምህርት የመጀመሪያው ቀን ትምህርት መስጠት ጀምረው አሁንም እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የመምህራን እና ትምህርት አመራሩን አቅርቦት፣ ተነሳሽነት እና ብቃትን ማሳደግ ሌላኛው ቁልፍ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫ ነው፡፡ በዚህም ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚያስተምሩ መምህራን እና ትምህርት አመራሮች የትምህርት ደረጃ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት እንዲያሟሉ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህ የሚያገለግል ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ ለመተግበር ጥረት ተደርጓል፡፡ የትምህርት አመራሩንና መምህሩን ሙያ የሚያሻሽሉ ልዩ ልዩ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች በመሰጠት ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ከተጀመረ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መጻሕፍት ተማሪ ጥምርታ 1፡2 ለማድረስ ታቅዶ በዘመኑ ለተማሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው መጽሃፍት ብዛት 8,038,353 (የአንደኛ ደረጃ መጽሃፍት 5,771,623፣ የመካከለኛ ደረጃ መጽሃፍት 2,266,730) የደረሰ ሲሆን አሁን ተመዝግበው በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት መድረስ የሚገባው መጽሃፍ ብዛት (በትምህርት አይነት በየክፍሉ ተማሪ ብዛት ተባዝቶ) 18,835,187 በመሆኑ የተማሪ መጽሃፍት ጥምርታው ከ1፡2.34 ደርሷል፡፡ ይህም ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር 85.4% ተፈጽሟል፡፡ ይሁንና ይህ አፈጻጸም በርካታ የክልሉ ህጻናት ትምህርት ስላልጀመሩ የተገኘ ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሱ አማካይ ጥምርታው አንድ መጽሃፍ ለ3 ተማሪ እና ለ4 ተማሪ አካባቢ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በክልላችን ውስጥ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ትምህርት ባልተጀመረባቸው ዞኖችና ትምህርት ጀምረውም ከክዘና ማዕከላት ወደ ትምህርት ቤቶች ለማጓጓዝ አስቼጋሪ ወደ ሆኑ አካባቢዎች ማሰራጨት አልተጀመረም፡፡

ሌላኛው ወሳኝ ተግባር የተማሪዎችን ተሳትፎ ማጎልበት መቻል ነው፡፡ በ2016 የትምህርት ዘመን የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ 6,292,241 (ወንድ 3,095,327፣ ሴት 3,196,914) ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 3,673,250 (ወንድ 1,787,453፣ ሴት 1,885,797) መመዝገብ ተችሏል፡፡ ይህም ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር 58.38% (ወንድ 57.75%፣ ሴት 58.99%) ነው፡፡ ለአፈፃፀሙ ዝቅ ማለት

ዋነኛው ችግር በክልላችን የተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ሲሆን ከተመዘገቡትም ውስጥ የማሰለስ ምጣኔው ከፍተኛ ሆኗል፡፡ ከላይ በተገለት ችግሮች ምክንያት ከ3,000 በላይ ትምህርት ቤቶች አልተከፈቱም፡፡ ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችም ከትምህርት ውጭ ናቸው፡፡ በጸጥታ ችግሩ ምክንያት በየጊዜው የሚዘጉና የሚከፍቱ ትምህርት ቤቶችም በርካታ ናቸው፡፡

በጐልማሶች መሰረታዊ ትምህርትና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መስክ 28,155 የመማማሪያ ጣቢያዎችን ለማቋቋም ታቅዶ 5,290 ጣቢያዎችን ማቋቋም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 18.8% ነው፡፡ በ2016 የትምህርት ዘመን 844,654 ጎልማሶችን ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ለማሳቻል ታቅዶ 36,736 (4.3%) ጎልማሶች ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ችለዋል፡፡ የጎልማሶችን ትምህርት ለማሻሻል እንደ ትምህርት ብርሃን ምዘና ያሉ አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበር ጅምር ስራዎች የነበሩ ሲሆኑ ካለፈው አመት ጀምሮ በአዲስ መልክ የማነቃነቅ ስራ ተጀምሯል፡፡ በወረዳዎች የሚቀጠሩ አመቻቾችን ቁጥር ለማሻሻል እንዲሁም በየአካባቢው በታቀደ ሁኔታ የተፋጠነ ትምህርት እንዲጀመር ጥረት ተደርጓል፡፡

በትምህርት ስራችን ላይ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ብርቱ ርብርብ ማድረግ ከሚገቡን ወሳኝ ተግባራት መካከል አንዱ የተማሪ ምገባ ስራችን ነው፡፡ በ2016 የትምህርት ዘመን 1,000,000 ተማሪዎችን ለመመገብ የታቀደ ሲሆን 221,103 (117,480 ሴቶች) ተማሪዎችን ወይም 22..11% (11.74% ሴቶች) በመፈፀም 446 ትምህርት ቤቶችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ሂደት ውስጥ ከረጅ ድርጅቶች ድጋፍ በተጨማሪ የክልሉ መንግስት የመደበው 75 ሚሊዮን ብር በድርቅ በተጎዱ 4 ወረዳዎችና 102 ትምህርት ቤቶች ለ56,340 ተማሪዎች የተማሪ ምገባ እንዲካሄድ ማድረግ አስችሏል፡፡ ይህ ተግባር ክልሉ ከሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ጥሩ የሚባል ቢሆንም ከእቅዳችን አንፃር ግን ገና በጅምር ላይ ያለ ሲሆን በትምህርት ስራችን ላይ ዘላቂ ለውጥ በሚያረጋግጥ መንገድ፣ የህብረተሰቡንና ሌሎችንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ባካተተ መልኩ ልዩ ትኩረት ሰጥተን መፈፀም ይኖርብናል፡፡

### 1.2.3.2. ጤና ጥበቃ

የጤናው ዘርፍ ለክልሉ ኢኮኖሚ እድገት በአማካይ የ2.23 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ አበርክቶ አለው፡፡ስለሆነም በበጀት አመቱ ልክ እንደሌላው ዘርፍ ሁሉ ለጤናው ሴክተር ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ የጤናው ዘርፍ ለክልሉ ኢኮኖሚ እድገት በአማካይ የ2.23 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ አበርክቶ አለው፡፡ በክልሉ ጥራት ያለዉ ፍትሃዊ የጤና

አገልገሎትን ለማሳለጥ እና ማህበረሰቡን ለማርካት የተጀመሩ ሰባት አዳዲስ ተግባራት/new initiatives) አፈጻጸም ሲታዩ በጤና ጣቢያ ደረጃ አልትራሳውንድ አገልግሎት የጀመሩ ቁጥር 132፣ ጤና ጣቢያዎችን የቀዶ ህክምና አገልግሎት ማስጀመር 19፣ ኦዲቴብል የሆነ የፋርማሲ አገልግሎት (APTS) የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ቁጥር 144፣ የሙሉ ኤሌክትሮኒክ የህክምና መረጃ አያያዝ ስርዓት (Full EMR) የተገበሩ ጤና እና ሆስፒታል ቁጥር 6 እና የማህበረሰብ መድሃኒት ቤት አገልግሎት በወረዳ/ከተማ አስተዳደር በቁጥር 27 በማድረስ 5 በዝግጅት ላይ ናቸዉ፡፡

የላብራቶሪ አገልገሎትን ጥራት እና ሽፋን ለማሳደግም ከህ/ሰ/ብ ጤና ኢንስቲዩቱ ጋር በርካታ የተሻሉ ስራዎች ተሰርተዋል የግቦችን አፈጻጸምም ስንመለከት በ11 ወሩ የቤተሰብ እቅድ 82% ለማድረስ ታቅደ 3,243,321 (75.4%) ለሚሆኑ በመውለድ እድሜ ክልል ላሉ ሴቶች መስጠት ተችሏል፡፡ የቅድመ ወሊድ ክትትል ለመጀመሪያ ጊዜ (ANC1) አገልግሎት ለ90% ለማድረስ ታቅደ 83.5% ለሚሆኑ ነፍሰጡር እናቶች የአንድ ጊዜ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን 22.4% የሚሆነት የእርግዝና ጊዜቸው ከ12 ሳምንት በፊት ሁኖ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሲሆኑ ቅድመ ወሊድ አራት  ጊዜ ክትትል ያገኙ እቅድ 78%  ክንዉን 66% ነዉ፡፡

በተጨማሪ በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት 75% ለማድረስ ታቅደ 59% የሚሆኑ እናቶች በጤና ተቋም አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ 10.2% የሚሆኑት በቀዶ- ጥገና ህክምና የወለዱ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ለ35,668 ጨቅላ ህፃናት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ሆስፒታሎች በጨቅላ ህፃናት ፅኑ ህክምና ክፍል ተኝተው የታከሙ ሲሆን 76.6%(26,404) የሚሆኑት በተሰጣቸው ህክምና ሙሉ በሙሉ ድነዋል፡፡ በክልሉ ይሞታሉ ተብሎ ከሚገመተው 3,120  እናቶች መካከል 273(9.1%) እናቶች  ሞት ሪፖርት ተደረገዋል፡፡ሞተዉ ይወለዳሉ ተብለዉ ከሚገመተዉ 4,197 ጨቅላ ህፃናት 3,442 ሞተዉ የተወለዱ ሪፖርት ተደርገዋል፡፡ ችግሩ  የበዛባቸዉን ሆስፒታሎች በመምረጥ የሞት መጠኑን ለመቀነስ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በ2016 በጀት አመት በ11 ወር ዉስጥ ከ1 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ፔንታቫለንት አንድ፣ ፔንታ ቫለንት ሦስት እና የኩፍኝ አንድ ክትባት 100% ለማድረስ ታቅዶ በቅደም ተከተል ክትባቱን ይወስዳሉ ተብሎ ከሚጠበቁት 95.8%፣ 91.3%፣ 86.6% ተከትበዋል፡፡ ከ5 ዓመት በታች ህፃናት የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ልየታ ስራ 75% ታቅዶ 47% ለሚሆኑ ህፃናት የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ 56.2% የሚሆኑት መካከለኛ የምግብ

እጥረት የተገኘባቸው ሲሆን 4.1% ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸዉ ናቸው፡፡ የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ከገቡት መካከል 47,757 (78%) የሚሆኑት በህክምና ጋይድላይኑ መሰረት ታክመው ድነው መውጣት ችለዋል፡፡

በተጨማሪም ባለፋት 11 ወራት ተላላፊ የሆኑ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር ስራ የተሰራ ሲሆን ኤች አይ ቪን ከመከላከል እና መቆጣጠር አንፃር ሶስቱን 95 ኢላማዎች ለማሳካት በ11 ወር ዉስጥ ጠቅላላ ኤችአይቪ በደማቸው መኖሩን ያወቁት ቁጥር ይኖርባቸዋል ተብለው ከሚጠበቁት (Estimated PLHIV estimate) 173,416 ውስጥ 157,302 ራሳቸዉን አውቀዋል በመሆኑም የመጀመሪያው 95 ኢላማ 92% ማድረስ ተችሏል፡፡ሁለተኛውን 95 ለማሳካት የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመጠቀም ላይ ያሉ ህሙማን መጠን (currently on ART) 154,928 (99.8%) የሚሆኑ ሰዎችን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 3,066 ህጻናት ናቸው ፡፡ በተጨማሪ ሶስተኛውን 95 ኢላማ ለማሳካት ከጸረ-ኤች አይቪ መድሃኒት ተጠቃሚዎች 145,336 (96%) የሚሆኑት በደማቸው ያለው የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1000 ኮፒ በታች ነው፡፡

የቲቢ ሕክምና ሽፋን (ሁሉም አይነት) በ 11 ወሩ 65% ሲሆን ባለፈው በጀት አመት ከነበረው 77% ዝቅተኛ አፈጻጸም ተመዝግቧል እንዲሁም ሕክምና በትክክል ወስደው ህክምናቸዉን ሙሉ ለሙሉ ያጠናቀቁ 96% ማድረስ ተችሏል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት በ11 ወር ውስጥ 3,682,162 የሚሆኑ የወባ ተጠርጣሪዎች በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት የላቦራቶሪ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 1,246,910 (33.9%) ወባ ተገኝቶባቸዋል ፡፡ በክልላችን ውስጥ ባሉ ጤና ተቋማት ውስጥ 25 ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት የሞቱ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ በ2016 በጀት ዓመት በ11 ወር ዉስጥ 72,626 (11.7%) ሴቶች የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ልየታ ተደረገዉ 2,569 (3.5%) የማህፀን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምልክት ተገኝቶባቸዋል 1,683 (65.5%) ህክምና ተደርጎላቸዋል፡፡ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ዞኖች በኮሌራ በበሽታ ወረርሽኝ 4,983 ሰዎች ተይዘው የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ከበሽታው ያገገሙ 4,893 ሲሆኑ የሞቱት ደግሞ በቁጥር 90 ነበሩ፡፡ 33,885,622 ሰዎች ለተመላላሽ ህክምና፣ 318,007 ሰዎች ለተኝቶ ህክምና እና 726,900 ለድንገተኛ ህክምና በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ጤና ተቋማት ጎብኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 81,073 ሰዎች ከፍተኛ ቀዶ-ህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በሌላ መልኩ በ2016 11 ወር የማዐጤመ አባል ይሆናሉ ብለን

ከያዝነው 4,576,373 አባ/እማወራ ውስጥ 2,827,458 (62%) አባል ማድረግ ተችሏል፡፡ከከፋይ አባላት 2,072,602,115 ብር የተሰበሰበ ሲሆን 2,043,506,977.00 (99%) ወደ ጤና መድህን አካውንት ገብቷል፡፡

### 1.2.3.3. ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ

በበጀት አመቱ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ አንዱ በቢሮው ታቅዶ ሲፈጸም የነበረ ተግባር ነው፡፡የሴቶችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ በሚመለከት በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊትነት ዙሪያ ሴቶች ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ውስጥ 276,485 ሴቶች በተለያዩ አደረጃጀቶች ተደራጅተው መብታቸውን እንዲያስከብሩ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጡን የተሻለ ለማድረግ 4 የአንድ ማእከል አገልግሎት ለማጠናከር በእቅድ ተይዞ 22 (100%) የአንድ ማዕከላትን ከተለያዩ አጋር አካላት በተገኘ የገንዘብ እና የአይነት ድጋፍ ማጠናከር የተቻለ ሲሆን በማዕከላቱ 1058 ሴቶች የህክም፣ የስነ ልቦና ድጋፍና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ በተመሳሳይ የተለያዩ ጥቃት (የኢኮኖሚ፣የስነ ልቦና እና ፆታዊ ጥቃት) ለደረሰባቸው 18,190 ሴቶች የንግድ ክህሎት ስልጠና በመስጠት፣የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎች በማመቻቸት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሀብት በመሰብሰብ 13,556,016 ብር ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ሴቶችን የሰላሙ ባለቤት ለማድረግ ከሴቶች አደረጃጀት ጋር በመሆን በተሻለ ንቅናቄ የሰላም ኮንፈረንሶችን በማስኬድ 900,000 የሚሆኑ ሴቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ 783,788 ሴቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡

የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማሳደግ በሚመለከት በበጀት ዓመቱ 700,000 ሴቶች በልማት ቡድንና ራስ አገዝ እንዲቆጠቡ በማድረግ 700,000 ሚሊዩን ብር እንዲቆጥቡ በዕቅድ ተይዞ 371232 ሴቶች ብር 501,281,256 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ከሴቶች አኳያ 53 በመቶ እንዲሁም ከቆጠባ አኳያ 64 በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 3,522,738 ሴቶች፣1,268,000,000 ብር እንዲበደሩ በእቅድ ተይዞ 429,556 ሴቶች፣ 444,723,909 ብር ብድር ወስደዉ በተለያዩ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 9,040 የልማት ህብረቶችን በአዲስ ለማቋቋም እና 164,555 የልማት ቡድኖችን ለማጠናከር ታቅዶ 10,210 የልማት ቡድኖችን በአዲስ በማቋቋም እና 50,115 የልማት ህብረቶችን በማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡

የህፃናትን ሁለንተናዊ መብትና ደህንነት ማስጠበቅን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ 1,538,020 (ሴት 769,010) ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በህጻናት ላይ በሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሃይል ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር በዕቅድ ተይዞ 1,274,458( ሴት.689,974) ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ግንዛቤ ከመፍጠር አኳያ 83% ነው፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 724 ቀበሌዎችን ከህጻናት ጋብቻ ነጻ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 139(19.2 ከመቶው) የሚሆኑ ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህጻናትን ተሳትፎ ማረጋገጥን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 596,125 (ሴት 290,691) የሚሆኑ ህጻናትን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው መካከልም 613,618 (ሴት 306,809) የሚሆኑትን ህፃናት በአዲስ የህፃናት ፓርላማና በክበባት እንዲደራጁ ታቅዶ 342.746(ሴት.179,881)የሚሆኑ ህፃናትን በልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን ማደራጀት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 56% ነዉ፡፡ 3,648 የሚሆኑ በየደረጃዉ የሚገኙ የህዝብ ም/ቤቶች የህፃናት ተወካዮችን በማሳተፍ 10,944 (ሴት 5472) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ አባላትን በመወከል በየደረጃዉ በሚገኙ የህዝብ ምክር ቤቶችም እንዲሰተፉ ለማድረግ በተያዘዉ እቅድ መሰረት 884 በሚሆኑ ምክርቤቶች 3,798 (ሴት 1,730) የሚሆኑ የህጻናት ፓርላማ ተወካዮች እንዲያሳትፉ ተደርጓል፡፡

የህጻናትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚመለከት በበጀት ዓመቱ 451,610 (ሴት 226,919) ህጻናትን በተለያዩ አማራጭ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 348,444 (ሴት 186,560) ህፃናትን በተለያዩ አማራጭ የህጻናት ድጋና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የህፃናት ማዋያዎችን 62 በአዲስ በማቋቋም በአዲስ በተቋቋሙና በነባሮች 2,380 (ሴት 1,190) ህፃናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 26 ተቋቁመዋል፡፡ በአዲስ በተቋቋሙና በነባሮች 3,875 ( ሴት 1,937) የሚሆኑ ህጻናት በማቆያዉ ገብተዉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ በሚመለከት የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶችን አማካኝነት ከነባርና ከአዲስ የጥምረቱ አባላት በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት 144,705,402 ብር ሀብት ለመሰብሰብ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 82,620,260.00 በዓይነት 42,132,339,በድምሩ 124,765,449 የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ 86% ነው፡፡ በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች አማካኝነት

በተሰበሰበ ኃብት በበጀት ዓመቱ 201,717 ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 165,641 (ሴት 88,450) ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን አፈፃፀሙም 82% ነው፡፡

በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ ሆነው የሰብዓዊ ድጋፍ የተደረገላቸው ሴቶች፣ ህፃናት እና ሌሎች የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ ዜጎች በተመለከተ ዕቅድ 452,252 ሲሆን ክንውን 430,967 (ሴት 260,003) ሲሆን አፈፃፀም 95% ነው፡፡ የመብት ጥሰት ለደረሰባቸው 1744 አረጋዊያን እና 1176 አካል ጉዳተኞች  የሕግ ጥበቃ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መብታቸው እንዲከበር ለመሥራት በዕቅድ ተይዞ 788 (ሴት 466) አረጋውያን እና 595 (ሴት 295) አካል ጉዳተኞች ሲሆን ከዕቅዳችን አኳያ 45.2% እና 50.6% እንደቅደም ተከተላቸው መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የአረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ በሚመለከት በየደረጃው የሚገኙ 311 የአረጋዊያን እና 402 የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን  ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለማጠናከር በዕቅድ ተይዞ 182 የአረጋውያን እና 394 የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን በማጠናከር ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 12,303 አረጋውያን እና 2394 አካል ጉዳተኞችን  በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ድጋፍ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 5,758 አረጋዊያን እና 2,449 አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 47% እና 102.3% እንደቅደም ተከተላቸው ሆኗል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 94,446 አረጋውያን ቋሚ እና 76,618 አረጋውያን ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ታቅዶ ለ158,937 አረጋዊያን ቋሚ እና 138,210 ልዩ ልዩ ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ ለ12011 አካል ጉዳተኞች የአካል ተሃድሶ አገልግሎት ታቅዶ ለ10,416 (ሴት 3632) አካል ጉዳተኞች የተጠቀሰውን አገልግሎት በመስጠት የእቅዳችንን 86.7%ማከናወን ተችሏል፡፡ የሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ በሚመለከት በበጀት ዓመቱ ለ3582 ለሚሆኑ ሴት አመራሮች በሊደርሽፕ (በአመራርነትና መሪነት) የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1660 ለሚሆኑ ሴት አመራሮች በሊደርሽፕ የአቅም ግንባታ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም 46.34 % ነው፡፡

በየደረጃው ለሚገኙ ለ5245 የተቋማት ባለሙያዎች በአካቶ ትግበራ እና በአዲሱ የተቋማት መመዘኛ ማዕቀፍ (Inclusion Leveling Tool) ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 4203 የተቋማት ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 80.13%  ነው፡፡ በዚህ በጀት

አመት ውስጥ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ለሚገኙ ለ4783 ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ4009 ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙም 83.8% ነው፡፡ በጀት አመቱ ውስጥ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በድምሩ 201 በአካቶ ትግበራ ዙሪያ የምክክር መድረኮችን ለማካሄድ ታቅዶ በድምሩ 72 የምክክር መድረኮች በአካቶ ትግበራ አፈፃፀም ዙሪያ በየደረጃው ከሚገኙ የመንግስት ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር ውይይቶችን በማካሄድ የአካቶ ትግበራ ስራው ያለበትን ደረጃ የመገምገም ስራ ተሰርቷል፡፡

### 1.2.3.4. ወጣቶችና ስፖርት ልማት

የወጣቶችን የመደራጀት መብት ከማስጠበቅ አንጻር የተከናወኑ ተግባራትን ስንመለከት በ11 ወር 1,189,800 (ወንድ 594,900 ሴት 594,900) ወጣቶችን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 1,076,921 (ወንድ 538,461 ሴት 538,461) ወጣቶችን በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች (በሊግ፣ በማህበራት፣ በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 489,088 (ወንድ 268,077 ሴት 221,011) ወጣቶችን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 255,444 (ወንድ 167,455 ሴት 87,989) ወጣቶችን በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 41% እና 24% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ11,898 (ወንድ 5,949 ሴት 5,949) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው በማድረግ 10,769 (ወንድ 5,385 ሴት 5,384) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በልዩ ልዩ አደረጃጀት እንዲገቡ ታቅዶ 3,512 (ወንድ 1,859 ሴት 1,653) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው በማድረግ 3,866 (ወንድ 2,392 ሴት 1,474) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀት (በሊግ፣ በማህበራት፣ በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ለማረጋገጥ፤ 13,056 (ወንድ 8,705፣ ሴት 4,351) የወጣት አደረጃጀት አመራሮች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ወጣቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ 13,056 (ወንድ 8,705 ሴት 4,351) የወጣት አደረጃጀት አመራሮች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ወጣቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ ለ9,408 (ወንድ 5,825 ሴት 3,583) (72.1%) ማሳተፍ ተችሏል፡፡

ለ616,927 (ወንድ 308,464 ሴት 308,464) ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ በማድረግ 3,000,000,000 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 81,392 (ወንድ 46,325 ሴት 35,067) ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ በማድረግ 730,927,481 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም በወጣቶች ተሳትፎ ደረጃ 13% ሲሆን በመቆጠብ ደረጃ ደግሞ 24% ነው፡፡

ከዚህ ውስጥ 6,169 (ወንድ 3,085 ሴት 3,085) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች በቁጠባ እንዲሳተፉ ታቅዶ 214 (ወንድ 105 ሴት 109) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለ269,936 (ወንድ 134,968 ሴት 134,968) ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተቅዶ 41,830 (ወንድ 23,690 ሴት 18,140) ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 15% ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 2,706 (ወንድ 1,354 ሴት 1,354) አካል ጉዳተኛ ወጣቶች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ 158 (ወንድ 68 ሴት 90) አካል ጉዳተኛ ወጣቶችን የብደር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከብድር ጋር በተያያዘ በ11 ወር 3 ቢሊየን ብር በብደር ለመስጠት ታቅዶ ብር 474,070,600(16%) በብርድር መሰጠቱን ያሳያል፡፡

የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥን በተመለከተ የክረምት ወራት በጎ ፈቃድ አገ/ የአስተባባሪ ተቋም በየደረጃው ያለው አጋር ተቋማትና አደረጃጀቶች አቅደው በክልል 16(88.9%)፣ በዞን 370(90%)፣ በወረዳ ደረጃ 3400(74%) ዕቅድ አቅደው ወደ ስራ ተገብተዋል፡፡ በክልላችን 5,218,244 ወጣቶችን ወደ ንቅናቄ ለማስገባት ታቅዶ 4,304,679 (ወንድ 2,654,132፣ ሴት 1,650,547) (82.5%) ወጣቶችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም12,521,544 (ወንድ 6,260,772፣ ሴት 6,260,772) የህ/ሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 10,397,059 (ወንድ 5,629,437፣ ሴት 4,767,622) (83%) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 73 አገር አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ የማዘዉተሪያ ስፍራዎች ለመለየትና ለመገንባት ታቅዶ 25(47.2%) ተለይተዋል፡፡ በተጨማሪም 850 የጥርጊያ ሜዳዎችን ለማስፋፋት ታቅዶ 310(49%) ተስፋፍተዋል፡፡ 685 ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ህጋዊ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ ታቅዶ 272(40%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን 624 በገጠር የተሰፋፉ ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ህጋዊ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ ታቅዶ 195(31%) ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም 61 በከተማ የተስፋፉ የማዘወተሪያ ስፍራዎች ካርታና ፕላን እንዲያገኙ ማድረ ታቅዶ 77(100%) ተከናወኗል፡፡ 9 የ2ኛ ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመገንባት ታቅዶ 2(22%) ተከናወኗል፡፡ እንዲሁም 13 የ3ኛ ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመገንባት ታቅዶ 8(62%) ተከናወኗል፡፡ በተጨማሪም በዞኖች 64 ለሚገነቡ የማዘዉተሪያ ስፍራዎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 63(98%) ተከናወኗል፡፡

## 1.2.4. የመሠረተ ልማት ዘርፍ አፈጻፀም

### 1.2.4.1. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ

በዚህ ዘርፍ በ11 ወር ውስጥ 8,595,345 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርከሪዎች በድግግሞሽ ስምሪት በመስጠት 114,012,137 ህዝብ በማጓጓዝ 359,364,472 ኪሎ ሜትር የመሸፈን ስራ የተሰራ ሲሆን 45,549,357 ብር ከመናኸሪያ፣ 332,361,008 ብር ከአሽከርካሪና ተሽከርካሪ የውስጥ ገቢ መሰብሰብ ተችሏል።

በሌላ በኩል 51,643 ብቁ ለሆኑ እጩ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ /መንጃ ፈቃድ/ በመስጠት 62,520 ነባር ና አዲስ የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታደሰ ሲሆን ለ11,763 አዲስ ወደ ክልላችን የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ በማድረግ ሰሌዳና ሊብሬ የመስጠት ስራ በመስራት፣ ወንድ 62,841 ሴት 1,081 ድምር 63,922 ነባር አሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክሎ የማሽከርከር ስልጠና የተሰጠ ሲሆን 26,265 የተሽከርካሪ ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ በማካሄድ ከባድ ችግር የተገኘባቸዉ 1,624(6%)፣ ቀላልችግር 4,380 (16.7%)፣ ምንምችግር የለለባቸው 20,261(77%)፣ 2,289,903 ተሽከርካሪዎችን በመደበኛና በራዳር ቁጥጥር በማድረግ ቁጥጥር ከተደረገባቸው መካከል 91,606 አሽከርካሪዎች ጥፋተኛ ሆነዉ በመገኘታቸዉ ብር 36,894,709 ብር እንዲቀጡ ተደርጎ ገንዘቡ ወደ መንግስት ገቢ የተደረገ ሲሆን ያለ ደረጃቸው የተጭበረበረ የተሽከርካሪ ኦፕሬተር ፈቃድ ይዘው በመገኘታቸው 235 ተሽከርካሪዎች ላይ እርምጃ ተወሰዶባቸዋል። በተጨማሪም ከስምሪት ውጭ የሆኑ 2,307 ተሽከርካሪዎችን ከነዳጅ ድጎማው በአማካኝ 7 ቀን እንዲታገዱ በማድረግ ከመንግስት ወጭ ሊሆን የነበረን ብር 6,955,070 የማስቀረት ስራ የተሰራ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ስምሪት ላይ ሳይሆኑ ያለአግባብ የነዳጅ ድጎማ የወሰዱ 12 ተሽከርካሪዎች የወሰዱትን ብር 94,713 መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ ተደርጓል። በሌላ በኩል 9,568 ተሽከርካሪዎች በመጠቀም በደርሶ መልስ 430,412 የ12ኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች ከማጓጓዝ በተጨማሪ 2,023 ተሽከርካሪዎችን በመጠቀም 75,249 ህዝብ የሱዳን ተፈናቃዮች ከመተማ ወደ መሃል ሀገር የማጓጓዝ ስራ ተስርቷል።

የትራንስፖርት መሠረተ ልማቱን የተቀናጀ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ለማሳደግ በደሴ ከተማ ከአለም ባንክ በተገኘ ከብር 71.2 ሚለዮን በላይ ገንዘብ ነባሩ መናኸሪያ የመልሶ ግንባታ ስራ100% ለማጠናቀቅ በተቀደው መሰረት በአሁኑ ወቅት የግንባታዉ ደረጃ 100% መድረሱን ያመለክታል። በሌላ በኩል በዚሁ ከተማ ከአለም ባንክ በተገኘ ከብር 120 ሚለዮን ብር በላይ ድጋፍ በ2013 በጀት

የተጀመረ መናሐሪያ በአሁኑ ጊዜ ግንባታዉ 96% ላይ ደርሷል፡፡በአለም ባንክ እና በከምቦልቻ ከተማ አስተዳደር የበጀት መቀናጀ ከብር 151,840,744.9 ብር ተመድቦለት በ2008 ዓ.ም ግንባታዉ የተጀመረዉ የከምቦልቻ ከተማ መናህሪያ ግንባታዉ ተጠናቆ ተመርቋል፡፡

ነባር መናኸሪያዎችን ማስፋፋት፣ ማጠናከርና መጠገንን በተመለከተ፡- የባ/ዳር ነባሩ መናኸሪያ አጥር ግንባታ ከአንድ የህንጻ ስራ ተቋራጭ ጋር በብር 21,187,557.15 የዉል ስምምነት በተፈጸመዉ መሰረት ግንባታዉ ተጠናቆ ጊዚያዊ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ ደረጃ ሶስት 12 አዲስ መናኸሪያ እንዲገነባ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ሶስት አዲስ መናህሪያዎችን እንዲገነባ እቅድ የተያዘዉን በተመለከተ በደቡብ ወሎ ዞን ለገሂዳ ወረዳ ሽኮች መናህሪያ ከመዘጋጃ ቤት ብር 110,000 ከህዝብ መዋጮ ብር 285,120 በድምሩ 385,120 ተመድቦ የመጸዳጃ ቤት፤የትኬት ቢሮ፣የስምሪት ቢሮ፣ የጥበቃ ቤት እና አጥር የተሟላለት መናህሪያ ተገንብቶ ተጠናቋል፡፡

በክልላችን የሚገኙትን የትራፊክ ኮምፕሌክስ ቁጥር ለማሳደግ በ2015 በጀት አመት መጨረሻ የኮሶበር ከተማ ትራፊክ ኮምፕሌክ አጠቃላይ ግንባታ ከአሸከርካሪ ተሸከርካሪ የዉስጥ ገቢ በብር 190,512,686.86 ከአማራ ህንጻ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር የዉል ስምምነት ተፈጽሞ እና ለድርጅቱ 30% የቅደመ ክፍያ ተከፍሎት ወደ ግንባታ የገባ ሲሆን በዉል ስምምነቱ ከተያዘዉ ጊዜ አኳያ እስከዚህ ወር ድረስ ከአጠቃላይ ግንባታዉ ከ63.4% በላይ መድረስ የሚገባዉ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ከአጠቃላይ ግንባታዉ 10.02 % ብቻ እንደተከናወነ ያመለክታል፡፡

የ3 ከተሞች ትራፊክ ኮምፕሌክስ የአጥር፣ የጥበቃ ቤት እና መዝግብ ቤት ግንባታ ከአሽከርካሪ ተሽከርካሪ የዉስጥ ገቢ ብር 99,836,056.65 ተመድቦ ከሞገስ አበጀ የህንጻ ተቋራጭ ጋር የዉል ስምምነት በመፈጸም እና ለድርጅቱ 30% ቅድመ ክፍያ ተከፍሎት ድርጅቱ ወደ ግንባታ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ የሶስቱ ፕሮጀክቶች አማካኝ አፈጻጸም 89% ደርሷል ( የባህር ዳር ትራፊክ ኮምፕሌክስ 95%፤ የጎንደር ትራፊክ ኮምፕሌክስ 92% እና የደብረ ማርቆስ ትራፊክ ኮምፕሌክስ 80%) ተከናዉኖል፡፡

የህዝብ፤ የከተማ፤ የጭነትና የውሀ ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋትና ተደራሽነትን ማሳደግ በዓመቱ 125 በ11ወሩ112 የህዝብ ትራንስፖርት አዲስ የመንገድ መስመሮች እንዲከፈቱ ለማድረግ ታቅዶ ክንውን 36 (32%) ከዓመቱ 29% ማከናወን ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት በክልሉ ባለው ወቀታዊ ችግር ምክንያት ነው፣እንዲሁም

በዓመቱ 2401 በ11ወሩ 2401 የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ስምሪት መስመሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ታቅዶ ክንውን 2659 (›100%) ሲሆን ከዓመቱ 100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡በተጨማሪ በዓመቱ11,047 በ11ወሩ 11,047 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች አቅርቦት መርሃ ግብር አፅድቀው እንዲሰሩ ማድረግ ታቅዶ ክንውን 10,442(75%) ማከናወን ተችሏል፡፡

በዓመቱ 11,714 በ11ወሩ 11,714 የአነስተኛ፣ መለሰተኛ፣ ከፍተኛ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተሽከርካሪዎችን በማቅረብ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ታቅዶ 9,134 (78%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ 11,923,363 በ11ወሩ 11,1045,23 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርከሪዎች በድግግሞሽ ስምሪት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 8,595,345 (77%) ሲሆን ከዓመቱ 71% ነው፡፡ በተጨማሪም በዓመቱ 189,922,611 በ11ወሩ 175,285,045 በህዝብ ትራንስፖርት ህዝብ በማጓጓዝ ታቅዶ ክንውን 114,012,137(65%) ሲሆን ከዓመቱ 60% የተፈጸመ ሲሆን በዓመቱ 659,897,830 በ11ወሩ 604,906,345 በህዝብ ትራንስፖርት ኪሎ ሜትር መሸፈን ታቅዶ ክንውን 359,364,472 ኪሎ ሜትር (59%) በመሸፈን ከዓመቱ 54% ነው፣፡የመናኸሪያዎችን ስታዳንዳርድ ማስከበር 85% ለማድረስ ታቅዶ ክንውን 65% ማድረስ ተችሏል ነገርግን በወቅታዊ ችግር ምክንያት በአካል ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ለ162 የውሃ ትራንስፖርት መረጃዎችን ማሰባሰብ በእቅድ ተይዞ ክንውን 159 የውሃ ትራንስፖርት መረጃዎችን ማሰባሰብ ተችሏል አፈጻጸሙ 98% ደርሷል፡፡

ብቃቱ የተረጋገጠ ተሽከርካሪና አሽከርካሪ በማፍራት በክልሉ እየደረሰ ያለዉን የትራፊክ አደጋ በ26% ለመቀነስ በዓመቱ 75,816 በ11 ወሩ 69,498 እጩ አሽከርካሪዎች የንድፈ ሃሳብ ፈተና እና በዓመቱ 75,816 በ11 ወሩ 69,498 የተግባር ፈተና ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 64,992 (94%) የንድፈ ሃሳብ ፈተና 58,811 (85%) የተግባር ፈተና የተሰጠ ሲሆን ከዓመቱ ደግሞ 86% ና 78% ነው፡፡ እንዲሁም በዓመቱ 62,040 በ11 ወሩ 57,053 ብቁ ለሆኑ እጩ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ /መንጃ ፈቃድ/ መስጠት ታቅዶ ክንውን 51,643 ሲሆን አፈፃጸሙ 91% ከዓመቱ 83% ነው ፡፡ በተጨማሪም በዓመቱ 69,700 በ11 ወሩ 63,880 ለአዲስ የአሽከርሪወች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ ክንዉን 51,733 (81%) የታደሰ ሲሆን አፈፃጸሙ ከዓመቱ 74% ነው ፡፡ሌላው በዓመቱ 15,504 በ11 ወሩ 14,212 ለነባር የአሽከርሪወች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ ታቅዶ ክንዉን 10,787 (76%) የታደሰ ሲሆን ከዓመቱ 70% ነው፡፡ እንደዚሁም በዓመቱ 3,938

በ11 ወሩ 3,610 የመንጃ ፈቃድ ቅጅ/ግልባጭ ለመስጠት ታቅዶ ክንዉን 3,064 (85%) ከዓመቱ 78% ነው፡፡

በሌላ በኩል በ2016 በጀት ዓመት በ11 ወር የተከሰተውን የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር በማነፃፀር በ10,000 ተሽከርካሪ 26% መቀነስን በተመለከተ፤በ2015 በ11 ወሩ በ10,000 ተሽ/ሪ የደረሰ አደጋ የሞት 61 ሰዎች እና ጠቅላላ የደረሰ አደጋ 131 ሲሆን በ2016 11 ወሩ ድረስ የደረሰ የሞት አደጋ 27(34 በመቀነስ) እንዲሁም ጠቅላላ የደረሰ አደጋ 61(70 በመቀነስ) ሲሆን የሰው ሞት አደጋ 56% በመቀነስ እንዲሁም በጠቅላላ የደረሰ አደጋ 53% በመቀነስ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በንብረት ውድመት ረገድ በ2015 ተመሳሳይ ወቅት ብር 7.15 ሚሊዮን የሚያወጣ ሀብት የወደመ ሲሆን በ2016 11 ወሩ ድረስ ብር 3.89ሚሊዮን(በ3.25 ሚሊዮን ብር በመቀነስ) የተመዘገበ መሆኑን ያሳያል፡፡ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከእቅዱ አንጻር ሲወሰድ የሰው ሞት እና ጉዳት ከ100% በላይ ከታሰበው በታች መቀነሱን ያመለክታል፡፡

### 1.2.4.2. መንገድ

ከመንገድ ስራ አንጻር አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ ሽፋን (Road Network Coverage) በ2015 ከደረሰበት 31,392.89 ኪ/ሜ በ2016 ወደ 32,732.28 ኪ/ሜ ከፍ የማድረግ ግብን ለማሳካት በ2016 በጀት ዓመት በጠቅላላው በሁሉም የመንገድ ግንባታ ዘርፎች 1339.39 ኪ/ሜ የመንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ ባለፉት 11 ወራት ዉስጥ 808.6 ኪ/ሜ (61%) የጠጠር፣ ጌጠኛ እና ጥርጊያ መንገድ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 107.13 ኪ/ሜ (30%) የአስፓልት መንገድ ግንባታ ድርሻ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ የበጀት ዓመቱን የመንገድ ሽፋን ግብን ለማሳካት የድልድይ ፕሮጀክቶች ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ፡- በበጀት ዓመቱ የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው 63 ስትራክቸሮች በጀት ተይዞላቸዉ ለመገንባት ታቅዶ 39 የኮንክሪት፣ 24 ተንጠልጣይ የእግረኛ ድልድዮች በድምሩ 63 (100%) ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

የክልሉን የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን በመንገድ ተደራሽነትን ሽፋን ለማሳደግ በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት የክልሉን የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን በመንገድ ተደራሽነትን ሽፋን በ2015 ዓ/ም ከተደረሰበት 77.47% (2,621 ቀበሌዎች) በ2016 ወደ 80.13% (2,648 ቀበሌዎች) ለማሣደግ እንዲቻል በበጀት ዓመቱ 363 ኪ/ሜ መንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ እስከ 11 ወሩ ድረስ 330.5 ኪ/ሜ መንገድ በመገንባት እና 91% በመፈፀም 109 ቀበሌዎች ተገናኝተዋል፡፡

በዩራፕ፣ በወረዳ ገጠር መንገድና ህብረተሰብ ተሳትፎ የተገነቡ የክረምት ከበጋ አገልግሎት የሚሰጡ በወ ምክር ቤት በጀትና በህብረተሰቡ ተሳትፎ በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 7,880 ኪ..ሜ በ11 ወሩ 7,679 ኪ/ሜ (በማሽን 2,028 ኪ/ሜ፣ በሰው ሀይል 5,651 ኪ/ሜ) መንገድ ለመጠገን ታቅዶ በ11 ወር ዉስጥ 6,325 ኪ/ሜ (82.4%) መንገድ መጠገን የተቻለ ሲሆን በማሽን 1,853 ኪ..ሜ፣ በሰው ሃይል 4,472 ኪ..ሜ ተጠግኗል፡፡ በተመሳሳይ በፌደራል መንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ የመንገድ ጥገና በበጀት ዓመቱ በወቅታዊና መደበኛ ጥገና 4,560.63 ኪ/ሜ ለመጠገን ታቅዶ እስከ 11 ወሩ 4,404.93 ኪ/ሜ (96.55%) ተጠግነዋል፡፡ በተጨማሪም የመንገድ ፈንድ ሃብት አጠቃቀም ብር 812,955,051 የተመደበ ሲሆን ብር 782,593,551.63 (96.27%) ጥቅም ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎና ሃብት ማሰባሰብ በበጀት ዓመቱ ብር 793,859,769 ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 583,491,248 በጥሬ ገንዘብ በመሰብሰብ የተቻለ ሲሆን እንዲሁም ህብረተሰቡ በጉልበት ያደረገው ተሳትፎ በገንዘብ ሲተመን ብር 107,328,000 አስተዋጾ አድርጓል፡፡ በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር (ERA) ደረጃ ተይዘው ከነበሩ 61 ፕሮጀክቶች በክልላችን የሚገነቡ የአስፋልት መንገዶችን በተመለከተ በ2016 በጀት ዓመት ለ52 ፕሮጀክቶች በጀት ተይዞላቸዉ 415.38 ኪ/ሜ ለማጠናቀቅ እና  በ11 ወራት 318.59 ኪ/ሜ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የ32 ፕሮጀክቶች 101.78 ኪ/ሜ (30%) አስፓልት መንገድ ተገንብቷል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ሲል የተገነቡ የአስፓልት መንገዶች ጥገናን በተመለከተ በ39 የጥገና ፕሮጀክቶች በ2016 በጀት ዓመት 3,664.94 ኪ/ሜ፣ እንዲሁም በ11 ወር 3,503.61 ኪ/ሜ ለመጠገን ታቅዶ 2,413.06 ኪ/ሜ (69%) መንገድ መጠገን ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ ከ39 ፕሮጀክቶች ውስጥ በ33 የመንገድ ግንባታና 6 የስትራክቸር ግንባታ ፕሮጀክቶች አማካይነት 93.01 ኪ/ሜ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ እስከ 11 ወሩ 80.46 ኪ/ሜ (85%) ተከናዉኗል፡፡

የመንገድ ርክክብ ከ2004 ጀምሮ ተገንብተው የተሟላ ስትራክቸር ሳይገነባላቸው ከታለፉት በበጀት ዓመቱ 187 ኪ/ሜ እስከ 11 ወሩ  108 ኪ/ሜ የመንገድ ርክክብ  ለማካሄድ ታቅዶ እስከ 11 ወሩ 90.2 ኪ..ሜ (83.5%)  የመንገድ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ ከባለፈዉ በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተፈጸመዉ 265.54 ኪ/ሜ ጋር ሲነጻጸር በ203 ኪ/ሜ በማነስ ያሳያል፡፡

### 1.2.4.3. ውሃና ኢነርጅ

በበጀት ዓመቱ ልዩ ልዩ 1,200 አነስተኛ ውሃ ተቋማት ለመገንባት ታቅዶ እስከ 11 ወሩ ድረስ 485 ዉሃ ተቋማት በመገንባት የዕቅዱን (53%)  ማከናወን ተችሏል፡፡ የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በበጀት ዓመቱ የ2% የሽፋን እድገት በበመጨመር ከ73.64%

ወደ 75.64% ለማድረስ ታቅዶ እስከ 11 ወሩ ድረስ 1.7 % በማሳደግ 75.34 % ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 457,540 ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 177,017 (39%) ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የገጠር ንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት ሽፋን የ2% እድገት በመጨመር 73.85 ወደ 75.85 % ለማሳደግ ታቅዶ 1.2% በማከናወን ሽፋኑን (75.05%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን 5846 ህዝብ ማስጠቀም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተረሰበት 72.17% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት የ2 % ሽፋን እድገት በመጨመር የከተማ ንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ወደ 74.17 % ለማሳደግ ታቅዶ 3.1% ሽፋን እድገት በመጨመር 75..27% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 171,171 (የዕቅዱ ከ100% በላይ) ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 10,000 ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ የተለያዩ የዉሀ ተቋማት ጥገና ለማከናወን ታቅዶ እስከ 11 ወሩ 9,661 የተለያዩ ተቋማት የተጠገኑ ሲሆን ቀላል ጥገና 5,200 (96%)፣ መካከለኛ 3,000 (93.75%) እና ከባድ 1,300 (92.85%) ተከናዉኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ በከተማ ያለዉን የዉሀ ብክነት አሁን ካለበት 22.05% ወደ 21.53% በመቀነስ ንጽህናዉን የጠበቀ የመጠጥ ዉሀ ለህብረተሰቦ ለማድረስ ታቅዶ ወደ 22% ማድረስ ተችሏል፡፡ የዉሀ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ ከ11.45% ወደ 11.35% ለመቀነስ ታቅዶ የብልሽት ምጣኔዉን በ0.12 በመቶ በመቀነስ ወደ11.23% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ የሃይል አቅርቦ 2015 ከደረሰበት 6.6 ሜጋዋት ላይ 0.739 ሜጋዋት በመጨመር ወደ 7.39 ሜጋዋት ለማሳደግ ታቅዶ 7.339 ሜጋዋት ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም እስከ 11 ወሩ 99% ድርሷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 92,000 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በሰለጠኑ አምራቾች ለማስመረትና ለማሰራጨት ታቅዶ እስከ 11 ወሩ 69,334 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በሰለጠኑ አምራቾች ማስመረትና ማሰራጨት ተችሏል፡፡

የውሃ አገልግሎቶች የውሃ ምርትና ስርጭት በጀት አመቱ በዉሀ አገልግሎቶች 70,260,870 ሜ3 ውሃ ለማምረት ታቅዶ ዉሀ 59,046,959 ሜ3 (84.03%) ማምረት የተቻለ ሲሆን ከተመረተዉ ዉስጥ 46,050,722 ሜ3 (78%) ማሰራጨት ተችላል፡፡

### 1.2.4.4. መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት

ከመስኖና ቆላማ ስራዎች አንጻር ሲሰሩ ከነበሩ የበጀት አመቱ ተግባራት መካከል የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጥናትና ዲዛይን ዘርፍ በአማካሪ ድርጅቶች የጥናት እና ዲዛይን ሥራቸው በ2014 በጀት ዓመትና በፊት የጥናትና ዲዛይን ሥራቸው

በአማካሪዎች ተጀምሮ ያደሩ 15,060 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ እና ወንድ 18,863 ሴት 3,978 ድምር 22,841 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 21 መካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን በ2015 በጀት ዓመት ከደረሱበት አማካይ 64.1% አፈፃፀም በመነሳት 34.5% በመፈጸም 98.6% ለማድረስ እና 13 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 26.2% በማከናወን 72.9% መፈጸም የተቻለ ሲሆን  አጠቃላይ 90.3% ማድረስ  የተቻለ ሲሆን 1050 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 2 ፕሮጀክቶችne ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በመንግስት አማካሪ ድርጅቶች በ2015 በጀት ዓመት ተጀምረው ያደሩና በተለያየ አፈጻጸም ላይ የሚገኙ የማልማት አቅማቸው 71,550.40 ሄ/ር የሆነና 239,5867 ህዝብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 49 መካከለኛ ፕሮጀክቶችን ከደረሱበት አማካኝ አፈፃጸም 30.4% በመነሳት 44.61% በመፈጸም አማካኝ አፈጻጸማቸውን 75% ለማድረስ ታቅዶ 31% በመፈፀም 61.4% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 5,662ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 11 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 6,412 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 13 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በቢሮው አቅም በ2015 በጀት ዓመት ተጀምረው ያደሩና በተለያዩ አፈጻጸም ላይ የሚገኙ የማልማት አቅማቸው 672 ሄ/ር የሆነና 1,938 ህዝብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 8 ነባር ፕሮጀክቶችን በ2015 በጀት ዓመት ከደረሱበት 15% አማካኝ አፈጻጸም በመነሳት 60% በመፈጸም 75% ለማድረስ ታቅዶ 33.75% በመፈጸም 48.75% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ 350ሄ/ር የሚያለሙ 3 ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ 250ሄ/ር የሚያለሙ 2 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

በ2016 በዞንና ወረዳዎች ደረጃ የማልማት አቅማቸው 732.10 ሄ/ር የሆነና 1,894 የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የ15 አዲስ አነስተኛ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 80% መፈጸም የተቻለ ሲሆን 512 ሄ/ር ማልማት የሚችሉና 1,325 የህብረተሰብ ክፍሎች የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 12 ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ ማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን በምዕ/ጎንደር የሚገኙ 3 ፕሮጀክቶች ምንም ስራ እንዳልጀመሩ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም 26,204.9 ሄ/ር የሚያለሙና ወንድ 30,529 ሴት 8,438 ድምር 38,967 የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 214 ፕሮጀክቶች ግንባታቸውን ለማከናወን ታቅዶ አብዛኛው ፕሮጀክቶች የፀጥታ ችግር በመኖሩ 125 ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ማስገባት የተቻለ ሲሆን 3,680.37 ሄ/ር የማልማት አቅምና 9,027 አባወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 51 (23.8%) ፕሮጀክቶች (45 አነስተኛ እና 6 መካከለኛ) ግንባታቸውን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በፊት የግንባታ ውል ከተያዘላቸው

ፕሮጀክቶች ውስጥ ተቋራጮች በውላቸው መሰረት መፈጸም ባለመቻላቸው 1,070.55 ሄ/ር ማልማት የሚችሉና 2,378 አበዋራዎችን በመስኖ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የ18 ፕሮጀክቶች ውል የተቋረጠ ሲሆን 7 ፕሮጀክቶች እንደገና ውል ተወስዶ ወደ ግንባታ የገቡ ሲሆን 2 ፕሮጀክቶች በጫረታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

የመስኖ ልማትን በቴክኖሎጂ ለማገዝ 3,100 የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ዓመት በብር 170,190,430.67 ግዥ በመፈጸምና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለዞኖች በመደልደል 3,100 ወደ ዞኖች እና ወረዳዎች ተንጉዘዋል፡፡ በተጨማሪም 1,460 ሄ/ር የሚያለሙና 1432 የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 22 የመስኖ አውታሮችን ለመጠገን ታቅዶ 711 ሄ/ር የሚያለሙና ወንድ 564 ሴት 151 ድምር 715 የህ/ሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ 15 (68.2%) የመስኖ አውታሮች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡

በግብርና እድገት ፕሮግራም (ኤጅፒ) ፕሮጀክቶች 2,230.5 ሄ/ር ማልማት የሚችሉና 3,491 የህ/ሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ 8 ነባር ፕሮጀክቶች ግንባታ በ2015 ዓ.ም ከደረሱበት 73.12% በመነሳት 100% ለማድረስ ታቅዶ 91.2% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 4 ፕሮጀክቶችን ግንባታቸውን እንዲጠናቀቁ በማድረግ ለልማት ዝግጁ ተደርጓል፡፡ ግንባታቸው በክረምቱ ወቅት የቆሙና ፈጥነው ወደ ግንባታ ለመግባት በተለያየ ምክንያት የዘገዩ አባይ 3 እና የጎፎለፎይ ፕሮጀክቶች እንዲሁም ውላቸው ተቋርጠው የነበሩ 2 መስኖ ፕሮጀክቶችን (በርበራ 1 እና ዳንዲኒ) ወደ ግንባታ እንዲገቡ በማድረግ በጥሩ የግንባታ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በግንባታ ላይ ከነበሩ 8 ፕሮጀክቶች ውስጥ 530.5 ሄ/ር ማልማት የሚችሉና 1232 የህ/ሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 5 ፕሮጀክቶችን ተጠናቀው ለልማት ዝግጁ ሆነዋል፡፡

## 1.2.5. የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ አፈጻፀም

### 1.2.5.1. ሠላምና ፀጥታ

የአጎራባች ክልል የህዝብ ለህዝብና የአመራር ለአመራር ግኙነት በሚመለከት በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች መካከል በተለይ ከወል መሬት አጠቃቀም፣ ከአስተዳደር ወሰንና ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶችን ቀድሞ ለመከላከል በየደረጃው የአመራር ለአመራር ግንኙነት ተካሂዷል፡፡ በ11 ወሩ የኦሮሞ ብሄረሰብና የሰሜን ሸዋ ዞኖች ከአፋር ክልል ተጎራባች ዞን ጋር በዞን ደረጃ በ4 መድረክ 60 አመራር የተሳተፉበት የአመራር ለአመራር ግንኙነት

ተካሂዷል፡፡ የአጎራባች ክልል ወረዳዎች ግንኙነትን በተመለከተ በ32 መድረክ 427 አመራሮች የተሳተፉበት የአመራር ለአመራር ግንኙነት ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ በቀበሌ ደረጃ በ11 ወሩ ውስጥ በ35 መድረክ 1,449 አመራርና ጥምር የሰላም ኮሚቴ አባላት ግንኙነት አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ ክልሎች ትኩረታቸውን ወደ ወቅታዊ ጉዳይ ትኩረት ያደረጉ ቢሆንም በቀጣይም ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያለውን የአመራር ለአመራር ግንኙነቱ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በጋራ ተግባራትን እየገመገሙና የቀጣይ አቅጣጫዎችን እያስቀመጡ በተጎራባች ክልል ህዝቦች መካከል ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን /ግጭቶችን/ጥፋት ሳይደርስ ቀድሞ መከላከል ይጠይቃል፡፡ በሌላ በኩል ከአጎራባች ክልሎች ነዋሪዎች ጋር የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ከአፋር ክልል ተጎራባች ወረዳዎችና ቀበሌዎች ጋር በ69 መድረክ 16,439 ህዝብ የተሳተፈበት ኮንፈረንስ ተካሂዷል፡፡ በተጎራባች ህዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት ለመመስረት ከሚያስችሉ ተግባራት ውስጥ የተዘረፉ ንብረቶችን ማስመለስና ካሳ ማስከፈል አንዱ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በ11 ወሩ ውስጥ ከአማራ ወደ ሌሎች ክልሎች ከገቡ 1357 እንስሳት ዉስጥ 677 ማስመለስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከሌሎች ክልሎች ወደ አማራ ከገቡ 307 እንስሳት ዉስጥ 259 የተለያዩ እንስሳትን መመለስ ተችሏል፡፡

ክልሉ ውስጥ የአመራር ለአመራርና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በሚመለከት በበጀት አመቱ የአመራር ለአመራር ግንኙነት፤ ከኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ከአፋር ክልል ተጎራባች ዞን ጋር በዞን፣በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በ215 መድረክ 7,636 አመራሮች የተሳተፉበት የአመራር ለአመራር ግንኙነት ተደርጓል፡፡በዚህም አማራ ክልል ለአፋር ክልል ተጎራባች ቀበሌዎች የተዘረፉ 338 የተለያዩ እንስሳት ሲመለሱ ከአፋር ክልል ከተዘረፉ ንብረቶች ዉስጥ 6 የተለያዩ እንስሳትና 4 ክላሽ ለአማራ ክልል ለባቲ ዙሪያ ወረዳ ማስመለስ ተችሏል፡፡

የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት፡ በዓመቱ ከሚጠቀሱት ከኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር፣ሰሜን ጎንደር፣ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ እና ዋግኽምራ ዞኖች በተገኘው መረጃ መሰረት በ111 መድረክ 155,963 ህዝብ የተሳተፈበት ኮንፈረንስ ተካሂዷል፡፡ በተመሳሳይ ግጭት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሚመለከት በ11 ወሩ በዋግኽሞራ ብሄረሰብ ዞን፣ ሰሜን ጎንደር እና ሰሜን ወሎ ዞኖች በወል መሬት አጠቃቀም፣ በድንበር ይገባኛልና በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ዙሪያ 75 ግጭት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮች የተከሰቱ ሲሆን በአመራሩ፣ ባለሙያው፣ በሀገር ሽማግሌዎችና በሰላም ኮሚቴዎች ተሳትፎ 66 የመልካም

አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የተቻለ ሲሆን ቀሪዎች 9 ግጭት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት በሂደት ላይ ነው፡፡

የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ተግባራት በሚመለከት በክልሉ ከተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ጋር በተያያዘ በየደረጃው የሚገኘው ባለሙያ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ያልገባ በመሆኑ ምክንያት የተሟላ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ በየዕለቱ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የዘጠኝ ወሩ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ መረጃ ልውውጥ ከቀበሌ ወደ ወረዳ 5.9%፣ ከወረዳ ወደ ዞን 11.2%፣ ከዞን ወደ ክልል 24.1% መሆኑን ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የተደገፈ አለመሆኑ፣የቀበሌ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ፎካል ፐርሰኖች የግጭት መረጃ አሰባሰብና አለላክ ላይ የአቅም ክፍተት መኖሩ፣የሚላኩ መረጃዎች የመዘግየትና የጥራት መጓደል ያለባቸዉ መሆኑና ሌሎች ክፍተቶች በመኖራቸዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የባለሙያዉን አቅም መገንባትና ዘርፉነው በቴክኖሎጅ ማጎልበት የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋንና የሰው ሃይል ስምሪት በሚመለከት በ2016 በጀት በ11 ወራት የኮ/ፖሊሲንግ የቀበሌ ሽፋንን 80% ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም አሁን ካለው ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት በሁሉም ቀበሌና ሴንተሮች የነበሩ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰሮች በወረዳዎች እና በዋና ጣቢያዎች ላይ በአንድ ሆነው የተፈጠረዉን የሰላም ችግር ለመፍታት በጋራ እየሰሩ በመሆናቸው የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ስራ እየተሰራ አይደለም፡፡

አጠቃላይ እና ዋና ዋና ወንጀል በሚመለከት በ11 ወር የስራ አፈፃፀም  በክልሉ ዉስጥ አጠቃላይ ወንጀል 8439 ተፈጽሟል፡፡ሆኖም በክልሉ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት አብዛኛው ዞን የመረጃ ችግር ስለአለ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ዋና ዋና ወንጀል 3643 ተፈጽሟል፡፡የጠቅላላ ወንጀል አፈፃፀም ከህዝብ ቁጥር ብዛት ጥምርታ አንፃር ተደራሽ ግባችን  በ1,000 ሠዎች መካከል በገጠር 1.42 እና በከተማ 4.7 እና ዋና ዋና ወንጀል በገጠር ከ0.47 እና በከተማ ከ1.66 በላይ ወንጀል እንዳይፈፀም ለመከላከል የታቀደ ሲሆን በጠቅላላ ወንጀል በ1000 ህዝብ መካከል በገጠር 1.77 በከተማ 8.46 የተፈፀመ ሲሆን በዋና ዋና ወንጀል ደግሞ በገጠር 0.94 በከተማ 3.08 ተፈፅሟል፡፡

አጠቃላይ ምርመራ የማጣራት አቅምን በሚመለከት በ11 ወር አፈፃፀም  ዉስጥ ጠቅላላ የማጣራት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ ከቀረበዉ 9150 ክስ ዉስጥ 8100 ተጣርቶ ለአቃቢ ህግ የተላከ፣1005 በፖሊስ ላይ ያለ እና 32 እና 13 ክስ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ሐ ለተጨማሪ ምርመራ ከተመለሱ 95 መዝገቦች  በፖሊስ እጅ የሚገኙ በመሆኑ አፈፃፀሙ

88.83% ነዉ፡፡ ከእቅድ አንፃር በ1.17% የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የመንግስት ክስ የማጣራት አቅም በ11ወሩ አፈፃፀም የመንግስት ክስን 88% ለማጣራት ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከቀረበዉ 6875 የመንግስት ክስ ዉስጥ 5994 ተጣርቶ ለዐቃቢ ህግ የተላከ፤ 879 በፖሊስ እጅ ያለ እና 8 የቋረጠ ሲሆን አፈፃጸሙ87.1% ነዉ፡፡ አፈፃፀሙ ከእቅድ አንፃር በ0.9% ከእቅድ በታች መፈፀሙን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ ምርመራ ጥራትና የማጣራት አቅም በሚመለከት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታትና ፍትሃዊ የምርመራ ሥርዓትን ለማስፈን የሚቀርቡ ክሶችን የምርመራ ጥራትን ማሳድግ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሆኖ በመወሰዱ የምርመራ ጥራትን 99% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃጸማችን 99.21% ላይ ይገኛል፡፡

የትራፊክ አደጋ ምርመራ አቅም ማሳደግ በ11 ወር አፈፃፀም የትራፊክ ምርመራ የማጣራት አቅምን 90% ለማድረስ ታቅዶ 752 የትራፊክ አዳጋ ክስ ውስጥ 443 ተጣርቶ ለአቃቢ ህግ የተላከ ሲሆን በፖሊስ እጅ ያለ 257 እና 52 ክስ የተቋረጠ ሲሆን አፈፃፀሙ 59% ላይ ይገኛል፡፡

የሙስና የወንጀል ምርመራ አፈፃጸምን በሚመለከት በ11 ወር ውስጥ በአጠቃላይ ከክልል እስከ ወረዳ ወንድ 685 ሴት 53 በድምሩ 738 በሆኑ ጠቋሚዎች 992 የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች የቀረቡ ሲሆን ከተመዘገቡት 992 የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች መካከል 820 የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ተለይተው ምርመራ ሊያስጀምሩ የሚያስችሉ ሁነው በመገኘታቸው እንዲጣሩ ተወስኗል፡፡ ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልጋቸዉ 23 ሲሆኑ 3 በአስተዳደራዊ ሁኔታ ተፈተዋል፡፡ 125 የአመራሩን ዉሳኔ የሚጠብቁ ናቸዉ፡፡ ከቀረቡት 737 ጥቆማዎች መካከል የጥቆማው አቀራረብ በተመለከተ በአካል በመቅረብ የቀረበ ጥቆማ ብዛት 436 ከመስሪያ ቤት በፖስታ 223 በስልክ 78 ጥቆማና ክሶች መቅረብ ችለዋል፡፡ ምርመራቸው እንዲጣሩ ውሳኔ ካረፈባቸው 854 የሙስና ወንጀሎች መካከል 64 በክልል መርማሪ እየተጣራ ያለ፤4 በዞን መርማሪ የተጣራ ፤ 16 በወረዳ መርማሪ፣ 4 በዞን መርማሪና ዐ/ህግ በጋራ የተጣራ፣16 በወረዳ መርማሪና በዞን መርማሪ ሊጣራ ችሏል፡፡ እንዲጣሩ ዉሳኔ ካረፈባቸዉ 820 የሙስና ወንጀሎች በተጠርጣሪነት ወንድ 1342 ሴት 187 በድምሩ 1063 ተመዝግቧል፡፡

በእጅ ከፍንጅ/RTD/ የተጣሩ ክሶች፡ በእጅ ከፍንጅ የተያዙ ክሶችን 100% ለማጣራት ታቅዶ በእጅ ከፍንጅ መጣራት ከሚችሉት 912 ክሶች መካከል 887 ክሶች ተጣርተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 25 ክሶች በተለያዩ ምክንያቶቸ ተጣርተው ባለመቅረባቸው አፈጻጸሙ 97.25% ነው፡፡

የተከሰተ የትራፊክ አደጋ ስርጭትን በሚመለከት ከግንዛቤ እጥረትና ቁጥጥር ማነስ ጋር በተያያዘ ሲደርስ የነበረውን የትራፊክ አደጋ በ20% ለመቀነስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት የቁጥጥር ስርዓቱንና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራው ተጠናክሮ የተሠራ ቢሆንም 752 የትራፊክ አደጋ ደርሷል፡፡ በአጠቃላይ በአደጋው ወንድ 635 ሴት 178 በድምር 813 ሰዎች ጉዳት ከመድረሱም በተጨማሪም ብር 75,779,511.15 የሚገመት ንብረት ወድሟል፡፡

ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝዉዉርን መግታት በሚመለከት፡-በበጀት ዓመቱ የተጠኑ ህገ ወጥ ትጥቆችንና አዟሪዎችን 100% ወደ ህግ የማቅረብ ስራ ለመስራት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ 1 ስናይፐር፣ 240 ልዩ ልዩ መሳሪያ፣ 599 ልዩ ልዩ ሽጉጥ፣ 50 ቦንብ፣ 170 የክላሽ ካዝና፣1 የሞርተር ቅምቡላ እና 42276 ጥይት ማስወረድ ተችሏል፡፡

### 1.2.5.2. ፍትህ

ንጹህንን በመጠበቅ እና ወንጀለኞችን በማስቀጣት የሕግ የበላይነት ማስከበርን በሚመለከት በቀጥታ ክስ ለዐቃቤ ህግ የቀረበ ጉዳይ በ11 ወሩ ከቢሮ እስከ ወረዳ በሙስና፣ መደበኛ እና ኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች በድምሩ 13,772 መዛግብት ለዐቃቢ ህግ የቀረቡ ሲሆን ከቀረቡት ውስጥ 13,397(97.28%) መዛግብት በዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን 375 መዛግብት በዐቃቤ ህግ እጅ የሚገኙ ናቸው፡፡

በቀጥታ ክስ የፍርድ ቤት ክርክር በ11 ወሩ ከቢሮ እስከ ወረዳ በሙስና፣ በመደበኛ እና ኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች 15,671 መዛግብት ለፍ/ቤት የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 6,863 መዛግብት ውጤት የሚለኩ ውሳኔዎች ሰጥተዋል:: ከእነዚህም በ5,992 መዛግብት ላይ ጥፋተኛ ያሰኘ ሲሆን 871 መዛግብት ላይ ደግሞ ተከሳሾች በነጻ ተሰናብተዋል፡፡ የማስቀጣት ምጣኔን 95.6 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 87.31% ማድረስ ተችሏል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት የማስቀጣት አቅም 91.53 በመቶ ጋር ሲታይ በማነስ ያሳያል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የአቃቤ ህግ የክስ ጥራት ችግር፣ የክርክር ብቃት ማነስ፣ የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መዛባትና ምስክሮች ቃል መለወጥ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ቀሪ ወር በትኩረት መስራት ይገባል፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ 11 ወራት ውስጥ ለፍርድ ቤት ከቀረቡ 15,671 መዛግብት ውስጥ ተከሳሽ ባለመቅረባቸውና ምስክር ወይም ማስረጃ ባለመቅረቡ የተዘጉ መዛግብት ቁጥር 2,460 ነው፡፡ የማቋረጥ ምጣኔ እቅድ 3.5 በመቶ ሲሆን ክንዉኑ 15.7%ነዉ፡፡ በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ከነበረዉ 11.08 በመቶ ከነበረዉ አፈጻጽም በመጨመር አሳይቷ፡፡ ለዚህ ችግር ዋናዉ ምክንያት በወቅታዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት ፖሊስ ተከሳሽንና ምስክርን ማቅረብ እንዳልቻለ እየተራጋገጠ ፍርድ ቤቶች ይህንን

ችግር ባለመገንዘብ መዝገብ መዝጋት ላይ አተኩረዉ ስለሰሩ ነዉ፡፡ በቀሪ ወራት ከፖሊስ ጋር ተገቢውን ስራ መስራት የሚጠበቅ ሲሆን ህብረተሰቡም ማስረጃና ምስክር በመሆኑ ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡

የፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴርን በመወከል ክርክር ከተደረገባቸው በመደበኛ፣ በሙስና እና ኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች በክልልና በዞን በ11 ወሩ 655 መዛግብት ለዐቃቤ ህግ ቀርቦ 642 መዛግብት ውሣኔ አግኝተዋል፡፡13 መዛግበት በዐቃቤ ህግ እጅ የሚገኙ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው የማጥራት ምጣኔም 98.02 በመቶ ነው፡፡ ለበጀት ዓመቱ ከተያዘው 100% እቅድ አንፃር አፈፃፀሙ ዝቅ ያለ ቢሆንም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት የማጥራት ምጣኔ 98.2 በመቶ ጋር ሲነፃፀር  ዝቅ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

የዐቃቤ ሕግ ይግባኝን በተመለከተ በቢሮና በዞኖች ደረጃ በሙስና፣ በመደበኛ እና ኢኮኖሚ ወንጀል በ11 ወሩ 651 መዛግብት የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ በ281 መዛግብት ውጤትን የሚለኩ ውሳኔዎች ተሰጥተው በ229 መዛግብት ላይ በአሸናፊነትና በ52 መዛግብት በተሸናፊነት ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ የማሸነፍ/የማስቀጣት/ ምጣኔን 88 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 81.49% ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ እጅ ከፈንጅ ወንጀልን በተመለከተ በ11 ወሩ በዞንና በወረዳ 608 መዛግብት የቀረበ ሲሆን 500 (82.0%) መዛግብት ውሳኔ ሲያገኝ 108 መዛግብት በቀጠሮ ተላልፈዋል፡፡ በተመሳሳይ አጠቃላይ በወንጀል ጉዳይ ዘርፍ አጥፊዎችን በወንጀል ከማስቀጣት በተጨማሪ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተመዘበሩ ንብረቶችን ለማስመለስ በተደረገዉ ጥረት ብር 350,627,843.47 እና 6,942,947 ካ.ሜ የከተማና የገጠር ቦታ እንድሁም በአይነት ደግሞ በርካታ የጦር መሳሪያ፣ ነዳጅ፣ የአፈር ማዳበሪያ፣ የምግብ ዘይት፣ ቤት፣ ስኳር፣ ፕላፐሌት፣ ቦንዳ ልብስ  ለመንግስት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የፍትሐብሔር ጉዳዬችን በማየት የመንግስትንና የሕዝብን መብት ለማስጠበቅ የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት የሕግ ምክር አገልግሎትን በመስጠት በ11 ወሩ 5,529 የሚሆኑ ጉዳዮች የያዙት የገንዘብ መጠን 103,901,861.50 ቀርበው ሁሉም ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ በፍርድ ቤት ባሉ ጉዳዮች ውጤታማ ክርክር በማድረግ የሕዝብና የመንግሥትን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር  በቀጥታ ክስ ጉዳዮች በአጠቃላይ ከቢሮ እስከ ወረዳ በጥቅሉ በመንግሥት ይሁን ነጻ የሕግ ድጋፍ ለሚሹ አካላት ይዞ የሚከራከራቸዉ መዛግብት 7,026 ሲሆኑ የገንዘብ መጠን 17,770,165,186.00 በያዙት 2,937 መዛግብት አሸናፊ ሲሆን በ332 መዝገብ፣ የገንዘብ መጠን 85,882,568.00 ተሸናፊ ሆኗል፡፡ የ2016 በጀት ዓመት

በፍ/ቤት ክርክር የማሸነፍ ምጣኔ 92.0% ለማድረስ ታቅዶ የማሸነፍ ምጣኔ በመዝገብ 90.0%፣ በገንዘብ 97.0% ሲሆን ብር 2,467,903,117.00 የመንግስት ገንዘብ ከምዝበራ ለማዳን ተችሏል፡፡

### 1.2.5.3. ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት

የሰው ሃብት ልማት ስርአቱን ማሻሻል  አንጻር የፈፃሚውን አቅም ለማሳደግ ለሰራተኞች የተሰጠ የረዥም ጊዜ ስልጠና አፈፃፀምን ስናይ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች በረጅም ጊዜ ስልጠና አቅም ማጎልበቻ ስልጠና ለመስጠት በመጀመሪያ ዲግሪ 500 (ወንድ 250፣ ሴት 250)፣ በ2ኛ ዲግሪ- 1,000 (ወንድ 500፣ ሴት 500) በድምሩ 1,500 (ወንድ 750፣ ሴት 750፣) የታቀደ ሲሆን በመጀመሪያ ዲግሪ ተመልምለው የተላኩ 149 (ወንድ 97፣ ሴት 52) (29%)፣ በ2ኛ ዲግሪ 629 (ወንድ 368፣ ሴት 261 ) (63%) በአጠቃላይ በሁለቱ መርሃ ግብሮች አፈፃፀም 778 (52%) የመንግስት ሰራተኞች በተለያዩ በከፍተኛ የትም/ት ተቋማት በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የረጅም ጊዜ ስልጠና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ምልመላ ተከናውኗል፡፡

የተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀት ከማጎልበት አንጻር በተቋማት ለሚቀርቡ የሙሉና ከፊል መዋቅር ጥያቄዎች በጥናት ላይ በመመስረት ለ10 ተቋማት ምላሽ ለመስጠት የታቀደ ሲሆን በ11 ወራት ለከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት፣ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ በዞን ደረጃ እንዲሁም የ3 ከተማ ነክና 3 ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በ3ቱ ነባር ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ላይ በአጠቃላይ 8 ተቋማት የከፊል  የመዋቅር ማስተካከያ ስራ ተሰርቷል ከእቅድ ክንውን አንጻር 80% ተፈጽሟል፡፡

አዲስ ለሚቋቋሙ ዞኖችና የደረጃ ሽግግር ለሚያደርጉ ከተማ አስተዳደሮች የመዋቅር ስራ 100% ለመስራት ታቅዶ ለአንድ ዞን ማለትም ለስሜን ጎጃም ዞን ሙሉ መዋቅር ተፈቅዷል በተቋም ደረጃ ሲለካ ለ27 ተቋማት መዋቅሩ የተፈቀደ ሲሆን ከእቅድ ክንውን አንጻር 100% ተፈጽሟል፡፡ በተቋማት ለሚቀርቡ የተናጠል ስራ መደብ በጥያቄዎች በጥናት ላይ በመመስረት ለ1,200 የስራ መደቦች ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለ31ተቋማት ፤አዲስ ለተገነቡ ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች በጠቅላላ 2,011 (>100%) የስራ መደቦች ተፈቅደው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በተቋማት እንዲመዘኑ ለተጠየቁና ለተመዘኑ የስራ መደቦች የስራ ዝርዝር ማዘጋጀት 100% ለመፈጸም የታቀደ ሲሆን በ11 ወራት የ13 ተቋማት የ75 (100%) የስራ መደቦችን የስራ ዝርዝር የተዘጋጅቶ ስራ ላይ አንዲውል ተደርጓል፡፡

በተቋማት ለሚቀርቡ የተናጠል ስራ መደብ በጥያቄዎች በጥናት ላይ በመመስረት ለ1,200 የስራ መደቦች ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ ለ31 ተቋማት ፤አዲስ ለተገነቡ ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች በጠቅላላ 1,913 (>100%) የስራ መደቦች ተፈቅደው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

የሰው ሃይል አስተዳደር አሰራርን ማሻሻልን በተመለከተ፡- የተሻሻለውን የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 መሰረት በማድረግ በተገልጋዮች ጥያቄ የሚቀርብባቸውንና ለአፈፃፀም ያስቸገሩ የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችን በበጀት ዓመቱ 8 (2 አዳዲስ መመሪያዎች ለማዘጋጀት እና 6 ነባር በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎች ለማሻሻል እንዲሁም በ11 ወራት 4 ነባር እና 2 አዲስ መመሪያዎችን ለማሻሻልና ለማዘጋጀት በእቅድ ተይዞ 7 ነባር እና 3 አዲስ በድምሩ 10 (>100%) የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችን የማሻሻልና የማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም በየደረጃው ባሉ የሰው ሃይል አስተዳደሮች አማካኝነት በጀት ዓመቱ 33,956 እንዲሁም 11 ወራት 25,467 የሰው ሃይል ስምሪቶችን ለመፈፀም በእቅድ ተይዞ 8,156 (32%) የሰው ሃይል ስምሪት ስራዎች ተፈፅመዋል፡፡

በሌላ በኩል የአገልግሎት አሰጣጥን ውጤታማነት ለማሳደግ በ11 ወር በኮሚሽኑ በተገልጋዮች የቀረቡ ቅሬታዎችን 100% ምላሽ ለመስጠት በእቅድ ተይዞ የቀረቡ ቅሬታ/አቤቱታዎች ብዛት 18 (ው-15፣ሴ-3፣) ሲሆኑ ለ18(100%) ውሳኔ ተሰጧቸዋል፡፡ በተዋረድ በሚገኙ ተቋማት በተገልጋዮች የቀረቡ ቅሬታዎችን 100% ምላሽ ለመስጠት በእቅድ ተይዞ የቀረቡ ቅሬታ/አቤቱታዎች ብዛት 3,003፣ውሳኔ የተሰጣቸው 1,840 (61%) ናቸው፡፡ በተጨማሪም የተገልጋይ እርካታን በዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ ቢሮው በ2015 በጀት ዓመት የተገልጋይ እርካታ መጠንን 80% ለማድረስ በእቅድ ይዞ የእርካታ ደረጃውን ለመለካት የሚያስችል ኮሚቴ በማቋቋም በተመረጡ የክልልና ዞን ተቋማት መረጃው ተሰብስቦ በተገኘው የዳሰሳ ጥናት ውጤት  የተገልጋዮች እርካታ ምጣኔ 70% መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመትም የተገልጋይ እርካታ ምጣኔን 80% ለማድረስ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በተፈጠረው ክልላዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት ማከናወን አልተቻለም፡፡

በ2016 በጀት ዓመት የመጀሪያው መንፈቅ ዓመት የሰራተኞችን የሥራ አፈፃፀም ምዘና በተመለከተ፣ በክልል ደረጃ ከሚገኙ 52 ተቋማት ውል የተያዘላቸውና መመዘን ከሚገባቸው 7,377 (4,570 ወንድና 2,807 ሴት፣) ሰራተኞች መካካል 7,178 (97%) (4,470 ወንድና

2,708 ሴት) ውጤት የተሞላላቸው ሲሆን፤ በአፈጻጸም ደረጃ ሲቀመጥም በጣም ከፍተኛ የለም፣ ከፍተኛ የተሰጣቸው፡- 495 (6.7%) (330 ወንድና 165 ሴት)፣ መካከለኛ፡- 6,866 (95.6%) (4,230 ወንድና 2,636 ሴት)፣ አጥጋቢ ያገኙ 16 (0%) (10 ወንድና 6 ሴት) ሲሆን በክልል ደረጃ ዝቅተኛ ውጤት የተሰጠው ሰራተኛ የለም፡፡ከክልል በታች ባሉ ተቋማት ውል ከተያዘላቸውና መመዘን ከሚገባቸው 183,654 (104,595 ወንድና 79,059 ሴት) ሠራተኞች ውስጥ የተመዘኑት 111,874 (62%) (63,137 ወንድና 48,737 ሴት) ሰራተኞች ናቸው፡፡ ውጤት ከተሞላላቸው መካከል በጣም ከፍተኛ 485 (0.4%)፣ከፍተኛ 8400 (7.5%)፣መካከለኛ 102344 (91.5%)፣ አጥጋቢ 607 (0.5%)፣ ዝቅተኛ 73 (0.06%) መሆኑን ያሳያል፡፡ የልዩ ልዩ የሰው ሃይል ስምሪቶችን መፈፀም፡-በዘጠኝ በየደረጃው ባሉ የሰው ሃይል አስተዳደሮች አማካኝነት በጀት ዓመቱ 33,956 እንዲሁም በ11 ወራት 25,467 የሰው ሃይል ስምሪቶችን ለመፈፀም በእቅድ ተይዞ 8,156 (32%) የሰው ሃይል ስምሪት ስራዎች ተፈፅመዋል፡፡

## 1.2.6. የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ አፈጻፀም

የደን ምርት ለግብርናው እሴት ጭማሪ  ማደግ  በየዓመቱ በአማካይ የ7.4 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ለክልሉ ኢኮኖሚ ደግሞ በየዓመቱ በአማካይ የ12.08 ቢሊየን ብር እሴት ጭማሪ አስተዋፅኦ አለው፡፡  ዘርፉ ከ2008-2014 ዓ.ም በአማካይ 9.3% ያደገ ሲሆን ይህ ከሀገሪቱ 4.3% ሲነጻፀር ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በ2016 በጀት ዓመት የልማት ፕሮጀክቶች የሚያቀርቡትን የሚቀርቡ የአካባቢ ተጸዕኖ ሰነዶችን በመገምገም ለ2,455 ፕሮጀክቶች ይሁንታ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፡፡ በአካባቢ አማካሪነት ለመሠማራት ጥያቄ ላቀረቡና መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 56 ድርጅቶች እና ባለሙያዎች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ የአካባቢ ህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በ3,000 ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ ለ2,319(77%) በማከናወን የማስተካከያ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡ የአካባቢ ህግ ጥሰት በፈጸሙ 109 ፕሮጀክቶች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ በጣና ሀይቅ ላይ የተከሰተውን 305.25 ሄ/ር የእምቦጭ አረም ማስወገድ የተቻለ ሲሆን 62,942 ሄ/ር ሌሎች መጤና ወራሪ አረም ዝርያዎችን በህብረተሰቡ ተሳትፎ ማስወገድ ተችሏል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎችን (CRGE) በተለይም በተግባሪ ተቋማት ለማስተባበርና ለመከታተል ጥረት ተደርጓል፡፡ የክልሉ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ቆጠራ በዋና ዋና ሴክተሮች እንዲጠና ተደርጓል፡፡ በ73 ከተሞች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲጎለብት የሚስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል ከደን ሀብት ገቢ መሰብሰብን በሚመለከት ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ ብር 250 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 92.1 ሚሊዮን ብር ገቢ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙ 37% ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር 59 በመቶ እንደቀነሰ ያሳያል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ተከማችቶና ሲዘዋወር የተገኘ የደን ምርት ውጤት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና በመውረስ 2.8 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰባሰብ ታቅዶ 0.93 ሚሊዩን ብር ለመንግስት ገቢ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 33% ነው፡፡

## 1.2.7. የኮሚኒኬሽን ዘርፍ አፈጻፀም

በ2016 በጀት ዓመት በየደረጃው በወሣኝ ጉዳዮች ላይ በመደበኛ ሚዲያዎች፣ በማህበራዊ ሚዲያዎችና በሚኒ ሚዲያዎች ለህብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ በማቅረብና ግንዛቤ በመፍጠር የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ ርብርብ ተደርጓል፡፡ የመንግሥትን ወቅታዊ የትኩረት አቅጣጫን መሠረት ያደረጉ የመንግስትን አቋም የሚያንፀባርቁ ጽሁፎችን፣ መልዕክቶችን፣ መግለጫዎችንና ሌሎች አጫጭር መረጃዎችን በማዘጋጀት ኅብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ ኖሮት በተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ተሠርቷል፡፡

በተለይ በክልሉ የተፈጠረውን ቀውስ ለመቀልበስ የተሰሩ የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን ስራዎች አበረታች ነበሩ፡፡ በመሆኑም ግቦቻችንን ለማሳካት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ስንመከት፡- በዋና ዋና አገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት በመፍጠር የክልሉን ልማታዊ አስተሳሰብ ማጎልበት በሚመለከት በወሣኝ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግስት አቋም የሚያንፀባርቁ ወቅታዊ ጽሁፎችን በቁጥር 92 ለማዘጋጀት ታቅዶ 103 በማዘጋጀት የዕቅዱን (112%) በማከናወን ለህብረተሰቡ በተለያዩ ሚዲያዎች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንደዚሁም በተመረጡና ወቅታዊ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች 2,388 ጊዜ የሚዲያ መግለጫዎችን ለመስጠት ታቅዶ 1778 (74.5%) ጊዜ በልዩ ልዩ መንግስታዊና ህዝባዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለሚዲያዎች መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም አጫጭር መልዕክቶችንና ስፖቶችን በቁጥር 2384 ለማዘጋጀት ታቅዶ 1814(76%) በመፈጸም ለጋራ መግባባት ሥራ የዋሉ ሲሆን በክልሉ አሚኮ ሬዲዮና ቴሌቪዥን፣ በየደረጃው በሚገኙ ሚኒ ሚዲያዎች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች እና በፌስ ቡክና ልዩ ልዩ የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች በማቅረብ ስለክልሉ፣ ስለዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም ከተማ አስተዳደሮች እንደየተዘጋጁበት ወቅታዊ የትኩረት መነሻ ኅብረተሰቡ መረጃ ኖሮት በተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንና ልማታዊ አመለካከት ኑሮት የራሱን ሚና እንዲወጣ ጥረት ተደርጓል፡፡

ስለክልሉ ሁለንተናዊ የገፅታ ግንባታና የጋራ መግባባት ዙሪያ የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ማሻሻል በሚመለከት በተለያዩ ሀገራዊ፣ ክልላዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች ዙሪያና በክልሉ የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር ለመፍታትና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በርካታ የህዝብ ውይይቶችና የፓናል ውይይቶችን ከባለድርሻ አካላት፣ ከምሁራን፣ ከባለሀብቶች፣ ከመንግስት ሠራተኛውና ከመላው ህዝብ ጋር በክልልና በፌደራል ከፍተኛ አመራሮች የተመሩ ውይይቶች ተካሂደዋል። አፈጻጸሙም 770 ጊዜ ለማመቻቸትና ለማወያየት ታቅዶ 465 (60%) ጊዜ ማካሄድ ተችሏል። እንደዚሁም ወቅታዊ ሁነቶችና የልማት ውጤቶችን የሚያሣዩ የፎቶ ግራፍ ኢግዚቢሽን 2074 ጊዜ ለማዘጋጀት ታቅዶ ክንዉኑ 1172 ሲሆን አፈጻጸሙ (57%) ማከናወን ተችሏል። ሌላው ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ የሚከሰቱና የሚስተዋሉ እለታዊና ሣምንታዊ የህዝብ ጥያቄዎችና ችግሮችን መረጃ በማሠባሠብ በአጭርና በረጅም ጊዜ የመንግስትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዩችን በመለየትና በማደራጀት 52 ጊዜ የተተነተነ ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ ታቅዶ 50 (96%) ጊዜ አደራጅቶ ማቅረብ ተችሏል። በተጨማሪም በየዕለቱ የሚዲያ ክትትልና ዳሰሳ ስራ በማከናወን በክልላችን የሚደረጉ የተሳሳቱ ዘመቻዎችንና ዘገባዎችን በመለየት በፌስ ቡክ፣ በቲውተር፣ በቴሌግራም፣ በቲክቶክ፣ በዩቲዩብና ዌብሳይት ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል።

በተጨማሪም የመንግስት ኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አሠራሮችን ብቃት ማጐልበት በሚመለከት ይህን ግብ ለማሣካት በየደረጃው የሚዲያ፣ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ፎረሞችን በመምራትና ወቅታዊ አጀንዳዎችን በመለዋወጥ ተናቦ ለመስራት ጥረት ተደርጓል። አፈፃፀሙም በክልል ደረጃ የሚዲያ ፎረም 12 ጊዜ ታቅዶ 13(108%) ተከናውናል። ከዚህ ባሻገር በአጫጭር ውይይቶችና ስልጠናዎች ባለሙያውን ለማብቃት 390 ጊዜ የግንዛቤ መድረኮች ለማመቻቸት ታቅዶ 257(66%) የግንዛቤ መድረኮችን በማመቻቸት ፈፃሚውን ለማብቃት ጥረት ተደርጓል። እንዲሁም አጫጭር ተሞክሮዎችን በመቀመር የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም በሚዲያና ኘሮሞሽን ስራ ለመሠማራት የሚፈልጉ ደንበኞችን የምዝገባ የምስክር ወረቀትና እድሣት አገልግሎት በመስጠት የግል የፕሮሞሽንና ሚዲያ ኢንዱስትሪው እንዲስፋፋና በህግ እንዲመራ ክትትል ተደርጓል። በተመሳሳይ መንግስት የሚያከናውናቸውን የሰላም፣የልማት፣የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ግንባታ ስራዎች ዙሪያ ወቅታዊና መደበኛ የህዝብ አስተያየት ጥናት በማድረግ የተመዘገቡ ውጤቶችን፣የጋጠሙ ችግሮችንና የሚስተዋሉ አዝማሚያዎችን በመለየት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና ተቋማት አቅርቧል። በመሆኑም ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ መደበኛ የህዝብ አስተያየት 1,211 ጊዜ ለማጥናት ታቅዶ 579 (48%) ጊዜ ማከናወን ተችሏል።

በተመረጡ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይም 5 ጊዜ የህዝብ አስተያየት ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 5 ጊዜ (100%) ተከናውኗል፡፡ የተጠኑ ጥናቶችም የህብረተሰቡን ጥያቄዎችና ችግሮች ለማወቅና በአጭርና በረጅም ጊዜ በአግባቡ መፍትሄ ለመስጠት ጠቀሜታ አላቸው፡፡

### 1.2.8. የፕላንና ልማት አፈጻፀም

የክልሉን የመረጃ አሰራር ስርዓትን በቴክኖሎጂ በማዘመን ስታትስቲክሳዊ መረጃ ማደራጀትና አገልግሎትን ለማሻሻል በ11 ወሩ በሰነድ 1 የስታትስቲክስ፣ የአስተዳደራዊ እና የመልካ ምድራዊ መረጃዎች ተነባቢ እንዲሆኑ ስታንዳርዶችን ለማዘጋጅት ዕቅድ ተይዞ ወጣውን ሰነድ ወደ ክልል የመቀየር ስራ 80% ማከናዎን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የክልሉን እምቅ ሃብት የሚያሳይ መረጃ ለማደራጅት አመልካቾችን ለመለየትና 1 ታቅዶ በመሬት ሃብት፣ በውሃ ሃብት፣ በቁሳዊ ሃብት እና በቱሪዝም ሃብት በመለየት በ11 ወሩ 1 ዶክመት ተዘጋጅቷል፡፡

የክልሉን የ25 ዓመት የቀጠናዎች ልይታ እቅድ ማዘጋጀት መረጃ በሰብሰብና በማደራጀት የትንተና ስራ በመስራት የመጀመሪያ ሰነድ ድራፍት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ የክልሉን አጠቃላይ የልማት አመልካች /Development Indicator/ ለመስራት የ10 ዓመቱን ዕቅድ መሰረት ያደረገ የ15 ተቋማት የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማቶችን ለማዘጋጅት ታቅዶ የ14 ተቋማት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ የክልሉን ዓመታዊ ስታትስቲካል አብስትራክት ለማዘጋጀት ታቅዶ የ22 ተቋማት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በስነ ህዝብና ልማት ስራዎች የስነ-ህዝብ ጉዳዮች ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 203/2005 ዓ.ም በአዲሱ የቢሮዎች አደረጃጀት መሰረት የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡፡ በቀጣይ በህግ አካላት አስተያየት እንዲሰጥበ ይደረጋል፡፡ በክልሉ በስነ-ህዝብ ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመለየት ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል የውይይት መድረክ ማካሄድ ተችሏል ፡፡

የ2016 በጀት ዓመት የክልሉን ህዝብ ብዛት በነጠላ እድሜ እና በ5 ዓመት የእድሜ ክፍፍል 2 መረጃዎችን በመተንበይ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ መረጃዉ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ጸደርገዋል፡፡ የ38 የገጠር ወረደ፣ የ9 ከተማ አስተዳድር፣ የ1 ሪጂዮ ፖሊታን ከተማ፣ የ1 ዞን በትምህርት እድሜ የሚገኙ ከ2017 እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ ያለዉ ትንበያ ተሰርቶ ለመረጃ ፈላጊዉ አካል ተሰጥቷል፡፡ ክልላዊ ስፓሻል ፕላን ለማዘጋጀት በUN Habitat በኩል የ2015 ዓ.ም የአማራ ክልል አስተዳደራዊ የህዝብ ብዛት መረጃ በወረዳ ደረጃ የተሰበሰበ ቢሆንም በፕላንና ልማት ቢሮ በኩል እንዲረጋገጥ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት አስተዳደራዊ መረጃውን የማጥራት ስራ ተሰርቷል፡፡ አስተዳደራዊው መረጃ

ከ2015 ዓ.ም የትንበያ መረጃ ጋር ሲነጻጸር ከሰባት ሚሊዩን በላይ ልዩነት ያለው መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡

ከክልል ኢኮኖሚ ግመታ አንጻር የክልል የ2014 በጀት ዓመት ኢኮኖሚ ግመታ ሰነድ የመጀመሪያ ድራፍት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩለረ ከ2008 እስከ 2014 በጀት ዓመት የተገኙ ግብአቶችን በማካተት የመጨረሻ ክልላዊ ምርትና አገልግሎት ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ መፈፅም ተቸሏል፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች ተዘጋጅተው በስራ ላይ እንዲዉሉ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የ2015 የ3ቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች እና የሁሉም ንዑስ ዘርፎች እሴት ጭማሪ በወቅቱ የገበያ ዋጋ እና በቋሚ ዓመት ዋጋ መሠረት ተገምቷል፡፡

ክልላዊ የዕቅድ ዝግጅት አሰራርን በማጠናከር ክልሉ በትክክለኛ የዕቅድ አስተቃቀድ ስልት እንዲመራ ለማስቻል የ2016 በጀት ዓመት ክልላዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድን ማዘጋጀትና ማስጸደቅ የተቻለ ሲሆን የ2017 በጀት ዓመት ሪቂቅ እቅድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ከ2018-2022 ዓ.ም ክልላዊ የ5 ዓመት መሪ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

የልማት ፕሮጀክቶችን ፕላን መረጃዎች ምቹ በሆነ መንገድ ለማደራጀት ታቅዶ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ አዋጭ የልማት ፕሮክቶች በበጀት እንዲደገፉ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ ለገንዘብ ቢሮ ቀርቧል፡፡ የካፒታል በጀት የጸደቀላቸዉን መ/ቤቶች የ35 ተቋማት ፕሮጀክቶች መረጃ ለመያዝ ታቅዶ የሁሉንም መረጃ መያዝ ተችሏል፡፡ በክልሉ ካፒታል በጀት፣ በፌደራልና በበይነ መንግስታት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን መረጃ የመሰብሰብና የክትትል ስራዎች ተከናዉነዋል፡፡ ክልላዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች ክትትልና ግምገማ አኳያ የክትትልና ግምገማ  አሰራርን በማጠናከር በ2016 በጀት ዓመት የክትትል ግምገማና ድጋፍ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ ተሰርቷል፡፡

# ክፍል ሁለት፡- የዕቅድ መነሻዎች፣ የትኩረት መስኮች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዓላማዎች እና ዋና ዋና ግቦች፤

## 2.1. የዕቅድ መነሻዎች

የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ግልጽ የሆኑ መነሻ ታሳቢዎችን፣ ጥራት ያለው ግብ እና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ተገቢነት ያላቸውን ዋና ዋና ተግባራት በትክክል በማስቀመጥ ለመፈጸም ያስችላል፡፡ ስለሆነም የዕቅድ መነሻዎች በተሟላ ሁኔታ ተተንትነው መነሻ ሆነዉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

**ሀ/ አገራዊ የረጅም ጊዜ ርዕይ፤**

በአገር ደረጃ ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት የማድረግ ርዕይ ተነድፎ የቀጣይ 10 ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ (Home grown economy ፖሊሲ) ስትራቴጂ የዚሁ ሀገራዊ ርዕይ ማሳኪያ ስልት በመሆኑ እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

**ለ/ ሀገራዊ ማህበረ-የኢኮኖያዊ ፖለቲካዊ ማዕቀፎች**

በሃገር ደረጃ የሚቀረፁ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማእቀፎች ረጅም ዘመናትን ተሻጋሪ የመሆን ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ወደ ተግባር የሚመነዘሩት በየዓመቱና አምስት አመቱ በሚነደፉ መርሃ ግብሮችና መርሃ ግብሩን ተከትሎ በሚዘጋጁ እቅዶች አማካኝነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የ2017 በጀት ዓመት እቅድ ሲዘጋጅ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና አቅጣጫዎች በመመራት ነዉ የመጣውን ለውጥ ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስትራቴጂዎቹን በጥልቀት ለመገንዘብ የሚያግዝ ይሆናል፡፡

**ሐ/ የሕዝቡ አዳዲስ ፍላጐቶችና ጥያቄዎች፤**

የክልሉ ህዝብ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ በየጊዜው አዳዲስ ፍላጎቶችና ጥያቄዎችን የሚያነሳ ሲሆን፡፡ እነዚህን አዳዲስ የሕዝብ ፍላጐቶችንና ጥያቄዎችን የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደመነሻነት ተወስደዋል፡፡

**መ/ የክልሉ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ፤**

በቀጣይ 10 ዓመታት የክልሉን ህዝብ ወደ ተሻለ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደረጃ ሊያሸጋግር እንደሚችል የታመነበት መሪ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ነው፡፡ ስለሆነም

ከዚህ ጋር ተናባቢ የሆነ ዓመታዊ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ እንደመነሻነት ተወስዷል፡፡

**ሠ/ የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እና አጀንዳ አፍሪካ 2063፤**

የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን የክልል ድርሻን መውሰድ ስለሚገባ ተገቢነት ባላቸው ዘርፎች በዕቅድ ዝግጅት ሂደት ከግምት ማስገባት ይገባል፡፡ እ.ኤ.አ. ከ2013-2063 ለ50 ዓመታት የሚዘልቅና የአህጉሪቱ መሪዎችና አገራት የተስማሙበት አጀንዳ 2063 ተቀርጾ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በአፍሪካ አጀንዳ 2063 ከተቀመጡ አቅጣጫዎች መካከል በአህጉሪቱ መልካም አስተደደር፣ ዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር ፍትህና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ጠንካራ ባህል እና የጋራ እሴትን መገንባት፣ በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በተለይም ሴቶችና ወጣቶችን ያሳተፈና በማደግ ላይ ያሉ ህጻናትን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ልማትን እውን ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህን እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

## 2.2. የዕቅዱ የትኩረት መስኮች

- ✓ ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር
- ✓ ዘላቂ የከተማ ልማት ማስፋፋት
- ✓ መሠረተ ልማት ማሳደግ
- ✓ ሰብ-ዓዊ ልማትን ማጎልበት
- ✓ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ አቅርቦት
- ✓ ተቋማዊ አቅም መገንባት

## 2.3. የትኩረት አቅጣጫዎች

- ✓ ጥራት እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ፣
- ✓ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ
- ✓ የሴቶችና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ማሳደግ፣
- ✓ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፤
- ✓ የክልሉን እምቅ አቅምን መሠረት አዳኒነት ያለዉ ኢኮኖሚ መገንባት
- ✓ ፍትሃዊ ልማትን በሁሉም አካባቢዎች ማረጋገጥ
- ✓ የስርዓታት ሽግግር

- ✓ የህዝቡን ተሳትፎ በማጉልበት ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን

## 2.4. የዕቅዱ ዓላማዎች

- ✓ ፈጣን እና ቀጣይነት ያለዉ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ
- ✓ ግብርናዉን በቴክኖሎጅ በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ
- ✓ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የማምረት አቅማቸዉን ማሳደግ
- ✓ የማዕድን ሃብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ከዘርፉ የሚገኘዉን ገቢ ማሳደግ
- ✓ መሰረተ-ልማትን በማስፋፋት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ማፋጠን
- ✓ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በማጠናከር የህዝቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትና ደህንነት ማረጋገጥ

## 2.5. የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ

### 2.5.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅድ

**በኢኮኖሚ ዘርፎች ፈጣን እድገት በማስመዝገብ የክልሉን ኢኮኖሚ በ10.6 በመቶ ማሳደግ፣**
በ2017 በጀት ዓመት የክልሉ ኢኮኖሚ በ10.6 በመቶ እድገት እንዲያስመዘግብ ግብ ተቀምጧል፡፡ ይህ ግብ በየክፍላተ ኢኮኖሚው ሲመነዘር በዕቅድ ዓመቱ የግብርና ዘርፍ በ8.8 በመቶ እድገት የሚያስመዘገብ ሲሆን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችም በቅደም ተከተል 14.9 በመቶ እና የ11.4 በመቶ እድገት እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል፡፡ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የአምራች (ማኑፋክቸሪንግ) ዘርፍም የ15.4 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ይጠበቃል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡- ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት እድገት**

| ተ.ቁ | የኢኮኖሚ ዘርፎች | የ2015 መነሻ /በመቶኛ/ | የ2017 ግብ /በመቶኛ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 3.6 | 8.8 |
| 2 | የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 6.1 | 14.9 |
| 2.1 | ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ | 14.2 | 15.4 |
| 3 | አገልግሎት ዘርፍ | 8.5 | 11.4 |
| | **ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት እድገት** | **5.6** | **10.6** |

አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱን በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 5.6 በመቶ በ2017 በጀት ዓመት ወደ **10.6** በመቶ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ማሳደግ፣ በዚህም የግብርናውን ዘርፍ ዕድገት ከነበረበት 3.6 በመቶ ወደ 8.8 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.1 በመቶ በ2017 በጀት ዓመት ወደ 14.9 በመቶ ማሳደግና የአምራች ኢንዱስትሪውን ከነበረበት 14.2 በመቶ ወደ 15.4 በመቶ ከፍ ማድረግ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉን በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 8.5 በመቶ ወደ 11.4 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

ለግብርናው ዘርፍ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረቶች የሆኑትን የሰብልና የእንስሳት ሃብት ልማት ገበያን መሠረት ባደረገና ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ በማቅረብ በኩል ያላቸውን ድርሻ በማሳደግ ዘርፉ የኢኮኖሚ እድገት ምንጭነታቸውን ማስቀጠል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እሴት በሚጨምሩ የግብርና ልማቶች ላይም የሚተኮርበት ይሆናል፡፡

የኢንዱስትሪ ዘርፍን የ14.9 በመቶ እድገት በማስመዝገብ ረገድ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ሚና የጎላ ድርሻ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ በሚሸጋገሩ ዘርፎች ላይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩልም በግንባታ ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ግንባታቸውን አጠናቀው ወደ ማምረት ሥራ የማስገባት ሥራ ይከናወናል፡፡ በአገልግሎት ዘርፉም በተመሳሳይ በግብርና እና ኢንዱስትሪ ዘርፍ በመመሥረት የተሻለ እድገት እንዲመዘገብ ጥረት ይደረጋል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ በማድረግ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ማሳደግ፣ በ2017 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ዘርፉን በማሳደግ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ለማሳደግ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለዘርፉም ሆነ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ የማሳደግና ከሌሎች ዘርፎች በላቀ ፍጥነት እንዲያድግ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡ ይኸውም የኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት (GDP) ያለውን ድርሻ የማሳደግና ለኤክስፖርትም ሆነ የገቢ ንግድ በመተካት በኩል ድርሻው ከፍ እንዲል የማድረግ ስራ ይሠራል፡፡

ግብርናው ድርሻ በ2015 በጀት ዓመት ከነበረው 52.5 በመቶ ወደ 50.83 በመቶ ዝቅ እንደሚል፤ የኢንዱስትሪ ዘርፉ ከአጠቃላይ የክልል ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2015

በጀት ዓመት ከነበረው 15.7 በመቶ ወደ 16.91 በመቶ፣ የአምራች ኢንዱስትሪዉ ከነበረዉ 8.6 በመቶ ወደ 9.23 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ ከጠቅላላው የክልል ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ከ33.2 በመቶ ወደ 33.66 በመቶ እንደሚያድጉ ተገምቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡- የዋና ዘርፎች ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ**

| ተ.ቁ | የኢኮኖሚ ዘርፎች | የ2015 መነሻ /በመቶኛ/ | የ2017 ግብ /በመቶኛ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 52.5 | 50.83 |
| 2 | የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 15.7 | 16.91 |
| 2.1 | ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ | 8.6 | 9.23 |
| 3 | አገልግሎት ዘርፍ | 33.2 | 33.66 |
| | **ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት** | **100** | **100** |

### 2.5.2. የሥራ እድል ማስፋት

በክልሉ ተከማችቶ የቆየው የሥራ አጥ ዜጋ ብዛት እና ወደ ሥራ ሥምሪት ገበያ የሚቀላቀለው አዲስ የሰው ኃይል ከፍተኛ መጠን ያለው በመሆኑ የሥራ አጥነት ችግሩ አሁንም በከተማ ከፍተኛ ነው፡፡ በማዕከላዊ ስታትስቲክ አገልግሎት መረጃ መሠረት በአማራ ክልል በ2010 ዓ/ም ከነበረበት 19.7 በመቶ በ2014 ዓ/ም ወደ 20 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ስለሆነም የሥራ አጥነት ምጣኔው ለሥራ ሥምሪት ከተዘጋጀው ኃይል አንፃር ተወስዶ ሲታይ በክልሉ አሳሳቢ ሁኔታ ያለ ከመሆኑም በላይ በከተማ እያደገ የመጣው ሥራ አጥነት እንዲሁም በተለይ የሴቶች እና የወጣቶች የሥራ አጥነት ሁኔታ ግን በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆን ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የከተማ ሥራ አጥነት ምጣኔን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 20.0 በመቶ በ2017 በጀት ዓመት ወደ 19.13 በመቶ ለመቀነስ ግብ ተጥሏል፡፡ ስለሆነም በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የልማት ሥራዎች ዜጎችን በማሳተፍ ከ1,233,744 (80 በመቶ ቋሚ) በላይ ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ በዕቅድ ተይዟል፡፡

### 2.5.3. የዋጋ ግሽበት መቀነስ

በአገር አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረት በ2016 በጀት ዓመት 26.6 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህ ማለት የሸቀጦች ዋጋ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የነበረን የሸቀጦች ዋጋ መጨመር ምጣኔን የሚያሳይ ነው፡፡ ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች ዋጋ 24.30 በመቶ ሲሆን፡ የምግብ

ሸቀጦች ዋጋ ደግሞ 28.1 በመቶ ነበር፡፡ በ2015 በጀት ዓመት የአማራ ክልል የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ሲታይ 33.1 በመቶ የደረሰ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑት 34.3 በመቶ ምግብ ነክ የሆኑ ሸቀጦች ደግሞ 32.2 በመቶ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ማለት በክልሉ ከፍተኛ የዋጋ ንረት መከሰቱን ያመላክታል፡፡ በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ ክልላዊ የዋጋ ንረት ምጣኔን ከነበረበት 33.2 በመቶ ትርጉም ባለው ደረጃ ለማዉረድ የታቀደ ሲሆን በዚህም ከፍተኛና የተጠናከረ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡ የዋጋ ንረቱን ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ተግባራትን ማለትም ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን መጨመር፣ የግብይይት ሰንሰለቱን የሚያሳልጡ ተግባራትን ማከናወን እንዲሁም ተመንግስት የወጪ አስተዳደር በብቃት መምራት አስፈላጊ ተግባራቶች ይሆናሉ፡፡

## 2.5.4. መዋዕለ-ንዋይ ዕቅድ

አጠቃላይ ኢንቨስትመንት (Gross capital formation) ለኢኮኖሚ እድገት እና ለሚፈለገው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እውን መሆን እንደ መነሻ የሚወሰድና ለአጠቃላይ ክልላዊ ልማት አስቻይ ሁኔታ ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የኢንቨስትመንት ምጣኔ ከጥቅል የክልል ውስጥ ምርት አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የኢንቨስትመንት ምጣኔውን ማሳደግ የግድ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ መሠረት በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ ኢንቨስትመት ከክልል ውስጥ ጠቅላላ ምርት/RGDP/ አንጻር 31.1 በመቶ እንደሚደርስ ተተንብዮአል፡፡ በቂ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ካስፈለገ ደግሞ የቁጠባ መጠን ማደግ ይገባዋል፡፡ ስለሆነም ኢንቨስትመንትን ከማሳደግ ጎን ለጎን ቁጠባን ማሳደግ ለኢንቨስትመንት በሚያስፈልገው መዋዕለ-ንዋይ እና በቁጠባ መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት የማጥበብ ስራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

## 2.5.5. የልማት ፋይናንስ ዕቅድ

የገቢ በጀት አስተዳደር፡- የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት በመሰብሰብ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ለማስቀጠል እንዲሁም ወጭን በራስ ገቢ ለመሸፈን በቴክኖሎጅ የታገዘ የገቢ አሰባሰብ ስልት መከተል ወሳኝነት አለዉ፡፡ ከዚህ አንጻር የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን በሰው ሀይልና በቴክኖሎጂ የተጠናከረ ስራ በመስራት በ2017 በጀት ዓመት ለማከናወን የታቀዱትን የልማት ስራዎች በበጀት ለመደገፍ በ2016 በጀት ዓመት የ11 ወር ከተሰበሰበዉ 34.38 ቢሊዮን ብር ወደ 82.39 ቢሊዮን ብር በማሳደግ ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

የወጪ በጀት አስተዳደር፡- በክልሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት የገቢና የወጪ ፋይናንስ አስተዳደር ትልቅ ትርጉም ያለው ስለሆነ በቀጣይ በጀት ዓመት በዘርፉ የክልሉን የገቢ አቅም የማሳደግ እና ወጪን ውጤታማ በሆነ መልኩ የማስተዳደር ሥራዎች ይከናወናሉ። በዚህም መሠረት በ2017 በጀት ዓመት የክልሉን ገቢ ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። የግብር አሰባሰቡን ውጤታማ ለማድረግ የግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ግብሩን በወቅቱ እንዲከፍል የመቀስቀስና የግብር ትምህርት የመስጠት፣ የታክስ ህጎችን የማስከበር እና በዘርፉ የሚታየውን ብልሹ አሰራር ችግር የመታገል ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለ2017 በጀት ዓመት ለልማት ሥራዎች ማስፈፀሚያ በቀጣይ የክልሉ ምክርቤት ሲያጸድቀዉ በዕቅዱ የሚካተት ይሆናል።

## 2.6. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች ዕቅድ

### 2.6.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዕቅድ

#### 2.6.1.1. ግብርና ልማት

የግብርናው ዘርፍ ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን ድርሻ መሠረት በማድረግ የግብርና ልማቱን በምርምር፣ በመስኖ ልማት፣ በአፈርና ውሃ ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎች በመደገፍ በርካታ ተግባራት በመፈጸማቸዉ ግብርናውን ውጤታማ ለማድረግ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። ስለሆነም በ2016/17 በጀት ዓመት ለማከናወን የታቀዱት ግብና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በ2015/16 የምርት ዘመን በመኸር የተገኘውን 145,304,384 ኩ/ል ምርት (በክልሉ ምርት ትንበያ) በ2016/17 የምርት ዘመን በ2,751,340 ሄ/ር መሬት በማልማት 100,617,893 ኩ/ል የምግብ ሰብሎች፣ 1,622,695 ሄ/ር መሬት በማልማት 58,105,780 ኩ/ል በኢንዱስትሪ ሰብሎች፣ 811,434 ሄ/ር መሬት በማልማት 10,429,387 ኩ/ል የኤክስፖርት ሰብሎች ምርት በድምሩ 5,185,468 ሄ/ር መሬት በማልማት ምርቱን ወደ 169,153,059 ኩ/ል ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል።

በሌላ በኩል በ2016 በጀት አመት በመስኖ ልማት የተመረተዉን 32,030,801 ኩ/ል ምርት በ2017 በጀት አመት 338,007 ሄ/ር መሬት በማልማት ምርቱን ወደ 41,670,301 ኩ/ል ለማሳደግ ታቅዷል። በተጨማሪም በ2016 በጀት አመት በመስኖ ስንዴ ልማት ከተመረተዉ 151,625 ሄ/ር መሬት በ2017 በጀት አመት 250,000 ሄ/ር በማድረስ 10

ሚሊየን ኩንታል ለማምረት በዕቅድ ተይዟል፡፡ እንዲሁም በ2016 በጀት ዓመት የተመረተውን 9,188,100 ኩንታል የበልግ ምርት በ2017 በጀት ዓመት ወደ 9,996,658 ክ/ል ለማምረት ይሰራል፡፡

በ2015/2016 ምርት ዘመን በተመረጡ ወረዳዎች በመኸር አትክልት፣ ሥራስርና ቅመማ ቅመም ኮሞዲቲ ስብሎች ከነበረዉ 4,539,000 ኩ/ል ምርት በ2016/17 ምርት ዘመን 76,716 ሄ/ር መሬት በማልማት ወደ 8,064,283 ኩ/ል ምርት ለማሳደ ይሰራል፡፡ የሆርቲካልቸር ልማትን ለማሳደግ 1,000 ኩ/ል የቡናና 2,000 አቮካዶ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ እንዲሁም 10136,757 ቡና፣ 7,366,772 የቆላ ፍራፍሬ እና 549,348 የደጋ ፍራፍሬ ችግኝ በማፍላት እንዲተከል የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የግብርና መካናይዜሽንን በማስፋት በግል ባለሃብቱ በ2015/16 ምርት ዘመን 475,903 ሄ/ር መሬት በማልማት የተገኘዉን 4,172,230 ኩንታል በ2016/17 499,698 ሄ/ር በማልማት ወደ 4,539,390 ኩንታል ምርት ለማሳደግ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም 144 ትራክተር፣ 23 ኮምባይነሮች እና 100 አነስተኛ መዉቂያ መሳሪያዎችን በምርት ዘመኑ ጥቅም ላይ ለማዋል በዕቅድ ተይዟል፡፡ በክላስተር ሰብል ልማት መርሃ ግብር 1,032,911 አርሶ አደሮችን ተሳታፊ በማድረግ 552,550 ሄ/ር መሬት በማልማት 27,541,294 ኩ/ል ምርት ለማምረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተሸሻሉ አሰራሮችንና የቴክኖሎጂ ዘዴዎችን በመጠቀም በመስመር በመዝራት 2,462,427 ሄ/ር፣ በሰብል ስብጥር 238,947 ሄ/ር፣ በቅብብሎሽ ሰብል ልማት 2,007,906 ሄ/ር፣ 83,885 ሄ/ር በዳግም ሰብል ልማት ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል በዕቅድ ተይዟል፡፡ የግብዓት አጠቃቀምን በማሻሻል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ 8,057,900 ኩ/ል ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ፣ 339,532 ኩ/ል ምርጥ ዘር፣ 1,801,457 ሊ/ር እና 74,639 ኪ/ግ ጸረ ተባይና ጸረ ፈንገስ ኬሚካል ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዷል፡፡

አፈር ለምነት ለማሻሻል 2,691,090 ኩ/ል ኖራ፣ 547,572 ሳቸት ህየወ ማዳበሪያ፣ በዘመናዊ 193,558 ሄ/ር በባህላዊ 484,355 ሄ/ር በድምሩ 677,913 ሄ/ር መሬት በማጠንፈፍ ከኮትቻ አፈር ልማት 7,525,429 ኩ/ል ምርት ለማግኘት ይሰራል፡፡ በተጨማሪም 102,031,197 ሜትር ኩብ ኮምፖስት በማዘጋጀት 2,805,858 ሄ/ር ማሳ፣ 2,265,196 ኩ/ል ቨርሚ ኮምፖስት በማዘጋጀት 45,304 ሄ/ር ማሳ እንዲሁም 292,152 ሜትር ኩብ ባዬ ስለሪ በማዘጋጀት 36,519 ሄ/ር ማሳ ለማልማት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች

የሚከናወኑ ናቸዉ፡፡ በምርት ዘመኑ የምርት ብክነትን በ4 በመቶ ለመቀነስ 1,300 ዘመናዊ የብረት ጎተራ (ሜታል ሳይሎ)፣1,500,000 ዘመናዊ ሄልማቲክ ጆንያ፣ 93 የበቆሎ መፈልፈያ 900 ሁለገብ መዉቂያ 68 ሀርቨስተር ኮምባይነር፣ 59 ኮምባይነር የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል በትጋት ይሰራል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራን በማጠናከር የተራቆተውን መሬት እንዲያገግም ማድረግና የክልሉን የደን ሽፋን አሁን ካለበት 15.7 በመቶ ወደ 16.7 በመቶ ለማድረስ፣ በአዲስ 204,118 ሄ/ር መሬት በተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ በመሸፈን፣ 150,000 ሄ/ር የተራራና የተራቆተ መሬት ከልሎ በማልማት እንዲያገግም የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

ከእንስሳትና እንስሳት ተዋጽዖ ምርትን ለማሳደግ የወተት ምርትን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,903,068,000 ሊትር ወደ 2,218,930,000 ሊትር ፣ የሥጋ ምርትን ከ448,816 ወደ 645,087.30ቶን፣ የዓሳ ምርትን 31,870 ቶን ወደ 41,354 ቶን፣ የእንቁላል ምርትን ከነበረበት 851 ሚሊዮን ወደ 871.05 ሚሊየን ፣ የማር ምርትን ከነበረበት 22,292ወደ 32,492 ቶን፣ የሰም ምርትን ከነበረበት 856 ቶን ወደ 1,752 ቶን ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን ዘርፉን ዉጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የመኖ ማልሚያ ዘዴዎችን በመጠቀም 49.6 ሚ/ን ቶን የድርቆ የመኖ ምርት ጥቅም ላይ እንዲዉል ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የእንስሳት በሽታ ቅድመ-መከላከል ህክምና ከ18 ወደ 29.9 ሚሊየን እንስሳት ፣ የእስሳት ክትባትን ከ36.3 ወደ 65.2 ሚሊየን እና የፈውስ ህክምና ከ8.5 ወደ 10.8 ሚሊየን እንስሳት በማድረስ የእንስሳት በሽታ የመከላከልና የመቆጣጠር አቅምን ለማሻሻል የሚሰራ ይሆናል፡፡

ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ለየአካባቢው ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ የምርምር ስራዎችን ለማዉጣት የሚሰራ ሲሆን በዚህም የሰብል ልማት ምርታማነት የሚያሻሽሉ 42፣ የዘር ጥራትን ሊያሻሽል የሚችል 1፣ የዕንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ምርትን ሊያሳድጉ የሚችሉ 26፣ የደን 6 እንዲሁም በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት አያያዝ 4 ቴክኖሎጂዎችን የምርምርና የማውጣት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር የምርት ግብይት ሚናቸውን እንዲወጡ ለማድረግ፣ የመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ቁጥር አዲስ 2,314 በመጨመር በ2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 6,908 ወደ 9,222 ማድረስ፣ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት ቁጠባ አሁን ካለበት ከብር 8,132,862,053 ወደ ብር 10,019,951,913 ማሳደግ፣

መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትን ግለሰብ አባላት ቁጥር ሁን ካለበት 6,492,035 ወደ 6,650,539 ማሳደግ እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራትን ካፒታል ከብር 14,687,154,444 ወደ ብር 15,483,792,524 ማሳደግ እንዲሁም የብድር ስርጭት አሁን ከደረሰበት ብር 28,192,760,018 ብር ወደ 33,493,847571 ለማድረስ በትኩረት ይሰራል።

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ወቅታዊ መረጃዎችን ከሁሉም ዞኖች በሳምንት 1 ጊዜ፣ በወር 4 ጊዜ፣ በዓመት 48 ጊዜ መሰብሰብና መረጃውን ተንትኖ ምላሽ ለሚሰጡ አካላት ማስተላለፍ፣ በ10 ወረዳዎች የአደጋ ስጋት ቅነሳ ጥናት ማካሄድ እና አደጋን ቀድሞ የመከላከል ስራ መስራት፣ የ2016/17 የመኸር ምርት ዘመን የሰብል ግምገማን መሰረት አድርጎ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የዕለትና የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ድጋፍ ማቅረብ፣ ለ621,797 ተፈናቃይ ወገኖች በዘላቂነት ለማቋቋም የዘላቂነት ጥናት ማጥናት፣ ለ1,884,378 የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ወቅታዊ እና ተመጣጣኝ የሆነ የምግብ ድጋፍ ማቅረብ እንዲሁም የሴፍቲኔትን ሀብትና ጉልበት የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ስራ ላይ እንዲውል ታላሚ አድርጎ መስራት የሚሉት በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት ናቸዉ።

### 2.6.1.2. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት

በክልሉ ጸጋዎች ላይ ተመስርቶ በተመረጡ ቦታዎች ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን በመከለል እና በማቋቋም ለኢኮኖሚያዊ ሽግግር ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ኢንቨስትመንቶችን ማስፋፋትና ክልሉን ተወዳዳሪ እና ቀዳሚ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ የክልሉን ቀጠናዊ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ዝርዝር ጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር 2 የልማት ቀጠና ዝርዝር ጥናት በማስጠናት ወደ ስራ ማስገባት፡ በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ 36,609 አዳዲስ የሃገር ዉስጥ ባለሃብቶችን ለይቶ የመመልመልና ወደ ስራ ማስገባት።

የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን (Promotion Strategies) በመጠቀም ከ17,031 በላይ የሚሆኑ የተለዩ ባለሃብቶችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማስተዋወቅና ገፅታ ግንባታ ስራ መስራት ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ 303 ቢሊዮን ብር ካፒታል የሚያስመዘግቡ 3,593 የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች በተለያዩ ዘርፎች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለክልሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት ተግዳሮቶችን በመለየት እንዲፈቱ የማድረግ ተግባራት በትኩረት የሚሰሩ ተግባራት ናቸዉ።

ማኑፋክቸሪንግን በተመለከተ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውል የመሬት እና ሌሎች መሰረተ-ልማት አቅርቦትን በማሟላት የተሻለ የእሴት ጭማሪ ያላቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት ለማሳደግ ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር ማሳደግ፣ ለሁሉም አምራች ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች 3,700 ሄ/ር መሬት ማዘጋጀት፣ ለ318 አምራች የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የ731.75 ሚሊዮን ብር እንዲሁም ለ7 ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 50 ሚሊዮን ብር የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኙ መደገፍ፣ 68 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አማካይ የማምረት አቅም ከ56.04 ወደ 61.46 በመቶ ለማሳደግ፣ ለ564 አምራች ኢንዱስትሪዎች 153,928.5 ቶን የሀገር ዉስጥ ግብዓት አቅርቦት ትስስር መፍጠር፣ ለ1,647 አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣ ለ278 አምራች ኢንዱስትሪዎች የ285.79 ሚሊዮን ብር በሃገር ውስጥ በኢንዱስትሪዎች መካከል በሚፈጠር የገበያ ትስስር 54,674 ቶን ማቅረብ፣ ለ6 አምራች ኢንዱስትሪዎች በውጭ ገበያ የሚሸፈን 14.52 ቶን ግብአት ማቅረብ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልግ 11.1 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኙ የማስቻል እንዲሁም የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግር ለገጠማቸዉ 650 በምርት ሂደት ላይ ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ከባለ ድርሳች ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለመፍታት ይሰራል፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ከ120.26 ሚሊየን ዶላር ወደ 244.3 ሚሊየን ዶላር ለማሳደግ አምራች ኢንዱስትሪዎች 26 ዓይነት ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንዲልኩ በመደገፍ 77,738.41 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲሁም የሆርቲ ካልቸር ፕሮጀክቶች ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ድጋፍ ማድረግ 3,000 ቶን ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ የሚሰራ ይሆናል፡፡ 518 ተኪ ምርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች በመለየት እና ድጋፍ በማድረግ የሚመረት የገቢ ምርት መጠንን ማሳደግ፣ ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና 338,519.18 ቶን ምርት እንዲያመርቱ በማድረግ 1.46 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬን ለማዳን፣ ስትራቴጅክ ገቢ ምርትን የሚተኩ 63 የምርት አይነት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ እንዲሁም ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ስራ ይከናወናል፡፡ በአምራች ኢንዱስትሪው እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 61,530 ለሚሆኑ ዜጎች ስራ እድል እንዲፈጠር ማስቻል፣ የሚሉት በዋናነት የሚተገበሩ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተግባራቶች ናቸዉ፡፡

### 2.6.1.3. የማዕድን ሀብት ልማት

የስነ-ምድር ጥናት ስራዎችን በማካሄድ የማዕድን ነክ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ከዉጭ የሚገቡ ማዕድናትን በአገር ውስጥ ማዕድናት በመተካት ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ትርጉም ያለዉ አስተዋጾ ማበርከት ይጠበቅበታል በመሆኑም ይህንን ታሳቢ ያደረገ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደሚከተለዉ ታቅዷል፡፡

የማዕድን ሃብት ክምችትን በማጥናት ሽፋኑን ለማሳደግ በ1፡50,000 መስፈርት የስነ ምድር ጥናትና ካርታ ዝግጅትን አሁን ካለበት 31,807.98 ካ/ኪ ሜትር ወደ 45,524.98 ካ/ኪ ሜትር ማሳደግ በ1፡500,000 መስፈርት የማዕድን ሀብት የልማት ቀጠና ልየታ ሽፍንን ከ25,000 ካ.ኪ. ሜትር ወደ 30,000 ካ.ኪ.ሜትር፣ የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናትን ፍለጋ ጥናትን ከ81.83 ካ.ኪሜ ወደ 106.83 ካ/ኪሜ እንዲሁም የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍለጋ ክምችት ግመታ ጥናትን ከ4,056.73 ካ.ኪሜ ወደ 4,966.73 በማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ 1 የኖራ ምርት ማምረት ፍቃድ 133 የማዕድን ምርመራ ፍቃድ፣ 26 ከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ ለ4 ልዩ አነስተኛ የወርቅማዕድን፣ ለ23 አነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት እንዲሁም 76 ከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት የማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት በድምሩ ለ263 የማምረትና የምርመራ ፍቃድ ለመስጠት ይሰራል፡፡ ወደ ውጭ የሚላክ የወርቅ፣ ጥሬ ኦፓል እና አምበር ማዕድን ምርት መጠንን ከነበረበት 21,792.33 ኪ/ግ በ2017 በጀት ዓመት ወደ 25,039.39 ኪ.ግ በማሳደግ 6,7 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማስገኘት ታቅዷል፡፡

ተኪ ኢንዱስትሪ ማዕድን ምርትን ከነበረበት 390,380 ቶን ወደ 544,800 ቶን በማሳደግ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 7,628,699 USD በ2017 በጀት ዓመት በ63,256,200 USD የውጭ ምንዛሬን ለማዳን የሚሰራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የኮንስትራክሽን ማዕድን ምርትን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ3,974,088 ሜትር ኩብ ወደ 8,212,399 ሜ3 በማሳደግ ለማምረት ይሰራል፡፡ እንዲሁም ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 56,573,801 በ2017 በጀት ዓመት ወደ ብር 81,274,285.67 ለማሳደግ ከመሬት ኪራይና ከማዕድን ስራ ፈቃድ አገልግሎቶች 41,291,094.69፣ ከሮያሊቲ ብር 25,295,494.69፣ ከቁርጥ ዋጋ እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ክፍያዎች 14,687,696.29 ብር ገቢ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡ በማዕድን ዘርፍ የሚስተዋሉ ህገወጥነቶችን ለመከላከል ፈቃድ ሳይኖራቸዉ ህገ-ወጥነት የሚሰሩ 24 ክሬሸሮች፣ 50 ግለሰቦች፣ 3 የተቋማት ወደ ህጋዊ ስርዓት እንዲገቡ እርምጃ የማስወሰድ ስራዎች ተጠናክረዉ የሚሰሩ ይሆናል፡፡

### 2.6.1.4. ባህልና ቱሪዝም ልማት

ቅንጅታዊ አሠራርን በሁለንተናዊ መልኩ በማጠናከርና የማህበረሰብ ተሳትፎን በማጎልበት የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ለክልሉ ዘላቂ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕምርታ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ በርካታ ተግባራት በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የታቀደ ሲሆን ከቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ አኳያ የቅርስና መስህብ ሃብቶች በዘላቂነት ለመጠበቅ፣ ለ301 ቋሚ ቅርሶች የጉዳት መጠን ልየታ 119 ቋሚ እና 991 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን እንዲሁም፣ ለ4 ጥንታዊ የስዕል ቅርስ ተቋማት የመጠገን፣ ለ474 ቋሚ እና 16,271 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የማጽዳትና መንከባከብ፣ 154 ቋሚ ቅርሶች የተከለለ ወሰን እንዲኖራቸዉ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን በማጎልበት የክልሉን ባህል እሴቶችና ቋንቋዎች ለማሳደግና ለማጠናከር በክልሉ የሚከበሩ 14 ነባር እና 3 አዳዲስ ባህላዊ ክብረ-በዓላትን በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ማልማትና ለማክበር በትኩረት ይሰራል፡፡ ከዚህ አኳያ በባህል ኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ 50 ተቋማት የገበያ ትስስር በመፍጠር ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የቱሪዝም ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ የቱሪዝም መሰረተ ልማት አቅርቦት የ665 ኪ.ሎ አዲስ የመንገድ ዝርጋታ፣ 50 ከ.ሜ የዉስጥ ለዉስጥ እግረኛ መንገድ /walk way/ እንዲሁም የዉሃና ኤሌክትሪክ አቅርቦት ስራዎችን የማስተባበር ተግባራት ይከናወናል፡፡

የቱሪዝም ምርትና ገበያ ልማት ተደራሽነት በማስፋት ከዘርፉ ሃብት የሚገኘዉን ገቢ ለመጨመር ለማስፋፋት በክልሉ የሚገኝ 1 የፍል-ዉሃ ምርትን፣ 1 ብሄራዊ ፓርክ እና 1 ማህበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ስፍራ በማልማት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣ የዉጭ አገር ቱሪስት ፍሰትን በ2016 ከነበረበት 17,305 ወደ 25,085፣ የሀገር ዉስጥ ደግሞ በ2016 ከነበረበት 6,283,802 የቱሪሰተ ፍሰት ወደ 9,497,033 በማድረስ ከዉጭ አገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘዉን ገቢ በ2016 ከነበረበት 70,137,061 ብር ወደ ብር 436,751,849፣ እንዲሁም ከሀገር ዉስጥ ቱሪስት ፍሰት የሚገኘዉን ገቢ በ2016 ከነበረበት 2,378,872,489 ብር ወደ 4,360,662,850 ብር ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ በቱሪስት መዳረሻዎች የዉጭ እና የሃገር ዉስጥ ቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ከነበረበት 1.2 እና 1.4 እንደቅደም ተከተላቸዉ በአማካይ 3 እና 4 ቀናት ለማድረስ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶችን መጠን፣ አይነት እና ደረጃ ማሻሻልና በማጎልበት፣ በቱሪዝም ዘርፍ ጥራት ያለውና የላቀ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ለማድረግ፣ የሆቴሎችን ብዛት በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,756 ወደ 1,956፣ እንዲሁም የሬስቶራንቶችን ብዛት በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,478 ወደ 3,874 ለማሳደግ

በተጨማሪም በሆቴሎችና ሬስቶራንት ተቀጥረው አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞች ብዛትን ከ51,953 ወደ 57,875 ለማሳደግ የተጠናከረ የቁጥጥርና ድጋፍስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በተጨማሪም 20 ሆቴሎችና ሎጅዎች ተመዝነዉ የኮከብ ደረጃ እንዲያገኙ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በትብብር የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 2.6.1.5. ሳይንስና ቴክኖሎጅ ልማት

የቴክኖሎጅ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ተደራሽነትን ለማሳደግ የቴክኖሎጅ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ 6 የአሰራር መመሪያዎችን የማስጸደቅና በተግባር ላይ የማዋል እንዲሁም በ6,377 ተቋማት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የፀደቁ የአሰራር መመሪያ ተደራሽ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በቴክኖሎጅዉ ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት አቅምን ለማጐልበት በግብዓትና በአሰራር ለማሻሻል ለ85,000 የማህበረሰብ ክፍሎች የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ስልጠና፣ ለ1,100 ባለሙያዎች የአድቫንስድ ቴክኖሎጅ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን፣ በተጨማሪም የቴክኖሎጅ አጠቃቀምና አያያዝ ሥልጠና በመስጠት በቴክኒሎጅ ብልሽት ምክንያት የሚወጣ 24 ሚሊዮን የሚገመት ሀብት ወጭን ለመቀነስ ታቅዷል፡፡ በ12 ኢንተርኘራይዞች/ካምፓኒዎች የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ ማስቻል እምዲሁም 36 ካምፓኒዎች በኢንኩቤሽን ማዕከል እንዲታቀፉ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በምርምር የተለዩ ቴክኖሎጅዎችን ማሸጋገርና ጥቅም ላይ ለማዋል ቴክኖሎጅዎችን ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማሸጋገር በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች 35,000 የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የመንግስት አሰራርን በቴክሎሎጅ ለመደግፍ/ለማዘመን 36 አዲስ የቴክኖሎጅ መሠረተ-ልማቶችን መዘርጋት 15 አፕሊኬሽኖች እና 50 ዌብ ሳይቶች ማልማት፣ ለ79 ኢንተርኘራይዞች/ቢዝነስ ኢንኩቤሽን ካምፓኒዎች በምርምርና ስልጠና እንዲደገፍ ማድረግ 70 ተቋማት በለሙ አፕሊኬሽኖች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ይሰራል፡፡

በተጨማሪም 208 ተቋማትንና 22,000 የማህበረሰብ ክፍሎች የቪዲዮ ኮንፈረንስ በተጠቃሚ ማድረግ የመንግስት አገልግሎቶችን በቪዲዮ ኮንፈረንስ በማካሄድ 3 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሃብት ለማዳን የሚሰራ ሲሆን በጥናት የተለየን 1 የአማራጭ የሀይል ቴክኖሎጅዎችን በማልማት ጥቅም ላይ እንዲዉል ይደረጋል፡፡ የተመረጡ ሀገር በቀል ዕውቀቶች በሳይንስ በመታገዝ ማልማትና ጥቅም ላይ ለማዋል 1000 ኢንተርፕራይዞችነ የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠርላቸዉ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ሽፋንን ለማሳደግ 201 ቴክኖሎጅዎች የተናበቡና አቅማቸው ያደገ እንዲሆን ማስቻል፣ 35 አይነት የመንግስት አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ስራ አመራር ስርዓት ታግዘው ለህ/ሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል 36 አዲስ የቴክኖሎጅ መሠረተ-ልማቶችን መዘርጋት እንዲሁም 36 ካምፓኒዎች በኢንኩቤሽን ማዕከል እንዲታቀፉ የማስቻል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

### 2.6.1.6. ንግድና ገበያ ልማት

የንግድ መሠረቱን በማስፋትና ህጋዊ የንግድ ሽፋንን በማጠናከር የሸማቹን መብት ማስከበር ይገባል፡፡ በመሆኑም ከንግድና ገበያ ልማት አኳያ ህጋዊ የንግድ መሠረቱን ከ54.2 ወደ 56 በመቶ ለማሳደግ ለ561,672 የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት የኢንስፔክሽን ስራ በመስራት ጉደለት የተገኘባቸዉን የመለኪያ መሳሪያዎች እንዲወገዱ ማድረግ፣ ለ349,730 ነጋዴዎች የደረጃ ፍረጃ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ግብርና እና የኢንዱስተሪ ምርት ትስስርን ቀልጣፋና ጤናማ በማድረግ የኑሮ ውድነትን ከማቃለል አኳያ፣ በ2016 ከነበረበት 2,719,509 ወደ 4,228,488 ኩንታል የአገር ውስጥ የሰብል እና የኢንዱስትሪ ምርት ትስስር መፍጠር፣ 800 ሚሊዮን ብር የተዘዋዋሪ በጀት በማስመደብና የግብርና ምርት 1 ሚሊየን ኩ/ል እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን 200,000 ኩ/ል፣ 7,070,000 ሊትር ዘይትና ፈሳሽ ሳሙና የገበያ ትስስር በመፍጠርና የኑሮ ውድነቱን የማረጋጋት ስራ መስራት፣ ለ207,848 ቶን የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርቶች 644 የስጋ፣ 3,112 የአሳ፣ 185,129 የወተት፣ 189,963 የማር ምርትን የግብይይት ትስስር መፍጠር በትኩረት ይሰራል፡፡

የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት፣ በመገንባት፣ በማሳስተዳደርና የገበያ መረጃ ተደራሽነትን በማሳደግ የግብይት ስርዓቱን ለማሳለጥ፣ የግብርና ምርቶ መሸጫ የገበያ ማዕከላትን ከነበረበት ከ16 ወደ 78 ማሳደግ፣ 231 አዲስ የገበያ ማዕከላትን ማቋቋም እንዲሁም 1,486 ነባር ገበያ ማዕከላትን የማጠናከር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

የኤክስፖርት ግብይትን በማጠናከር የሰብል፣ የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርት ለማሳደግ በ2016 በጀት ዓመት ነበረበት 4,590,366 ኩ/ል 5,553,794 ኩ/ል ወደ ውጭ የሚላኩ አስገዳጅ የሰብል ምርቶችን (ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር፣ ቦሎቄ እና ማሾ) በማሳደግ 417.5 ሚሊዩን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት፣ ወደ ውጭ የሚላኩ የቁም እንስሳትን ከነበረበት 22,229 ወደ 23,856 በማሳደግ እና የዓሳ ምርትን 32 ቶን በማድረስ በ2016 በጀት ዓመት

ከተገኘዉ 55,800 ዶላር በ2017 በጀት ዓመት 2.35 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት፣ ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ናቸዉ፡፡

### 2.6.1.7. ስራና ስልጠና

ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን በማስፈን ዘላቂ የሥራ ዕድል በመፍጠርና በማስፋፋት የዜጎች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ተግባራት በዕቅድ ተይዘዋል፡፡ ክልላዊ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ የመረጃ ተደራሽነትንና ጥራትን ለማሻሻል፡ የየገር ውስጥና ውጭ አገር ሥራና ሰራተኛ ማገኛኛ ዳታ ቤዝ ስርዓትን በመተግበር የስራ ስምሪትን ማሳለጥ፣ በቢሮ አንድ እና በዞን መምሪያዎች 22 በድምሩ 23 የስራ ገበያ መረጃ በማደራጀት መፅሄት በማሳተምና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ በተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች፣ የመንግስትና የልማት ድርጅቶች እና የግል ድርጅቶች 840,025 በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል መረጃ ማሰባሰብ እና ጥቅም ላይ እንዲዉል ይደረጋል፡፡

የስራ ባህልን በመገንባት የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን በማስፋፋት 80,000 በሕጋዊ መንገድ ለሥራ ወደ ውጭ አገር መሄድ ለሚፈልጉ ዜጎች መብታቸውና ደህንነታቸው ጠብቆማሰማራት፣ ለ500 በዉጭ ሀገር የስራ ስምሪት ተሰማርተዉ የስራ ጊዜያቸዉን አጠናቀዉ የሚመለሱትን የመልሶ ማቋቋም ስራ መስራት፣ ለ237,650 ስራ ፈላጊዎች የሙያ ምክር አገልግሎት መስጠት፣ በተመዘገቡ ክፍት የስራ መደቦች ላይ 27,194 ዜጎችን ከስራ ጋር በማገናኘት የስራ ቅጥር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን በመከላከል የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለ5,978,076 የህብረተሰብ ክፍሎች የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ግንዛቤ ማሳደግ በተጨማሪም ለ15,000 ስደት ተመላሾች በዘላቂነት የመልሶ ማቋቋምና ተገቢውን የድጋፍና ክትትል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን በዘላቂነት በማሻሻል የአሰሪና ሠራተኛውን ግንኙነት ለማሳደግ ለ48 ድርጅቶች የሁለትዮሽ የሥራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት የመዘርጋት እና ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚቀርቡ የስራ ክርክሮችን 51% በስምምነት እንዲፈቱ ለማስቻል ይሰራል፡፡

ከስራ ዕድል ፈጠራ አኳያ በገጠርና በከተማ 68,175 አዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም ለ493,498 እና በቅጥር ለ740,246 በድምሩ ለ1,233,744 (ቋሚ 80 በመቶ) ስራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን በግብርና ዘርፍ ለ20,453 (ከተማ 6,367 ገጠር 14,086) በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለ21,816 (ከተማ

15,265 ገጠር 6,551) በአገልግሎት ዘርፍ ለ25,906 (ከተማ 19,725 ገጠር 6,181) ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡

በሀገር ውስጥ ገበያ 42,000 ኢንተርፕራይዞችን በውጭ አገር ገበያ ደግሞ 132 ኢንተርፕራይዞችን የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸዉ እንዲሁም ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለ24,471 ኢንተርፕራይዞች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በመደበኛ ብድር ለ14,908 ኢንተርፕራይዞች 29,816 አንቀሳቃሾች ብር 1,490,800,257 በተዘዋዋሪ ብድር ለ8,063 ኢንተርፕራይዞች (16,127 አንቀሳቃሾች) ብር 1,612,665,352 ለ1,500 ኢንተርፕራይዞች (3000 አንቀሳቃሾች) ብር 1,250,000,000 የማሽነሪ ብድር እንዲያገኑ የማመቻቸት ስራዎች ይሰራሉ፡፡

198,927 መደበኛ እና 986,995 በአጫጭር ስልጠና ሰልጣኞችን በመቀበል የስልጠና ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ለማሳደግ፤ በመደበኛ መርሃግብር ወደ ቴክኒክና ሙያ የሚገቡ ነባር ሰልጣኞች ቁጥር በመንግስት 41,261 በግል 19,385 በድምር 60,646 ተቀብሎ ማሰልጠን፣ በመደበኛ መርሃ-ግብር ወደ ቴክኒክና ሙያ የሚገቡ አዲስ ሰልጣኞችን ቁጥር በመንግስት 110,625 በግል 27,656 በድምሩ 138,281 ሰልጠኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣ በአጫጭር ስልጠና በኢንተርፕርነርሽፕ 986,995 እና በቴክኒካል 456,668 ሥራ ፈላጊዎችን ስልጠና ይሰጣል፣ በኢንተርፕርነርሽፕ ከሚሰለጥኑት መካከል ለ15,000 ከስደት ተመላሾች የአጫጭር ስልጠና የሚሰጡ ይሆናል፡፡

ክፍተትንና የእድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ ለ29,982 (ለነባር 20,532፣ ለአዲስ 9,450) ኢንተርፕራይዞች፣ 89,941 (ነባር 61,591፣ አዲስ 28,350) አንቀሳቃሾች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በመስጠት 13,445፣ ኢንተርፕራይዞች ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማድረግ የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ይሰራል፡፡ 150 ሄ/ር መሬት (በከተማ 105 ሄ/ር፣ በገጠር 45 ሄ/ር) 3,500 አዲስ ሸዶች በመገንባት በአዲስ ለሚቋቋሙ ለ17,500 (በከተማ 12,250፣ በገጠር 5,250) ኢንተርፕራይዞችን የማምረቻና መሸጫ ቦታ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ይሰራል፡፡

### 2.6.1.8. መሬት አስተዳደር

በክልሉ ዘመናዊ የመሬት አስተዳድር ሥርዓትን በመዘርጋት ፍትሐዊ የመሬት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ በ2017 በጀት ዓመት ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል ለ380,944 ባለ ይዞታዎች 1,422,081 ማሳ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በመስጠት ከነበረበት

2,675,854 ወደ 3,056,798 ለማሳደግ፤ የታቀደ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ለ11,324 የወል መሬቶች 19,409 የማሳ ካርታ፣ ለ2,017 የመንግስት ተቋማት ለ4,642 የማሳ ካርታ፣ ለ1,779 መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ለ3,864 የማሳ ካርታ መስጠት፡ 365,824 የግልና የጋራ ባለይዞታዎች ለ1,394,166 የማሳ ካርታ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ 47,284 ባለይዞታዎች ብር 712,695,000 የብድርና የኪራይ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም ብድር ያገኙ አርሶ አደሮችም የቁጠባ መጠን ብር 252,888,474 እንዲደርስ የማስቻል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የ548,995 ባለይዞታዎችን የመሬትመረጃ ወደ ብሄራዊ የመሬት አስተዳደር መረጃ በማሸጋገር የ24,882 የመሬት ግብይትና የ262,839 ባለይዞታዎችን በዲጅታል የመረጃ ስርዓት ወቅታዊ የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡

በገጠር መሬት ያለውን ህገ-ወጥ ተጠቃሚነትን በመከላከል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቀነስ 201,577 አቤቱታ መፍታት፣ በዚህም በተሳሳተ ማስረጃ ይዞታቸውን ያጡ 7,315 ተጎጅ የህብረተሰብን ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ማድረግ፣ የመጠቀም መብት የሌላቸው 1,791 ግለሰቦች የያዙትን 215 ሄ/ር መሬት የማስመለስና ወደ መሬት ባንክ ማስገባት፣ የተወረሩ የወል መሬቶችን ከ40,288 ህገ ወጦች 15,842 ሄ/ር መሬት እንዲመለስ ማድረግ፣ እንዲሁም ለ58,290 አዲስ መሬት ጠያቂዎችና ለስራ ፈላጊ ወጣቶች በቡድንም ይሁን በተናጠል በቋሚነትና በጊዜአዊነት 23,985 ሄ/ር መሬት የማቅረብ ስራ በዕቅድ ተይዟል፡፡

በ14 ከተሞች ለ77400 ባለይዞታዎች የይዞታ መብት ምዝገባ በማካሄድ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 22,630 ሰርተፊኬት ወደ 100,030 በማድረስ የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና የማረጋገጥ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ የመሬት ሀብትን ከብክነት ለመከላከል፤ በክልሉ 77 ከተሞች ከሶስተኛ ወገን ነጻ የሆኑ እና በጊዜያዊነት የተላለፉ 42,000 ሄ/ር መሬት ቆጠራና ምዝገባ በማካሄድ ወደ መሬት ባንክ የማስገባት ስራ ይከናወናል፡፡

ጥራት ያለዉ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አያያዝ እቅድ ለ574,303 ለባለይዞታዎች በማቀድ አሁን ካለዉ 3,678,693 የባለይዞታዎችን ቁጥር ወደ 4,252,996 ለማሳደግ ሲታቀድ በዚህም በ341 ቀበሌዎች 1,707,911 ማሳ ብዛት እና 2,219,039 ማሳ ስፍት ጥራት ያለዉ እቅድ የሚታቀድ ይሆናል፡፡

በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አርሶ አደር በቀበሌ ማእከል ለማሰባሰብ የ200 ቀበሌዎች ስኬች ፕላን በማዘጋጀት ሽፋኑን ከ1,930 የቀበሌ ማዕከላት ፕላን ወደ 2,130 ቀበሌዎች ማሳደግ፤ በዚህም 11,889 ግለሰቦች (ለመኖሪያ 11,213፣ ለተቋማት 241፣ ለንግድ 445) 2,916 ሄ/ር ቦታ ማስረከብ እና ሳይት ፕላን መስጠት፣ በ170 የቀበሌ ማእከላት 12,872 የቤት መስሪያ ቦታዎችን በ5,934 ሄ/ር መሬት ላይ በፕላናቸው መሰረት መሸንሸን የሚሸነሸን ይሆናል፡፡ በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለሚነሱ 39,884 ባለይዞታዎች ለ9,971 ብር 19.94 ቢሊዮን የሚገመት ካሳ እንዲከፈላቸው የሚሰራ ሲሆን ለኢንቨስትመንት የሚዉል አዲስ 39,809 ሄ/ር መሬት ማዘጋጀትና ማስተላለፍ ስራ ይከናወናል፡፡

## 2.6.2. የከተማ ልማት ዘርፍ ዕቅድ

ከተሞች የልማት፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ማዕከል እንዲሁም ለነዋሪዎች ተስማሚና ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም በመሆኑም ከተሞች አካታች፣ አሳታፊ እና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ በተሟላ ፕላን እንዲመሩ ለ37 ከተሞች አዲስ መዋቅራዊና መሰረታዊ ከተማ ፕላናቸዉን ማዘጋጀት 57 ከተሞች የፈርጅ ለዉጥ እንዲያገኙ ማድረግ እንዲሁም በፕላን የሚመሩ ከተሞችን ቁጥር በ2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 676 ወደ 683 ማድረስ በዚህም የክልሉን የክትመት ምጣኔ አሁን ካለበት 22.77 መቶ ወደ 23 በመቶ እንዲያድግ ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ስርዓትን በማሻሻል በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 10,406 ሄ/ር መሬት በመለየት 7906 ሄ/ር መሬት ለልማት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ስራዎች በማጠናከር በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች በሪል ስቴት 200 ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኅበራት 19,476 ቤቶች፣ በግለሰቦች 21,400 ቤቶች፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው (ለአቅመ ደካሞች) 1,460 ቤቶች በድምሩ 42,536 ቤቶች እንዲገነቡ በማድረግ እስከ 2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 915,628 ወደ 958,164 ለማድረስ ይሰራል፡፡

በሌላ በኩል የከተሞች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል በከተሞች የማህበራዊና አካባቢ ደህንነትን መሠረተ ያደረገና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የጌጠኛ ድንጋይ (Cobblestone) ንጣፍ መንገድ 80 ኪ.ሜ፣ ጠጠር መንገድ 350 ኪ.ሜ፣ የጥርጊያ መንገድ (መንገድ ከፈታ) 411 ኪ.ሜ፣ የአስፓልት መንገድ 5 ኪ.ሜ፣ በድምሩ 876 ኪ/ሜ መንገድ የሚገነባ ይሆናል፡፡ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ ግንባታ

180 ኪ.ሜ፣ 25 ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ እና 300 ስላብ ከልቨርት ማስገንባት፣ 423 ኪ.ሜ የከተማ ውስጥ የመንገድ መብራት መስመር ዝርጋታ፣ 473 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ዝርጋታና በቁጥር 122 የውሃ ቦኖ ግንባታ ማከናወን የማህበራዊና አካባቢ ደህንነትን መሠረተ ያደረጉና የጥራት ደረጃውን የጠበቁ 1,500 ሽዶች፣ 120 የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች፣ 5 የወጣት ማዕከል እና 7 የገበያ ማዕከል፣ 1 ዘመናዊ ቄራ፣ 36 ጊዜያዊ ቄራ እና 1 ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ (ደብረ ብርሃን) እንዲገነባ ማድረግ፡፡ 23 ኪ.ሜ ጌጠኛ መንገድ፣ 428 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ እና 6 ኪ.ሜ የአስፋልት መንገድ ጥገና ይከናወናል፡፡

በከተሞች የፅዳትና ውበት አገልግሎትን ለማሻሻልና ለማሳደግ በሁሉም ከተሞች ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 954,072 ወደ 1,014,400 ሜትር ኪዩብ በማሳደግ በተገቢው ቦታ ማስወገድ፣ በ30 ከተሞች ደረቅ ቆሻሻን ቤት ለቤት በዓይነት በመለየት 15 በመቶ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ዑደት (ኮምፖስት ዝግጅት፣ ፕላስቲክ መሰብሰብ) ማከናወን በ683 ከተሞች 880,000 የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ 22 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 1,510 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎች የማልማት ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ስራ አመራር፣ ቁጥጥርና ተወዳዳሪነት በማሳደግ በክልሉ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚታየዉን የአቅም ክፍተት በመሙላት 400 ተቋራጮች እና 60 አማካሪዎች አገር አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ በሆኑ 18 ከተሞች ለምግብ ዋስትና ተጋላጭ ሆኑ 95,922 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸዉ እንዲረጋገጥ በተኩረት ይሰራል፡፡

## 2.6.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ ዕቅድ

### 2.6.3.1. ትምህርትና ስልጠና

ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በፍትሐዊነት በማዳረስ የዜጎችን አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ እንዲሁም መልካም ዕሴቶችን በማጐልበት ብቁ ዜጋ ማፍራት ክልሉ ለሚፈልገዉ ሁለንተናዉ የልማት ዕድገት ድርሻዉ የላቀ ነዉ፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተደራሽነትና ውስጣዊ ብቃትን ለማሳደግ፣ በክልሉ በሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች የሚሠሩ መምህራን እና የተማሪዎችን ቁጥርእንደየቅደም ተከተላቸዉ ከነበረበት 183,346 እና 4,535,751 ወደ 204,247 እና 5,052,826 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 28.80 በመቶ ወደ 45.64 በመቶ፣ ንጥር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 28.62 በመቶ ወደ 43.50 በመቶ፣ ጥቅል የአንደኛ ክፍል ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 61.1 በመቶ ወደ 109.83 በመቶ እንዲሁም ንጥር አንደኛ ክፍል ቅበላ ምጣኔ ከነበረበት 50.37 መቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በሌላ በኩል ጥቅል ከ1-6ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 45.31 በመቶ ወደ 83.08 በመቶ እንዲሁም ንጥር ከ1-6ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 45.31 በመቶ ወደ 76.58 በመቶ ለማድረስ ጥረት ይደረጋል፡፡ ጥቅል ከ7-8ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 39.74 በመቶ ወደ 63.56 በመቶ እንዲሁም ንጥር ከ7-8ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 31.03 በመቶ ወደ 41.09 በመቶ ከፍ ለማድረግ በዕቅድ ተይዟል፡፡ በተጨማሪም ጥቅል ከ9-12ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 20.10 በመቶ ወደ 41.68 በመቶ እና ከ9-12ኛ ክፍል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ከነበረበት 17.02 በመቶ ወደ 28.68 በመቶ ከፍ ለማድረግ በእቅድ ተይዟል፡፡

የ1ኛ ክፍል የመድገም ምጣኔን 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 4.38 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ-6ኛ ክፍል) መጠነ መድገም ደግሞ ከነበረበት 3.53 በመቶ ወደ 2 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ይሰራል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ-8ኛ ክፍል) መጠነ መድገም 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.44 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ፣ የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ ክፍል) መጠነ መድገም ደግሞ ከነበረበት 24.34 በመቶ ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ለማድረግ በዕቅድ ተይዟል፡፡

የቅድመ አንደኛ ደረጃ መጠነ ማቋረጥ 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 24 በመቶ ወደ 2 በመቶ፣ የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ-6ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥ ከነበረበት 8.1 በመቶ ወደ 2 በመቶ እንዲሁም የመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ-8ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥ ከነበረበት 23.7 በመቶ ወደ 2 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ ክፍል) መጠነ ማቋረጥ 2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 53.9 ወደ 2.0 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ይሠራል፡፡

የ6ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔ 2016 በጀት ዓመት 59.9 በመቶ ወደ 86 በመቶ እንዲሁም የ8ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔ ከነበረበት 24.6 በመቶ ወደ 81 ከፍ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን የ7ኛ ክፍል የመዝለቅ ምጣኔን ደግሞ ከነበረበት 23.6 በመቶ ወደ 95 በመቶ ከፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

የትምህርት ፍትሐዊነት እና አካታችነትን ለማሻሻል ከ7-8ኛ ክፍል የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ያታዊ ምጥጥን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 1:1.28 በ2017 ትምህርት ዘመን መጨረሻ ወደ 1:1.16 ማሳደግ፣ ከ9-12ኛ ክፍል የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ያታዊ ምጥጥን ከነበረበት 1:1.37 ወደ 1:1.26 እና የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መጻሕፍት ተማሪ ጥምርታ በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 1:2 ወደ 1:1 ለማድረስ ይሰራል።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ደረጃ-3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከነበረበት 24.5 በመቶ ወደ 45.2 በመቶ፣ ደረጃ-4 የደረሱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ወደ 10.8 በመቶ፣ ደረጃ-4 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ወደ 10.8 በመቶ ከፍ የማድረግ ስራዎች ተጠናክረዉ ይቀጥላሉ።

በሌላ በኩል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ወደ 1:50 በመቶ፣ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ከነበረበት ወደ 1:40 በመቶ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ከነበረበት 1:48 በመቶ ወደ 1:40 በመቶ ለማድረስ ይሰራል። በተጨማሪም የሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን የመማር ማስተማር ሂደት በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል፣ የተሟላ ቤተሙከራ ካላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ለSTEAM ፕሮግራም የተሟላ ላብራቶሪ ያደራጁ ብዛት ከነበረበት 97 በመቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ እንዲሁም በSTEAM የስራ ላይ ስልጠና የሰለጠኑ መምህራን ብዛት ከነበረበት 8.9 በመቶ ወደ 16.5 በመቶ ከፍ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ።

የት/ቤት ምገባ መርሀግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛ እና አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቁጥር ከነበረበት በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 245,366 (ወንድ 123,004፣ ሴት 122,362) ወደ 1,000,000 (ወንድ 500,000፣ ሴት 500,000) ከፍ ለማድረግ በዕቅድ ተይዟል። የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትንና ለማሳደግ የመማሪያ ጣቢያዎችን ብዛት ከነበረበት 5,290 ወደ 28,155 እንዲሁም ማንበብ ፣መጻፍና ማስላት የሚችሉ ጎልማሶችን ብዛት ከነበረበት 132,144 ወደ 844,654 ከፍ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ የሚሰራ ይሆናል።

### 2.6.3.2. ጤና ጥበቃ

ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ የህብረተሰቡን የጤና ሁኔታ ማሻሻልና ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን በዚህም

የእናቶችን፣ ህፃናትና ወጣቶችን ጤና እና ስርዓተ ምግብ ማሻሻል፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች መጠን ከ75 በመቶ ወደ 92.5 በመቶ (CAR) ማድረስ፣ ከወሊድ በኂላ ወዲያውኑ በ48 ስዓት ውስጥ የሚሰጥ (IPPFP) የድህረ ወሊድ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን ከ2 በመቶ ወደ 19.1 በመቶ ማድረስ፣የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ሽፋን 12 በመቶ ወደ 30.6 በመቶ ማድረስ ምቹ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አግልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማትን ከ61 በመቶ ወደ 86.1 በመቶ ማድረስ፣ በአፍላ ወጣቶች የሚከሰተውን እርግዝና ከ 9 በመቶ ወደ 6.3 በመቶ በመቶ መቀነስ፣ የቅድመ ወሊድ ክትትል 4 (ANC4) አገልግሎት ከ65 በመቶ በመቶ ወደ 82.7 በመቶ መጨመር እንዲሁም የቅድመ ወሊድ ክትትል 8 (ANC8) ከ15 በመቶ ወደ 35.1 በመቶ ማድረስ፣ በሰለጠነ ጤና ባለሙያ የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት ከ56 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማድረስ ይሰራል፡፡

በሌላ በኩል የነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የኤች አይቪ ምርመራ አገልግሎት ሽፋን 97 በመቶ ማድረስ፣ በሳምባ ምች ታመው በፀረተዋህሲያን የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሽፋን ከ 61 በመቶ ወደ 86.2 በመቶ ማድረስ፣ በተቅማጥ ይጠቃሉ ተብሎ ከሚታሰበው ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የህይወት አድንህ ህክምናን (ORS & Zinc or ORS) አገልግሎት ያገኙ ከ23 በመቶ ወደ 61.1 በመቶ ማድረስ፤ ሁሉንም ዓይነት ክትባት ያገኙ ህፃናት ሽፋን ከ86 በመቶ ወደ 99 በመቶ ማሳደግ፣ የመጀመሪያውን ፔንታቫለንት ክትባት ያገኙ ሕፃናት ሽፋን ከ96 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፤ ሶስተኛውን ጸረ አምስት/ፔንታቫለንት ክትባት ያገኙ ሕፃናት ሽፋን ከ91 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፡፡ የኩፍኝ 1 መከላከያ ክትባት ሽፋን ከ87 በመቶ ወደ 99 በመቶ ማሳደግ፤ የማህጸን በር ካንሰር መከላከያ ክትባት 1 (HPV-1) ሽፋን ወደ 98.4 በመቶ ማሳደግ; ከመንጋጋ ቆልፍ በሽታ ተጠብቀዉ የተወለዱ ጨቅላ ህጻናትን ወደ 98.3 ማሳደግ በጤና ተቋም ከተወለዱ ጨቅላ ህጻናት ውስጥ ክብደታቸው ከ2500 ግራም በታች የሆኑ ህፃናትን ሽፋን ወደ 3.6 በመቶ መቀነስ; የስርዓተ ምግብ ልየታ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች ሽፋን ከ43 በመቶ ወደ 84.8 በመቶ የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የበሽታ መከላከለል እና ቁጥጥር ሥራዎችን ለማጠናከር የነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች የኤች አይቪ ምርመራ አገልግሎት ሽፋን 83 በመቶ ወደ 96.3 በመቶ ማድረስ፤ ኤች አይ ቪ ካለባቸው እናቶች ለተወለዱ ሕፃናት የቅድመ መከላከል (prophylaxis) ህክምና ሽፋን ከ 45 በመቶ ወደ 93.8 በመቶ ማድረስ፤ በቅድመ ወሊድ ክትትል የቂጥኝ (Syphilis)

ምርመራ የተደረገላቸው እናቶች ሽፋን ከ 84 በመቶ ወደ 96.6 በመቶ ማድረስ፤ በቅድመ ወሊድ ክትትል የየጉበት በሽታ ኢንፌክሽን (Hepatitis B) ምርመራ የተደረገላቸው እናቶች ከ 528,064 ወደ 616,164 ማድረስ፤ የማህበረሰብ አቀፍ የቲቢ ልየታ ሽፋን ከ10 በመቶ ወደ 26.2 በመቶ ማሳደግ፤ የቲቢ መከላካያ ህክምና (TPT) ዕድሜያቸዉ ከ 15 በታች ለሆኑ ህጻናት ከ 78 በመቶ ወደ 87.2 በመቶ ማድረስ የቲቢ ህክምና ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ ህሙማን መጠን (TSR) ከ 96 በመቶ ወደ 98.2 በመቶ ማሳደግ፤ መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህሙማን ህክምና ስኬት ምጣኔ (DR-TB TSR) ወደ 66 በመቶ ማሳደግ የሥጋ ደዌ በሽታ ልየታ መጠን 95.7 በመቶ ማስቀጠል የሥጋ ደዌ በሽታ ልየታና ህክምና መጠንን ከነበረበት ከ15 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ይሰራል፡፡

የወባ በሽታን ከመከላከል አንጻር ተኘተው የታከሙ የወባ ህሙማን ብዛት ከ3.2 /10000 ህዝብ ወደ 0.4 መቀነስ፣ በጤና ተቋም ከተመዘገበ አጠቃላይ ሞት መካከል በወባ በሽታ ምክንያት የሞቱ ሰዎች ምጥንነት ከ 0.36 በመቶ ወደ 0.05 በመቶ ማድረስ፣ በወባማ አካባቢዎች በፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል የተረጩ ቤቶች ሽፋን ከ55.4 በመቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ዕድሜአቸው 30-49 የሆኑ ሴቶችን ቅድመ ካንሰር የማህፀን በር ምርመራ አገልግሎትን በመስጠት ሽፋኑ ከ 14 በመቶ ወደ 23.1 በመቶ ማድረስ፤ የቅድመ ካንሰር ምልክት ያለባቸውን ሴቶች የህክምና አገልግሎት በመስጠት የተመረመሩትን ሽፋን ከ 66 በመቶ ወደ 77.4 በመቶ ለማድረስ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

የህብረተሰቡን የባለቤትነት እና መሰረታዊ የጤና ክብካቤ በማሻሻል የሀይጂንና የአካባቢ ጤና አገልግሎትን በማጠናከር ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን ከ16 በመቶ ወደ 44.3 በመቶ ማሳደግ፣ የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ያለቸው አባወራዎች/እማውራዎች ሽፋን 53 በመቶ ወደ 76.5 በመቶ ማሳደግ፣ መሰረታዊ የሳኒቴሽን አገልግሎት ያላቸው ጤና ተቋማት ሽፋን 45 በመቶ ወደ 80.7 በመቶ ማሳደግ ኮምፐርሄንሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፓኬጆችን የሚተገብሩ ጤና ኬላዎችን ቁጥር ከ2 በመቶ ወደ 37.9 በመቶ ጤና ኬላዎች ማሳደግ፤ እንዲሁም የመሰረታዊ ድንገተኛ ቀዶ ህክምና አገለግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎችን ቁጥር ከ 16 ወደ 351 ለማድረስ ይሰራል፡፡

ጥራት ያለዉ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት እና ፍትሃዊ የህክምና አገልግሎትን ለማሻሻል የአንቡላንስ አገልግሎት ያገኙ ታካሚዎች ከ 78.9 በመቶ ወደ 89.4 በመቶ ማሳደግ፤ በጤና ተቋም የሚከሰት የድንገተኛ ሞት ምጣኔ ከ 0.28 ወደ 0.58 መቀነስ፤ ከበጎ ፈቃደኛ የሚሰበሰበውን የደም ልገሳ አሁን ካለበት 53,608 ዩኒት ወደ 64,330 ዩኒት ማሳደግ፤

በተቋማት የሚከሰት የሞት ምጣኔ ወደ 0.7 ዝቅ ማድረግ፣ የተመላላሽ የነፍስ ወከፍ ህክምና አገልግሎት ምጣኔ ከ1.8 ወደ 1.7 በመቶ ለማድረስ የሚረዱ ተግባራቶች ይከናወናሉ፡፡ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች እና ስጋቶችን የመከላከል፣ መቆጣጠር እና መቋቋም አቅምን/ስርዓት ለመገንባት የማህበረሰብ እና ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝት ከ4 በመቶ ወደ 35 በመቶ ማድረስ፣ በድንገተኛ ጊዜ ከባድ የሆነ አጣዳፊ የምግብ እጥረት እንዳለባቸው ለተለዩ ከ 5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት የህክምና አገልግሎት የተሰጣቸው መጠን ከ45 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማድረስ፣ በከባድ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ የማቋቋም መጠን ከ24.8 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ በከባድ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን ጤና ተቋማትን 100 በመቶ መልሰው እንዲቋቋሙ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የጤና ሥርዓቱን አቅም ለማጎልበት እና ቁጥጥርን ለማሻሻል አስገዳጅ የኢትዮጵያ የጤና ተቋማትን ደረጃ ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን ከ41 በመቶ  ወደ 86.6 በመቶ ለማድረስ፤ አጠቃላይ (Comprhnsive health post) የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፓኬጆችን የሚተገብሩ ጤና ኬላዎችን ቁጥር ከ13.3 በመቶ ወደ (25 በመቶ) ለማሳደግ፤ መሰረታዊ የድንገተኛ ቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች ቁጥር ከ 11 ወደ 44 ማሳደግ፣ የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደርን ለማሻሻል የባለሙያ ፍልሰት ምጣኔ ከ 3.2 በመቶ ወደ 2.4 በመቶ ለማውረድ፤ የጤና ባለሙያ ለ1000 ሕዝብ ጥመርታ (Physician, nurse, midwives and health officers) 1.91 ወደ 2.0 ለማድረስ ጥረት ይደረጋል፡፡

የጤና መሠረተ ልማት ከማሻሻል አኳያ የኤልክትሪክ አገልግሎት ያላቸው ጤና ተቋማት በመቶኛ ወደ 70.7 በመቶ ከፍ ማድረግ የጤና ተቋማት ብዛት ብዛትን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 4,770 ወደ 5,313 ለማድረስ ይሰራል፡፡ በጤና ኬላዎች የመሠረታዊ መድሃኒቶች (የessential drug availability) አቅርቦት አሁን ካለበት 88 በመቶ ወደ 88.4 በመቶ ማሳደግ፤ በጤና ጣቢያ የመሠረታዊ መድሃኒቶች (የessential drug availability) አቅርቦት አሁን ካለበት 88 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፤ የመድኃኒት የብክነት መጠንን በጤና ተቋማት አሁን ካለበት 1.7 በመቶ ወደ 1.6 በመቶ ለመቀነስ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራባቸዉ ናቸዉ፡፡

### 2.6.3.3. ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ

በበጀት ዓመቱ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት የማስጠበቅ ስራ የሚከናወን ሲሆን በዚህም 154 ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ እና 299 ቀበሌዎች ከሴት ልጅ ግርዛት ነፃ እንዲሆኑ እንዲሁም ጥቃት ደረሰባቸው የመጡትን መቶ በመቶ በአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ። በሴቶች ላይ የሚፈፀመውን የመብት ጥሰት ወይም በጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሃይል ጥቃት ዙሪያ ለ3,792,367 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የሚፈጠር ሲሆን 3,475 በየደረጃው የሚገኙ የጎጂ ልምዳዊ ድርጊቶች አሰወጋጅ ጥምር ኮሜቴዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል። በተጨማሪም 483 ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የተሀድሶ ማዕከላት ተጠቃሚ እንዲሁኑ ይደረጋል፣ እንዲሁም የተሀድሶ አገልግሎት ያገኙት 464 በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ የማመቻቸት ስራ ይከናወናል።

የሴቶች፣ የህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን ተሳትፎና ውክልና የማረጋገጥ ስራ የሚከናወን ሲሆን 1,792,544 ሴቶች በሰላምና መልካም አስተዳደር የንቅናቄ ኮንፈረንሶች እንዲሳተፉ እና ለ159,991 ህፃናት በሀገራዊ አንድነት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፤ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ 5,174 ሴት አመራሮች የአመራር ብቃታቸውን ለማሳደግ በአመራር የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪ የደረጃዉ ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች 12,474 የህጻናት ፓርላማ አባላትን በመወከል እንዲሳተፉ ጥረት ይደረጋል።

የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በልማት ቡድንና ራስ አገዝ 398,880 ሴቶች 257,292,080 ብር እና በገ/ቁ/ብ/ህ/ስ/ማህበራት 220,571 ሴቶች 181,424,756 ብር እንዲቆጥቡ ይደረጋል። በተመሳሳይ 474,512 ሴቶች 492,496,300 ብር በህብረት ስራ ማህበራት በህጋዊነት በመበደር በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል። በተጨማሪም 108,854 አዲስ የሴቶች ልማት ህብረት እንዲቋቋሙ በማድረግ 3,265,633 ሴቶች በአዲስ በልማት ህብረት አባል እንዲሆኑ ይሰራል።

የህፃናትን ሁለንተናዊ መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ ለ1,384,218 የህብረተሰብ ክፍሎች በህጻናት ላይ በሚፈፀሙ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሃይል ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፤ እንዲሁም 51,374 ለሚሆኑ ባለሙያዎች በህጻናት ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችና

የሃይል ጥቃቶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ 154 ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነጻ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል የህጻናትን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አጋር አካት፤ ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመተባባር 422,996 ህፃናት በተለያዩ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጭ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡ 436,487 ህፃናት በነባርና በአዲስ አደረጃጀቶች በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጠራል፣ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ውስጥ 248,230 ህፃናት እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ በየደረጃዉ ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች 12,474 የህጻናት ፓርላማ አባላትን በመወከል እንዲሳተፉ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከነባርና ከአዲስ የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት አባላት 151.96 ሚሊዮን ብር (በገንዘብ 106,375,781 እና በዓይነት 45,589,621) በማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት አባላት ሀብት በመሰብሰብ 210,891 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ፤ 173,498 የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች የቤት ለቤት ጉብኝት በማካሄድ ጉዳያቸውን በመከታተል ልየታ በማካሄድ 122,719 የልማታዊ ሴፍቲኔት ቋሚና ጊዚያዊ ድጋፍ ተጠቃሚ ቤተሰቦች የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር እንዲፈጠርላቸው ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም 1910 ዉሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች ከጎዳና በማንሳት ወደ ማዕከል ለማስገባት የስነ ልቦና፣ የህክምና፣ የምግብ እና የሙያ ስልጠና በመስጠት ወደ ማህበረሰቡ የመቀላቀል እና የማቋቋም ስራዎች ይሰራሉ፡፡ የአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞችን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ለማስጠበቅ በበጀት ዓመቱ 3356 አረጋውያን እና 5024 አካል ጉዳተኞችን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ ማስቻል፣ 26,144 አረጋዊያን እና ለ330 አካል ጉዳተኞች ቋሚ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል፣ እንዲሁም 137,573 አረጋዊያን እና ለ64,420 አካል ጉዳተኞች ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተቋማዊነትና ተጠያቂነት ስርዓት ለማጎልበት በየደረጃው የሚገኙ 10,226 የተቋማት አመራሮች/ዳይሬክተሮች፣ እና ባለሙያዎች እንዲሁም በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች 3,736 አፈ ጉቤኤና የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችና የምክር ቤት አባላት

በስርዓተ ፆታ፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማካተትና ተያያዥ ጉዳኞች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የሚሰጡ ይሆናል፡፡

### 2.6.3.4. ወጣቶችና ስፖርት ልማት

በበጀት ዓመቱ የወጣቶችን የመደራጀት መብት ማስጠበቅ ለ438,742 (ወንድ 285,182 ሴት 153,560) ወጣቶች እና ለ87,507 (ወንድ 56,880 ሴት 30,627) የአደረጃጀት መሪዎች በአመራር ጥበብ /Leadership/ ላይ ስልጠና መስጠት ከእነዚህ ውስጥ የአካል ጉዳተኛ 4,387 /ወንድ 2,852 ሴት 1,535/ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪ የወጣት አደረጃጀቶችን ውጤታማነት ለማሳደግና ለማጠናከር በሙያ 836 በቁሳቁስ 279 እና በገንዘብ ለ279 አደረጃጀቶች ድጋፍ ማድረግ፣ የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ፣ 13,056 (ወንድ 6,528 ሴት 6,528) የወጣት አደረጃጀት አመራሮች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እና በየደረጃው ባለው ም/ቤት የዉሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን ለማረጋገጥ ከነበረበት በህግ አውጪ 30 በመቶ በህግ አስፈፃሚ 15 በመቶ እንዲሁም በህግ ተርጓሚ 30 በመቶ የማድረስ ስራ ይሰራል፡፡

የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለ323,870 (ወንድ 161,935 ሴት 161,935) ወጣቶች 3,238 (ወንድ 1,619 ሴት 1,619) የአካል ጉደተኞች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማስቻል እና ለ5,550 (ወንድ 1,664 ሴት 3,886) ከስደት ተመላሽ ወጣቶች ግንዛቤ በመፍጠር በልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ የማድረግ ስራዎች ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለ5,269,613 (ወንድ 2,634,807፣ ሴት 2,634,806)፤ በበጋ በጎ ፈቃድ የአገልግሎት መስኮች ለ3,970,256 (ወንድ 1,985,128፣ ሴት 1,985,128) ወጣቶች ማሳተፍ፣ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክረምት 13,850,000 እና በበጋ 4,616,666 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ በክረምት ብር 6 ቢሊየን እና በበጋ ብር 3 ቢሊየን የመንግስት ወጪ ለማዳን ይሆናል፡፡ በበጀት አመቱ በየደረጃው በ4,018 ቀበሌዎች፣ በ250 ወረዳዎች፣ ከተሞችና ክፍለ ከተሞች፣ በ22 ዞኖች 1 በክልል የስፖርት ምክር ቤቶችን ለማደራጀት ታቅዷል፡፡

የገቢ መሰረቶችን ለማስፋት ከህብረተሰብ ክፍሎች /ከአርሶአደሩ፣ ከነጋዴዎች፣ ከመንግስት ሰራተኞች/ ብር 333,876,090 በመሰብሰብ ለስፖርት ልማት እንዲውል ለድረግ፣ ከስፖርት ልማት ፈንድ 1 ሚሊየን ብር፣ በስፖርት ማህበራት 1 ሚሊየን ብር እንዲሁም በስፖርት

ተቋማት ከተያዙ ቦታዎች 2.5 ሚሊየን ብር በመሰብሰብ ስፖርቱን የማጠናከር፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን እና የስልጠና ማእክላትን የስፋፋትና የማሳደግ ስራዎችም ይሰራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገር አቀፍ ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ 73 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ማስፋፋት፣ 890 ጥርጊያ እና 480 በት/ቤቶችና በተቋማት ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎችን በማስፋፋት ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆኑ ማድረግ፣ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለ409 (ወንድ 323 ሴት 86) ባለሃብቶች የሙያ ብቃት ወስደው በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ፣ በስፖርት ትጥቅ ማምረት ስራ 6 እና በስፖርት ትጥቅ ማከፋፈል ስራ 55 ባለሃብቶች እንዲሰማሩ የማድረግ ስራዎች በትኩረት የሚሰሩ ይሆናሉ፡፡

## 2.6.4. የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ

### 2.6.4.1. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ

የመንገድ ትራንስፖርት መሠረተ ልማቱን የተቀናጀ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በማሳደግ በሁሉም ዞንና ሪጂኦፖሊታን ከተሞች ያሉ መናኸሪያዎችን CCTV ካሜራ እንዲገጠምላቸዉ ማድረግ፣ 40 በሚሆኑ በዞን፣ ሪጂኦፖሊታን ከተሞችና ከተማ አስተዳደሮች ባሉ መናኸሪያዎች ላይ የኢ-ትኬቲንግ አገልግሎት ተግባራዊ የማስደረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን አሁን ካለበት 252 ወደ 266 የማሳደግ ስራ የሚሰራ ሲሆን በዚህም ከመናኸሪያ የዉስጥ ገቢ፣ ከመዘጋጃ ቤት፣ ከህዝብ ተሳትፎና ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ከሚመደብ በጀት ደረጃ ሶስት 12 አዲስ መናህሪያዎችን መገንባት እንዲሁም 51 ነባር መናኸሪያዎች የማስፋፊያ እና የጥገና ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ በተማሪም በክልሉ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ከነበረበት 5 ወደ 8 የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ከማሳደግ አኳያ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የአነስተኛ፣ መለስተኛ፣ ከፍተኛ ተሽከርካሪዎች ቁጥርን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 13,675 ወደ 15,233 በማድረስ የከተማ ትራንስፖርት አገልግትሎት ለማግኘት አማካይ የመጠባበቂያ ጊዜ ከ 5 ደቂቃ እንዳይበልጥ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የተሽከርካሪና የአሽከርካሪዎችን ብቃትን በማረጋገጥ የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋና የሰዉ ሞት መጠን በ10 ሺ.ህ ተሽከርካሪ 26 በመቶ ለመቀነስ ጥረት የሚደረግ ሲሆን በ2,908,670 መደበኛ የትራንስፖርት ቁጥጥር እና 739,536 ራዳር ቁጥጥር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በክልሉ በ10 ዋና ዋና ከተሞች 10 የጭነት ተርሚናሎች እንዲገነቡ የማመቻቸት ስራዎች ትከረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

### 2.6.4.2. መንገድ

የክልሉን የገጠር መንገድ አውታር በማሳደግና ጥራቱን በማስጠበቅ የመንገድ መሰረተ ልማት ተደራሽነትን ለማፋጠን አጠቃላይ የክልሉ የመንገድ መረብ በ2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 32,201.49 ኪ/ሜትር ወደ 32,725.78 ኪ/ሜትር ለማሳደግ በሁሉም የግንባታ ዘርፎች 524.29 ኪ/ሜ መንገድ ይገነባል፡፡ በዚህም የመንገድ ጥግግትን በ1,000 ካሬ ኪ/ሜትር በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ከ171.89 ኪ/ሜትር ወደ 180.114 ኪ/ሜትር ማድረስ፣ በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ ያለው አማካይ ርቀት በኪ/ሜትር በ2016 ከነበረበት ከ2.95 ኪ/ሜትር ወደ 2.776 ኪ.ሜትር ዝቅ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በበጀት ዓመቱ 240 ፕሮጀክቶች በወቅቱና በጥራት በመገንባት የመንገድ ተደራሽነቱን በማስፋፋት 51 ነባር ፕሮጀክቶች፣ በልማት ድርጅት የሚሰራ 1 መንገድ፣ 43 ኮንክሪትና 32 ተንጠልጣይ የዕግረኛ ድልድዮች፣ 29 መንገዶች ድንገተኛ ጥገናና 84 የተለያየ መጠንና አይነት ያላቸው ስትራክቸሮች በወቅቱና በጥራት እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል በመንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ አማካኝነት በወቅታዊ 517.85 ኪ/ሜ፣ በመደበኛ ጥገና 5410.78 ኪ/ሜ በድምሩ 5,928.63 ኪ/ሜ መንገድን በጥራት የመጠገን ስራ ይከናወናል፡፡ በወረዳ ምክር ቤት እና በህብረተሰቡ ተሳትፎ 226 ኪ.ሜ መንገድ በመገንባት የክልሉን የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በመንገድ ተደራሽነት ሽፋን ለመጨመር በ2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 2,621 (77.8) ቀበሌዎች ወደ 2,648 (78.8) ቀበሌዎች ከፍ የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡

በዩራፕ የተገነቡ የክረምት ከበጋ አገልግሎት የሚሰጡና በወረዳ የሚተዳደሩ የገጠር መንገዶችን በመጠገን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረው 6,325 ኪ.ሜ ወደ 7,421 ኪ/ሜ መንገድ የማድረስ ስራ የሚከናወን ሲሆን የህብረተሰቡን ተሳትፎ በመንገድ ስራዎች ላይ በማሳደግ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰበዉን የገንዘብ መጠን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 505,174,651 ወደ ብር 1,025,000,000 ለማሳደግ በትጋት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸዉ፡፡

### 2.6.4.3. ውሃና ኢነርጅ

የመጠጥ ውኃ፡- የህብረተሰቡን የንጹህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2016 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 75.79 በመቶ የ2 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ወደ 77.79 በመቶ ለማድረስ የሚሰራ ሲሆን በክልሉ የገጠር የመጠጥ ውሃ ሽፋን ከ75.05 ወደ 77.05 በመቶ የከተማ የመጠጥ ውሃ ሽፋን ከ75.27 ወደ 77.27 በመቶ የማድረስ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዚህም 192,000 የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ አዳዲስ 2,627 ልዩ ልዩ አነስተኛ ውሃ ተቋማት እንዲሁም 122 ባለመስመር የገጠር ቀበሌ አገናኝ የመጠጥ ዉሃ ተቋማት ይገነባሉ፡፡ 18 ነባር እና 12 ውል ማሻሻያ የተደረገባቸው ጥልቅ የዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም በ26 ከተሞች አዲስ የውኃ መሰረ ተልማት ግንባታ ማስፋፊያና ማሻሻያ እና የዉሃ ኢንቨስትመንት ወጪ 1.04 ሚሊዮን ብር ማስመለስ ስራዎችን የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የውኃ ብክነትን ለመቀነስ የውሃ ተቋማትን የብልሽት መጠን አሁን ካለበት ከ12.02 በመቶ ወደ11.5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ጥረት የሚደረግ ሲሆን በተለይም በከተማ ያለዉን የብክነት ምጣኔ አሁን ካለበት 22 በመቶ ወደ 21.53 በመቶ በመቀነስ የህብረተሰቡን የውኃ ፍላጎት ለማዳረስ ለ6,850 ቀላል፣ ለ3,800 መካከለኛ፣ እንዲሁም ለ1,800 የውሃ ተቋማትን ከባድ ጥገና የሚደረግ ሲሆን በዚህም ህብረተሰቡ በገንዘብ መዋጮ፣ በቁሳቁስ እና በጉልበት 21,845,540 ብር የሚገመት ተሳትፎ እንዲኖረዉ ይደረጋል፡፡ በሁሉም የዉሃ አገልግሎቶች የዉሃ ምርት መጠንን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 59,046,959 ሜትር ኩብ ወደ 70,260,870 ሜትር ኩብ የዉሃ ምርት ለማድረስ የሚሰራ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በ1,831 የተለያዩ የውኃ ተቋማት ላይ የኬሚካል ጥራት ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል፡፡ የከተሞችን ንጽህና አጠባበቅ ተጠቃሚ ህዝብ ሽፋን በማሳደግ በከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድና ንጽህና አጠባበቅ ተጠቃሚ ህዝብ ሽፋንን ወደ 23.02 በመቶ ማድረስ በከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድና ንጽህና አጠባበቅ ስርዓት በመዘርጋት 674,155 (5.42 በመቶ) የክልሉን የከተማ ህዝብ መጸዳጃ ቤት ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል፡፡

የኢነርጅ ልማት፡- ከአማራጭ የኢነርጂ ምንጭ ቴክኖሎጂዎችን በማልማትና በማስፋፋት ህዝቡን ተጠቃሚ ከማድርግ አኳያ የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን ስርጭት ሽፋን ከደረሰበት ከ70.97 ወደ 74.97 በመቶ በማሳደግ አጠቃላይ በተሻሻሉ ምድጃዎች የተጠቃሚዎችን ብዛት በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 469,355 ወደ 1.04 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ 6 አዲስ አነስተኛና መካከለኛ ከፀሃይ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች

(ሶላር ፤ሚኒገሪድ) ግንባታና ተከላ ስራዎችን በአማካይ 50 በመቶ እንዲጠናቀቅ የማስቻል ስራ ይከናወናል፡፡

የአነስተኛ ሶላር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በቤተሰብ ደረጃ አሁን ከደረሰበት 1,253,758 ወደ 1,383,758 አባወራ/እማወራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡ የኤሌክትሪክ ምድጃ እና ምጣድ ስርጭትና ቁጥጥር ስራዎች ማጠናከር ከደረሰበት የተጠቃሚ ቁጥር 216,243 ወደ 246,243 ማድረስ የቤተሰብና ተቋማት ባዮ ጋዝ የተጠቃሚዎች ቁጥር ከደረሰበት 19,432 ወደ 21,676 ማድረስ፣ በአማራጭ የኢነርጅ ምንጭ ቴክኖሎጅዎች የሚመረት የሃይል መጠንን ከነበረበት 7.339 ሜጋ ዋት በ2017 በጀት ዓመት 0.82 በማመንጨት ወደ 8.159 ሜጋ ዋት ለማድረስ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 2.6.4.4. መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት

ዘመናዊ መስኖ ልማትና አጠቃቀም እንዲኖር በማድረግ  የግብርና ምርትና ምርታማነትን መጨመር እንዲቻል አሳታፊ የመስኖ ጥናት ዲዛይን ሥራዎችን  በመስራት በመስኖ የማልማት አቅምን ማሳደግ፣ በዚህም 74,884.6 ሄ/ር የሚያለሙ 236,357 የሚሆነውን የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የ44 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ማጠናቀቅ እንዲሁም በአዲስ 2,810 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 6,278 የሚሆነዉን ህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርጉ አዳዲስ 50 አነስተኛና መለስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶችን መስራት፣ 4,484 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 94 ነባር አነስተኛ እንዲሁም 17,492 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 42 ነባር መለስተኛ ፕሮጀክቶች የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸዉ ጊዜ እንዲጠናቀቁ ከፍተኛ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፣ 1,742 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 8 አዲስ መለስተኛ እና 254 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 10 አነስተኛ ፕሮጀክቶችን ፈጥኖ ወደ ስራ ማስገባት፣ በተጨማሪም የመስኖ አጠቃቀም አቅምን ለማጎልበት 5,787.83 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸው 57 የመስኖ ተቋማትን የጥገና ስራ በወቅቱ ማከናወን በዚህም 3,252 ኪ.ሜ ዘመናዊና 9,785.1 ኪ.ሜ ባህላዊ የመስኖ አውታር ጠረጋ ስራ ከማከናወ በተጨማሪም በ238 የመስኖ ተቋማት ላይ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ማቋቋም በዋና ዋና ተግባርነት ታቅደዋል፡፡

## 2.6.5. የህዝብ አገልግሎት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ ዕቅድ

### 2.6.5.1. ሠላምና ፀጥታ

በክልሉ ውስጥ የተፈጠረውን የህልውና አደጋ በመቀልበስ አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ ሰፊ እና የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ይህንን

ታሳቢ ያደረገ ግቦችና ተግባራት እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡ የፀጥታ ተቋማትን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባት በመደበኛ ስልጠና አዲስ የሚመለመሉ 12,000 መደበኛ ፖሊስ፣ 2,000 አዲስ የማረሚያ ቤት ፖሊስ እና 5,000 አድማ መከላከል፣ የኢንቨዝትመንትና ቱሪዝም ፖሊስን ተግባራዊ ለማድረግ 1,000 የኢንቨዝትመንትና ቱሪዝም ፖሊስ፣ በባህርና በባህር ዳርቻዎች እየተከሰተ ያለውን ወንጀል ለመከላከል ያስችል ዘንድ 200 የጀልባ ፖሊሶች፣ በቀበሌ ደረጃ በ4,168 ቀበሌዎች በእያንዳንዱ ቀበሌ 70 (50 ወጣት) ሚሊሻ በመመልመል 291,760 ሚሊሻ፣ በስራ ላይ ያሉ 600 የወንጀል ምርመራ፣ 600 እግረኛ የትራፊክ ፖሊሶችን፣ 20 የፎረንሲክ ምርመራ ባለሙያዎች፣ የሰላም አስከባሪ ሃይላቸነን ለማጠናከርም 10799 ተጨማሪ የሰላም አስከባሪ ሃይል በልዩልዩ ፕሮግራሞች በማሰልጠን ወደ ስራ ለማሰማታት ታቅዷል፡፡

በክልሉ የተፈጠረውን የሰላምና ፀጥታ ችግር በመቀልበስ የሰላምና የፀጥታ ሁኔታውን ማሻሻልና እግር ለመትከል በፅንፈኛው የተያዙ ስድስት ወረዳዎች እና 1,291 ቀበሌዎች ከጠላት ነፃ በማድረግ በመንግስት ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ማድረግ፣ በሁሉም አካባቢዎች የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ክፈት እንዲሆን ማድረግ፣ በሁሉም አካባቢዎች መንግስታዊ ተቋማቶች ተገቢውን አገለግሎት እንዲሰጡ ማድረግ በሁሉም አካባቢ የሚንቀሳቀሰውን ፅንፈኛ ጠላት የሰላም አማራጩን ተከትሎ እንዲገባ ማድረግ የህን የማይቀበለውን በቁጥጥር ስር እንዲውል ማድረግ በልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወኑ ስራዎች ናቸዉ፡፡

በሌላ በኩል የፀጥታ ተቋማትን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችና የሎጀስቲክ ማሟላትን ለመፍታት በግዳጅ ላይ ያለውን የሰው ሃይላል ጥቅማጥቅም በማስከበርና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት፣ ስነ-ልቦናውን በመገንባት ጠንካራ ተዋጊ ማድረግ፣ ተቋማዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉና ችግር ፈች የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችንና የአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ በሁሉም የፀጥታ ተቋማት በዓመት 2 ጊዜ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጠን የማሻሻል፣ ጉዳት የደረሰባቸውን የፀጥታ ተቋማት የጉዳት መጠን በማጥናትና መልሶ የማቋቋም የፖሊስ እና የማረሚያ ቤቶችን የጥበቃና ደህንነት ስራ ለማጠናከር የሚያስፈልጉ የቅርብ እርቀት መገናኛ ሬዲዮ፣ ሲሲቲቪ ካሜራ፣ ፊንገር ፕሪንት ማሽን፣ ወክስሩ ሜታል ዲቴክተር የመፈተሻ መሳሪያ፣እና መሰል የቴክኖሎጅ ውጤቶችን የማሟላት ለፀጥታ ተቋማት የመረጃ ክትትል ባለሙያዎች ስራ አስፈላጊ የሆኑ አልባሳትና ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የማሟላት ተግባራት በስፋት የሚሰሩ ተግባራቶች ናቸዉ፡፡

በአጎራባች ክልሎችና አገራት ጋር የሚፈጠረውን ግጭት ለመከላከል በሠላም እሴት ግንባታ ዙሪያ ስልጠና በመስጠት የግጭት ክስተትን 99 በመቶ ለመቀነስ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የፅንፈኝነት አጀንዳዎችን በማንገብ የሃይማኖቶችን ግጭት እንዲፈጠር የሚሰሩ ሀይሎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ በማድረግ የሃይማኖት ጽንፈኝነት 90 በመቶ ለመቀነስ፣ የፅንፈኝነት አጀንዳዎችን በማንገብ የሃይማኖቶችን ግጭት አራማጆችን ለማምከን የሚያስችል በወረዳ ደረጃ በ170 መድረክ 205,936 እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ 141 መድረክ 423,009 ኮንፈረንስ ማካሄድ፣ ሃይማኖት ነክ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችንና ቅሬታዎችን በየደረጃው ባለው አካል በቅንጅት እንዲፈቱ የማድረግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

ህብረተሰቡን ያሳተፈ ጠንካራ የወንጀል መከላከል አሰራር በመዘርጋት ወንጀልን ለመከላከል አጠቃላይ ወንጀል1000 ሰዎች መካከል  በገጠር 1.42 እና በከተማ 4.7 መቀነስ፣ ዋና ዋና ወንጀል በ1000 ሰዎች መካከል  በገጠር 0.57 እና በከተማ 1.66 መቀነስ፡ የሰው መግደል ወንጀል በ1000 ሰዎች መካከል 0.005 በላይ እንዳይፈጸም መስራት፡ በ1000 ሰዎች መካከል የሴቶች ጥቃት 0.12 የህፃናትን ጥቃት በ0.106 መቀነስ፤ በክልላችን የሚፈፀመውን ሕገ-ወጥ የሰዎችና የገንዘብ ዝውውርን 95% መቀነስ፤ የኮሚኒቲ ፖሊስንግ አፈፃፀም ጥራት ደረጃ ከፍተኛ 40% መካከለኛ 60% ዝቅተኛ 0% ለማድረስ፤ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የክልሉን የትጥቅና ጦር መሳሪያ አስተዳደርን ለማሻሻል ህገ ወጥ ትጥቅና አዘዋዋሪዎችን ለህግ ማቅረብ፤ የመንግስት እና የግል ጦር መሳሪያዎች በተጨባጭ ቁጥር ላይ ተመስርቶ ሙሉ በሙሉ የፈቃድ አድሳት እና የአካል ቆጠራ ማድረግ የመንግስትና የግል ትጥቅ የሸጡና ያጠፉ አካላት በጥብቅ ተይዘው በህግ እንዲጠየቁ ማድረግ፣ የጦር መሳሪያ አያያዝና አስተዳደር ስርዓትን ለማዘመን የሚያስችል ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ይሰራል፡፡

የማረ/ቤቶችን የጥበቃና ደህንነት ስራ በማጠናከር የታራሚዎችን አስተዳደር ለማሻሻል የውጭና የውስጥ የጥበቃና ደህንነት  ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ የማድረግ፣ የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር፣ በታራሚዎች የዝውውር፣ የይግባኝና የፍች አገልግሎት አሰጣጥ ቅሬታ እንዳይፈጠር ማድረግ እና አገልግሎት አሰጣጡን 98 በመቶ የማሻሻል ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ታራሚዎች የእውቀትና የክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ የእርምት ስራዎችን ለማሻሻል ታራሚዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማስተባበርና የመቀስቀስ፤ ልዩ ልዩ የሙያ ስልጠናዎችን ዓይነትና ብዛት ለታራሚዎች

የማሳወቅና የአገልግሎት አሰጣጥን በጥራት፣ በዓይነት እና በመጠን የማሳደግ ስራዎች በበጀት ዓመቱ በዘርፉ የሚተገበሩ ስራዎች ናቸዉ፡፡

### 2.6.5.2. ፍትህ

የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ በፍትህ ዘርፍ በፌደራል ውክልና በክልል ጉዳዩች በቀጥታ ክስ የወንጀል ምርመራ መዛግብትን መርምሮ የመወሰን ቅልጥፍናን አቅም ከ98.4 ወደ 100 በመቶ ማሣደግ፣ በወንጀል መዝገቦች የዓቃቢ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን ከ92.1 በመቶ ወደ 95.8 በመቶ ማሣደግ፣ በወንጀል ጉዳዮች የተከሣሽ፣ ምስክር፣ መልስ ሰጭ እና ተጠሪ አቀራረብን በማጠናከር የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን ከ12.87 በመቶ ወደ 3 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በቀዳሚ ምርመራ መታየት ያለባቸው የወንጀል ጉዳዮች 100 በመቶ ማስረጃ እንዲጠበቅ በማድረግ አጥፊዎችን በህግ ፊት ተጠያቂነትን የማስፈን ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በወንጀል ምክንያት የተመዘበረ የህዝብ እና የመንግስት ንብረት የማስመለስ አቅምን ወደ 95 በመቶ የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡ የዐቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት ከ79.92 በመቶ ወደ 82 በመቶ ማሣደግ፣ የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት ከ86.68 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሣደግ፣ የወንጀል አቤቱታ አቀባበል ውሣኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነትን 99.24 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለመፈጸም ይሰራል፡፡

የህግና ፍትሐ-ብሔር አገልግሎትን በማጠናከር የመንግስትን እና የህዝብን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ አኳያ የህግ ረቂቅ ዝግጅትና ህግ ምክር አገልግሎት አቅም በማጠናከር ህጎችን ጥራትና ተፈጻሚነት የማረጋገጥ ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ በፍት-ሐብሄር ከሚያዙ ጉዳዮች ዉስጥ በድርድር መጨረስን በሚመለከት በመዝገብ ከነበረበት 18.84 በመቶ ወደ 28 በመቶ እንዲሁም በፍትሐ-ብሔር ጉዳዮች የሚቀርቡ መዝገቦችን የዉሳኔ አሰጣጥ ቅልጥፍናን ከነበረበት 98.2 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ ከሣሽ ወይም መልስ ሰጭ በሆንባቸው ጉዳዮች አግባብ ያላቸውን ማስረጃዎች በማሰባሰብ በ12 ቀናት ውስጥ በመዝገቡ ላይ ውሣኔ የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስና መልስ ሰጭነት የዓቃቢ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን በመዝገብ 91 በመቶ ወደ 92 በመቶ ለማሣደግ የሚሰራ ሲሆን በዚህም በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እንዲሁም አካል ጉዳተኞች የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ላይ የመርታት ምጣኔን 91 በመቶ ለማሳደግ ይሰራል፡፡ ተቋሙ ክስ ባቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ አስቀድሞ ንብረትን ማሳገድን በመዝገብ 63

በመቶ ወደ 64 በመቶ ማድረስ፤ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸዉ መዝገቦች ውስጥ የማስፈፀም አቅምን በመዝገብ ከ97.71 በመቶ ወደ 98 በመቶ ለማሣደግ ይሰራል፡፡

በሌላ በኩል የተጀረዉን የ16ኛ ዙር የቅድመ ስራ ስልጠና በዉጤታማነት ማጠናቀቅ እንዲሁም ለ17ኛዙር የቅድመ ስራ ስልጠና 300 የፍትህ ባለሙያ ሰልጣኞችን መመልመል፣ 1750 ለሚሆኑ የፍትህ አካላት የአጫጭር ጊዜ የስራ ላይ ሰስልጠና መስጠት፣ ችግር ፈች የሆኑ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ማከናወን የሚሉት ዋና ዋና በዘርፉ የሚከናወኑ ተግባራት ይሆናል፡፡

### 2.6.5.3. ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት

የመንግስት ተቋማትን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችል አደረጃጀት በመፍጠርና አሰራሮችን በቴክኖሎጅ የታገዘ በማደረግ ብቃት ያለው የሰው ሃይል ስምሪት በመፈፀም የአገልጋይነት ስሜት የተላበሰ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ፈፃሚውን ለማብቃት የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 778 ወደ 1,200 ማሳደግ እንዲሁም ለ6,814 የመንግስት ተቋማት የአቅም ክፍተትን የለየ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ለመስጠት ታቅዷል፡፡

የመንግስት ተቋማትን የለውጥ አመራር እና አደረጃጀት መመሪያ አተገባበርን በ2016 ከነበረበት 4,912 ተቋማት ወደ 6,814 ተቋማት የማሳደግ እና ከክልል እስከ ወረዳ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት የፈጣን ለውጥ አምጭ ተግባራትን አሟልተው እየተገበሩ መሆኑን የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 4,770 የመንግስት ተቋማት የዜጎች ቻርተር አዘጋጅው በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ይረጋገጣል፡፡

ከሲቪል ሰርቪሱ ጋር ተያያዥ የሆኑ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና በማሻሻል የተሻሻለውን የመንግስት ስራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 መሰረት በማድረግ በተገልጋዮች ጥያቄ የሚቀርብባቸውን 4 አዳዲስ እና 8 ነባር በስራ ላይ ያሉ በድምሩ 12 የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያዎችን በማዘጋጀትና በማሻሻል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

የተገልጋይ እርካታን በ2016 በጀት ዓመት ከነበረበት 72 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ 4,770 የመንግስት ተቋማት በአገልግሎት አሰጣጡ ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየትና የአጭር.መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ በማቀድ መፍትሄ እየሰጡ መሆኑን በድጋፍና ክትትል ስራ የማረጋገጥ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ የተቋማት የስራ መደቦች ስራ ምዘና በ2016 ከነበረው 96 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ በተቋማት እንዲመዘኑ ለተጠየቁና ለተመዘኑ የስራ መደቦች 100 በመቶ የስራ ዝርዝር የማዘጋጀት እና ለተመዘኑ

የስራ መደቦች ሙሉ በሙሉ ተፈላጊ ችሎታ የሚዘጋጅ ይሆናል። የሰራተኛው የስራ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት ለማሻሻል ለ6,814 የመንግስት ተቋማት የስራ አፈፃፀም ምዘና መመሪያውን ተከትለው መፈፀማቸውን የማረጋገጥ ስራዎች ይሰራሉ።

በ286 ተቋማት የተፈፀሙ የሰው ሃይል ስምሪት ስራዎች ላይ መደበኛ ምርመራ ማካሄድ እንዲሁም በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ውሳኔ አሰጣጥ ንጽጽር በ2016 ከነበረበት 1:34 ወደ 1:36 ለማሳደግ በሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ወሳኔ ከተሰጣቸውና የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦለት በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የተሻረ ውሳኔ መጠን ከ6.9 በመቶ ወደ 3 በመቶ ዝቅ ለማድረግ፣ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

## 2.6.6. የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ ዕቅድ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል በዚህም በዘርፍ መ/ቤቶች የአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎች በዕቅድ ተካተው እንዲተገበሩ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፣ በአየር ንብረት ለውጥ ተግዳሮቶችና አፈፃፀሞች ላይ ያተኮሩ ሁለት የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን ልኬታ የዘርፍ መ/ቤቶች እንዲያከናወኑ ማድረግ እንዲሁም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መጠን ግኝቱን ለሚመለከታዉ አካላት በማሳወቅ የበኩላቸዉን ሚና እንዲወጡ የማስቻል ስራዎች በትኩረት ይሰራል። የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ሥርዓትን በማጎልበት በ1,500 የማምረቻ፣ አገልግሎት ሰጭና ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የህግ ጥሰት በሚፈጽሙ 85 ፕሮጀክቶች እና ተቋማት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በ250 ኬሚካል አቅራቢዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

የደን ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን ለማሻሻል፤ በመንግስት ደኖች ውስጥ የችግኝ ተከላ ቦታዎችን በመለየት በ4,000 ሄ/ር ላይ 1.5 ሚሊዮ የማበልጸጊያ ችግኝ እንዲሁም 500 ሄ/ር መሬት ደን ልማት ላይ በሚሰሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አማካኝነት 1.5 ሚሊዮን ችግኝ የመትከል ስራዎች ይከናወናሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ነባር የመንግስት ደኖች በአግባቡ እንዲጠበቁ ይደረጋል። የደን ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ፤ 7,250 ኩንታል ዕጣን (5,500 ኩ/ል ነጭ ዕጣንና 1,750 ኩ/ል ጥቁር ዕጣን)፣ 2,500 ኩንታል ሙጫ እንዲሁም 6.5 ሚሊዮን ኩንታል ከሰል በህጋዊ መንገድ ተመርቶ ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ።

የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎችን ማልማት በዚህም የሚታየውን ህገ ወጥነት የመከላከል ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል፡ 37 የማስጠንቀቂያ ሳይን ፖስት በጥብቅ ስፍራዎች እንዲተከሉ ማድረግ በተማሪም ሁሉም ጥብቅ ስፍራዎች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖራቸው የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ የውሃ አካልና ውሃ አዘል መሬት ስርዓተ ምህዳሮችን ደህንነት ለመጠበቅና ለማጎልበት በ20 ውሃ አካላትና ውሃ አዘል መሬቶች ላይ የብዝሃ - ሕይዎት፣ የመጤ አረም፣ የብክለት እና አጠቃቀም ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እንዲሁምለ 10 ውሃ አካላትና ውሃ አዘል መሬት ስርዓተ ምህዳሮች የአካባቢ ማኔጅመንት ፕላን ማዘጋጀት በተጨማሪም ለ10 የጣና ሀይቅ ባዮስፌር ሪዘርቭ ኮርና በፈር ስፍራዎች የአካባቢ ማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት ዉጤታማ ስራዎችን ለመስራት ታቅዷል፡፡

## 2.6.7. የኮሚኒኬሽን ዘርፍ ዕቅድ

በበጀት ዓመቱ በዋና ዋና ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር የክልሉን ልማት ከማፋጠን አኳያ የክልሉን መንግስት አቋም የሚያንፀባርቁ በቁጥር 92 ወቅታዊ የአቋም መግለጫዎች በማዘጋጀት ለሚዲያዎች ተደራሽ የማድረግ እንዲሁም በተመረጡ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ 2388 የፕሬስ ኮንፈረንስ በማካሄድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፤ 2384 አጫጭር መልዕክቶችን የማሰራጨት ተግባራት የከናወናሉ፡፡ ስለክልሉ ሁለንተናዊ የገፅታ ግንባታና የጋራ መግባባት ዙሪያ የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር ከባለድርሻ አካላት፣ ከምሁራን፣ ከባለሀብቶች፣ ከመንግስት ሠራተኛውና ከመላው ህዝብ ጋር 770 ጊዜ የፓናል መድረኮችን የማካሄድ፣ ሁነቶችና የልማት ውጤቶችን የሚያሣዩ የፎቶ ግራፍ ኢግዚቭሽን 2074 ጊዜ የማዘጋጀትና ገፅታ የመገንባት፣ በየዕለቱ የሚዲያ ክትትልና ዳሰሳ ስራ በማከናወን በክልላችን የሚደረጉ የተሳሳቱ ዘመቻዎችንና ዘገባዎችን በመለየት በፌስ ቡክ፣ በቲውተር፣ በቴሌግራም፣ በቲክቶክ፣ በዩቲዩብና ዌብሳይት ትክክለኛ መረጃ የማሰራጨት፣ የመደበኛና ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ምላሽ የማሰጠት እንዲሁም የመንግስት ኮሚዩኒኬሽንና የሚዲያ አሰራሮችን ብቃት የማጎልበት ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ፡፡

የአካባቢ ሚዲያዎችን በማቋቋምና በመደገፍ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችን ከማስፋት አኳያ በየደረጃው የሚዲያ፣ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ፎረሞችን ለመምራትና ወቅታዊ አጀንዳዎችን ለመለዋወጥ ብሎም ተናቦ ለመስራት 810 ጊዜ የጋራ ፎረም ውይይቶችን የሚካሄዱ ይሆናል፡፡ ህብረተሰቡን ለልማት የሚያነሳሱ የሚዲያ ውጤቶችን ተደራሽነት የማሳደግ ስራም የሚሰራ ሲሆን በልዩ ልዩ የኮሙዩኒኬሽንና የመረጃ አቅርቦቶች ተፈላጊነት ላይ የሚደረጉ ጥናቶችን ለማጎልበት ጥረት ይደረጋል፡፡

የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችን (ሐዲስ መጽሄት፣ በራሪ ወረቀት ፣ፖስተር፣ አርቲክል ፣ዜናዎች....) በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አንጻርም ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ መደበኛ የሆነ የህዝብ አስተያየት ጥናት የማካሄድ እንዲሁም ከክልሉ መንግስት በሚወርዱ በሁሉም ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት መረጃ በመሰብሰብ ለውሳኔ ሰጭ አካላት የማቅረብ ተግባራት በትኩረት ይሰራሉ፡፡ በሌላ በኩል ከአጎራባች ክልሎችጋር ትብብርን መሰረት ያደረገ አሰራርና ትስስር ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 2.6.8. የፕላንና ልማት ዕቅድ

የክልሉ ህዝብ ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል፣ ተቋማዊ የዕቅድ በጀትና ሪፖርት አሰራር ስርዓትን ማጠናከር፣ የክልሉን የመረጃ አሰራር ስርዓትን በቴክኖሎጂ በማዘመን ስታትስቲክሳዊ መረጃ ማደራጀትና የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ ክልሉን በማክሮ ደረጃ የልማት አቅም የሚሆኑ ችግር ፈቺ የፖሊሲ ትንታኔዎች፣ የጥናት እና ምርምር ስራዎችን ማከናዎን፣ በክልሉ በሚገኙ ከተሞችና ወረዳዎች አስተዳደራዊ የወሰን ማካለል ስራ መስራት የወረዳዎች፣ የከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎች ወሰኖቻቸዉን ካርታ ስራና የህዝብ ብዛት ወቅታዊ የማድረግ ስራዎች በትኩረት ይከናወናሉ፡፡

የክልሉን የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በጥራት ማዘጋጀት፣ ክልላዊ የልማት ኘሮጀክት እቅድ ማዘጋጀትና የኘሮጀክት ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም በጥናት ላይ በመመስረት ክልላዊ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በአመራር ምዘና የማስፈጸም አቅምን የመገንባት ስራዎች በዋናነት ይከናወናሉ፡፡

***መልካም አጋጣሚዎች***

በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የመንግስት ቁርጠኝነት መኖር፣ በየዘርፉ ቀደም ባሉት ዓመታት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች መኖራቸው፣ ነባርና አዳዲስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መኖራቸው፣ በሀገር ደረጃ ተጀመሩ እንደ በጋ ስንዴ፣ የሌማት ትሩፋት፣ አረንጓዴ አሻራ፣ ኢትዮጵያ ታምርት፣ ገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ ያሉ ትኩረት የተሰጣቸው ስራዎች መኖራቸው፣ በክልሉ ከፍተኛ የሆነ እምቅ የመልማት አቅም /ለምሳሌ የተፈጥሮ ሀብት፣ ሰብዓዊ ሀብት፣ ባህላዊ ሀብት፣ ወዘተ/ መኖሩ፣ ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት ዕድል መኖሩ፣ ክልሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ እያደገ መምጣቱ፣ ቀደም ባሉት ዓመታት በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች የተመዘገቡ ውጤቶች ለቀጣይ ስራዎች መሰረት የጣሉ መሆናቸው፣ የክልሉ ህብረተሰብ ለመልማት ያለው ፍላጎትና ተነሳሽነት ከጊዜ ወደ ጊዜ

እያደገ መሄዱ፣ በክልሉ ያለው የቴክኖሎጅና የተሻሻሉ አሰራሮች አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ እንዲሁም እንደ ዘመናዊ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድን፣ ኢንፎርሜሽን ትክኖሎጅ ያሉት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋና መልካም አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

### ስጋቶች/ችግሮች

በክልሉ እየታየ ያለው የሠላም ችግር፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ የመጣው የዋጋ ንረት፣ የስራ አጥነት በተለይም የወጣቶች የስራ አጥነት ችግር ከፍተኛ መሆኑ፣ በክልሉ የነበረው የድህነት ምጣኔ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም አሁንም ብዙ የህብረተሰብ ክፍል በድህነት ውስጥ የሚኖር መሆኑ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከፍተኛ መሆኑ፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኘው ተፈናቃይ ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ፣ የልማት ፋይናንሱ ከክልሉ የመልማት ፍላጎት ጋር አለመጣጣም፣ የድርቅ አደጋ ተጋላጭነት፣ በየደረጃው ያለው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ ፕሮጀክቶችን በጊዜ፣ በጥራትና በተመደበው በጀት የማጠናቀቅ ትልቅ ችግር መኖሩ፣ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ ግብዓቶች በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት የአቅርቦት ችግር መኖሩ፣ የግብርና ምርቶች ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ ወደ ገበያ በወቅቱና በአስተማማኝ ሁኔታ የሚቀርቡበት አምራችና ሸማቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ ግልጽና ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓት ተሟልቶ አለመገኘቱ፣ የንግድ ሥርዓቱ ተወዳዳሪነትና ቅልጥፍና የጎደለው መሆኑ እንዲሁም የግል ባለሃብቱ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋና ስጋቶች/ችግሮች ሆነው ተለየተዋል፡፡

### የስጋት መከላከያ ስትራተጂዎች

ለክልሉ ልማት ወሳኝ የሆነው የክልሉ ሠላምና ጸጥታ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሲሆን ተፈናቃዮችን ለማቋቋምም ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ በክልሉ እንዲሁም በአገር ደረጃ ያሉትን ዕድሎች አሟጦ መጠቀም ዋነኛው የስጋት መከላከያ ስትራቴጂ መሆን ያለበት ሲሆን የተለዩ ስጋቶች/ችግሮች በተጨባጭ ከመከሰታቸው በፊት ለመከላከል የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡ የድርቅ ተጋላጭነትን ከመከላከል አንፃርም በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የህዝቡን ግንዛቤ ይበልጥ በማስፋትና በማዳበር በተለይ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ቀደም ባሉት ዓመታት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት በተሟላ ሁኔታ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋዎችን ለመከላከል በሁለም የክልሉ አካባቢዎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማሰፈን ጥረት ይደረጋል፡፡

የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ለማጠናከር ጥረት የሚደረግ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በእያንዳንዱ ዘርፍ የተቀመጡ ዓላማዎችና ግቦች በታቀዱበት አግባብ መሠረት መፈጸማቸውን የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል ለገበያ (ለአገር ውስጥም ሆነ ለዓለም ገበያ) የሚቀርቡ ምርቶች በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በትኩረት ይሠራል፡፡ በተጨማሪም አቅም በፈቀደ መጠን ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች ለመተካት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ከምንጊዜውም በላቀ ደረጃ በማሳደግ በቂ የክልል ብሎም የአገር ውስጥ የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥ ለቀላልና መካከለኛ የአምራች ኢንደስትሪዎች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት ግብዓት ለማቅረብ እና የግብርናውን ዘርፍ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን ልማታዊ ባለሃብቱ በአምራች ኢንዱስትሪዎች በስፋት እንዲሳተፍ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ የሚሠራ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት፡- የክትትልና ድጋፍ አግባብ

በበጀት ዓመቱ የተቀረጹ ግቦች ለማሳካት በተቀመጡ አመልካቾች መሰረት ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡

**ሁሉም ፈጻሚ ቢሮዎች**

- ✓ በሥራ ክፍል ደረጃ በየወሩ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያደርጉ ይሆናል
- ✓ የዕቅድ አፈጻጸም ሂደት የመስክ ምልከታዎች ይደረጋል
- ✓ በየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለሚመለከታቸዉ አካላት ማሳወቀ
- ✓ በየዘርፉ ላሉ የህዝብ ተወካይ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች አፈጻጸሞችን ተከታትሎ ሪፖርት ማድረግ፡

**የክትትልና ግምገማ አግባብም፡-**

- ✓ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፤
- ✓ በዘርፍ ደረጃ የሚካሄድ ግምገማ፤
- ✓ የመስክ ግምገማ/ሱፐርቪዥን ግኝትና ተሞክሮን በመቀመር ግብረ- መልስ በመስጠት
- ✓ የዳሰሳ ጥናቶችን በማድረግ፣
- ✓ የግምገማ ውጤቱ መሰረት ያደረገ እውቅና በመስጠት

በክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ውስጥ ተሣታፊ ሚሆኑ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻዎች የሚኖራቸው ሚና እንደሚከተለዉ ተመላክቷል፡፡

**የሕዝብ ምክር ቤቶች፡-** ምክር ቤቶች በቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት፣ አሠራር፣ በመስክ ክትትልና ቁጥጥር፣ በየደረጃው በሚካሄዱ የምክር ቤት ጉባዔዎች፣ በሕዝብ ውይይቶች አፈጻጸሙን በመከታተል የሚገመግሙ ይሆናል፡፡

**በየደረጀው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት፡-** ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ዕቅዶች በወቅቱ፣ በጥራት፣ በተጠያቂነትና በተሻለ አመራርና በሕዝብ ተሣትፎ እየተፈፀሙ መገኘተቸውን መከታተል፣ መገምገም፣ መደገፍና ቀጣይ አቅጣጫና አመራር መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

**የክልሉ ህብረተሰብ፡-** የዕቅዱን አፈጻጸም ለመከታተል፣ ለመገምገምና ድጋፍ ለመሥጠት በሚያመችው መልኩ በሚፈጠሩ መድረኮች ይሳተፋል፡፡

**ገንዘብር ቢሮ፡-** የሀብት አመዳደብ ሥርዓት ከጊዜና ከግብ ጋር ጥምረት ፈጥረውና በተሻለ ወጪና ጥራት እንዲፈጸሙ በማድረግ ዙሪያ ግንባር ቀደም ተቋም በመሆኑ በየደረጃው የሀብት አጠቃቀም ሥርዓት በተጠያቂነት እንዲመራ ያደርጋል፡፡

**ፕላንና ልማት ቢሮ፡-** በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዙ ዋና ዋና የልማትና የመልካም አስተዳደር ግቦች በሚጠበቀው ደረጃ እየተፈጸሙ ያሉ ስለመሆናቸው ይከታተላል ይገመግማል ዉጤቶችን አዝማሚያዎችን በማየት ለዉሳኔ ሰጭ አካላት ያሳዉቃል ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል ያስወስናል፡፡

**የክልሉ ዋና ኦዲተር፡-** አጠቃላይ የሃብት አጠቃቀም ሥርዓቱ ላይ የፊዚካል እና የፋይናንስ ኦዲት በማድረግ የሃብት አጠቃቀም ሥርዓቱ ከአሠራርና ሕግ አኳያ ክትትል የሚያደርግ ይሆናል፡፡

**የሚዲያና የኮሚኒኬሽን ተቋማት፡-** ተቋማቱ የሚሠሯቸው የዘገባ፣ የሕዝብ ግንኙነት ተግባሮችና የሚፈጥሯቸው የሕዝብ ውይይቶችና መድረኮች ለክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ማዕከል ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግና የተቋማቱ እንቅስቃሴዎች ዋና ዋና ግቦች ላይ ያተኮረ እንዲሆንና ለግቦች መሣካት አስተዋፅኦ በሚያደርግ መልኩ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ይሰራል፡፡

በአጠቃላይ የዕቅዱን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የአፈጻጸም ምዘና ስርዓት የተዘረጋ በመሆኑ ይህንን አሰራር ይበልጥ በማጠናከር የተጠያቂነትንና የማበረታቻን አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊው ሁሉ ጥረትና ክትትል ይደረጋል፡፡

**የዕቅዱ ታሳቢዎች**

- ✓ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ታሳቢ የተደረጉ ጉዳዮች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል
- ✓ የተከሰተው የፀጥታ ችግር ተፈቶ የሰላም ሁኔታ እየተሻሻለ እንደሚሄድ
- ✓ በአዲስ ለመታረስ የተለዩ የእርሻ መሬቶችን በስፋት ወደ ልማት ለማስገባት
- ✓ የግብርና ሜካናይዜሽንና እና ሌሎች የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች በሰፊው ጥቅም ላይ ማዋልን

- ✓ በየደረጃው ያለው የሰው ሃይልና ተቋማዊ አደረጃጀት ቀልጣፋና ዉጤታማ እንደሚሆን በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች የወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በሙሉ አቅማቸዉ ወደስራ እንደሚገቡ
- ✓ አዲስና ነባር ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸዉን ተግዳሮቶች በመቅረፍ በሙሉ አቅማቸዉ እንደሚያመርቱ
- ✓ ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ የልማት ዘርፎች ተመጣጣኝ የበጀት አመዳደብ እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- ✓ ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ የህዝብና የመንግስት ጉዳዮች
  - የአማራ ክልል ህዝብ የወሰንና ማንነት ጥያቄዎች፣
  - የሀገራዊ ምክር ኮሚሽን ስራዎች፣
  - ተፈናቃይ የመንከባከብና የማስመለስ ጉዳይ ወዘተ ስራወች በራሳቸው እቅድ ታቅደው የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡